## የግብፅ አፍሪካ ዋንጫ
ከፍቅሩ ኪዳኔ

## የአክሊሉ ለማና የካሳሁን ግርማሞ ትውስታ
ፋንታሁን ኃይሌ

## ወጣት "የለውጥ ምክንያት የለውጥ እንቅፋት"

## የጋዜጣ የሕትመት ታሪክ፤ በኢትዮጵያ!
ብሩክ መኮንን

## ኢሕአዴጎች ኢትዮጵያን ማስተዳደር ካልቻሉ...?
መታሰቢያ መልአከ ሕይወት


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 67 ነሐሴ 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99




## ከችግኝ ዘመቻው ወዲህና ወዲያ!

### የትግራይ "ዘመቻ መለስ ለአረንጓዴ ልማት" ለምን?



## "ካለንበት የመጠፋፋት ችግር እንደምንወጣ ተስፋ አደርጋለሁ"
ደራሲና ዳይሬክተር አምለሰት ሙጬ



## ‹‹ጥሩ ሥራ ሁሌም ፈተና ይበዛዋል››
ቀኛዝማች ኃይሉ ቃለወልድ

የእነ ብርጋዲየር ተፈራ እና የጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ የፍርድ ቤት ውሎ!!

.........2.........

የአረንጓዴ አሻራው ሪከርድ፣ የሚያመጣቸው ሕዝባዊ ትሩፋቶች!

.........4.........

ወጣት
“የለውጥ ምክንያት /የለውጥ እንቅፋት”
(ቄሮ፣ ፋኖ፣ ኤጀቶ ፣ሄጎ፣ ዘርማ፣ ፄላጋ፣ ጉርማሾ...)
መላክ ቢ.

.........7.........

የሆቴሎች ደረጃ በኢትዮጵያ!
“ሆቴሎቻችን የት ላይ ናቸው?”
በዝግጅት ክፍሉ

.........10.........

የግብፅ አፍሪካ ዋንጫ
ከፍቅሩ ኪዳኔ

.........11.........

ኢሕአዴጎች ኢትዮጵያን ማስተዳደር ካልቻሉ...?
መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

.........12.........

ቅምሻ

.........13.........

«ጥሩ ሥራ ሁሌም ፈተና ይበዛዋል»
ቀኛዝማች ኃይሉ ቃለወልድ

.........14.........

የጋዜጣ የሕትመት ታሪክ፤ በኢትዮጵያ!
ብሩክ መኮንን

.........16.........

“ኢትዮጵያዬ ብንረሳሽ ቀኝ ትርሳን”
ተሾመ ሺፈራው

.........17.........

የአክሊሉ ለማና
የካሳሁን ግርማሞ ትውስታ
ፋንታሁን ኃይሌ

.........19.........

ድንበሩ እና CVዉ
ዳንኤል ካሣ

.........21.........

እራስን በራስ ያሳዬ ውይይት
በአያሌው አስረስ

.........22.........

ዓለም ዓቀፍ ተሸላሚዋ መዓዛ መንግስቴ
ብሩክ መኮንን

.........23.........

ጥበብ በኛ ዘመን ማለት በዚህኛው
ፍቅርተ ተሾመ

........24.........

ዝክረ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጴጥሮስ!
የ83ኛ ሙት ዓመት ማስታወሻ

........25.........

ከችግኝ ዘመቻው ወዲህና ወዲያ!
የትግራይ “ዘመቻ መለስ ለአረንጓዴ ልማት” ለምን?

.........28.........



ቁጥር 66 ዕትም

ግዮን

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ነሐሴ 4
ይጠብቁን!

5



“ካለንበት የመጠፋፋት ችግር እንደምንወጣ ተስፋ አደርጋለሁ”
ደራሲና ዳይሬክተር እምለሰት ሙጬ

# ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሀገሪቱን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አጠንክሮ እየሰራ መሆኑ ተገለፀ

የኢፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ገዱ አንዳርጋቸው በአንድ ቀን ሁለት ለሀገሪቱ የላቀ ጠቀሜታ ያላቸውን የዲፕሎማሲ ተግባራት በተሳካ ሁኔታ ማከናወናቸው ተገለፀ፡፡

ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሐምሌ 23 ቀን 2011 ዓ.ም የኒካራጓ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑትን ክቡር ዴኒስ ሮናልዶ ሞንካዳ ኮሊንደርሰንን በፅ/ቤታቸው ተቀብለው ያነጋገሩ ሲሆን፣ በሰዓታት ልዩነትም የኢጋድ ልዑካን ቡድንን ተቀብለው በደቡብ ሱዳን የሰላም ስምምነት አተገባበር ዙሪያ ውይይት አድርገዋል፡፡

የኒካራጓ አቻቸውን በተቀበሉበት ወቅት “ኢትዮጵያ ከላቲን አሜሪካ አገሮች ጋር ያላትን የሁለትዮሽ እና የባለብዙ ወገን ግንኙነት ይበልጥ በማጠናከር በተለይም በደቡብ-ደቡብ የትብብር መንፈስ በጋራ ለመስራት ፍላጎት አላት” ያሉት አቶ ገዱ አንዳርጋቸው የኒካራጓ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የኢትዮጵያ ጉብኝት በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ሁለቱ አገሮች ያላቸውን ፍላጎት እንደሚያሳይ ገልፀዋል፡፡

የኒካራጓ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ክቡር ዴኒስ ሮናልዶ ሞንካዳ በበኩላቸው ለኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት ያላቸውን አክብሮት ገልፀው አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላት አመልክተዋል፡፡

በሁለቱ አገሮች መካከል የሚደረገውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር ሀገራቸው በኢትዮጵያ ኤምባሲዋን ለመክፈት መወሰኗንም አያይዘው ገልፀዋል፡፡

ኩባ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ላለፉት ዓመታት ኒካራጓንም ሸፍኖ ሲሰራ የቆየ ሲሆን፣ ኒካራጓ አሁን በአዲስ አበባ ኤምባሲዋን ለመክፈት በእንቅስቃሴ ላይ ትገኛለች፡፡

በሌላ በኩል የኢጋድ መልዕክተኛ የሆኑን አምባሰደር ዶ/ር ኢስማኤል ዋዓይስን፣ አምባሳደር ሌ/ጄነራል አጉስቲኖን እና ሜ/ጄነራል ደስታ አቢቾን በደቡብ ሱዳን የሰላም ስምምነት ትግበራ ዙሪያ ያነጋገሩት ው/ጉ/ሚ/ር ገዱ አንዳርጋቸው ኢትዮጵያ በኢጋድ ባላት የሊቀመንበርነት ሚናና እንደጎረቤት ሀገርም ደቡብ ሱዳን ሰላም የሰፈነባት ሀገር እንድትሆን አስፈላጊውን ድጋፍ እንደምታደርግ ገልፀዋል፡፡

ውይይቱ በጁባ በተካሄደው 67ኛው የኢጋድ ሚኒስትሮች ም/ቤት አስቸኳይ ስብሰባ የተላለፉ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችሉ ጉዳዮች እና ባጋጠሙ ችግሮች ዙሪያ እንዲሁም የሰላም ሂደቱ አፈፃፀም ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በጋራ ለመምከር የተካሄደ መሆኑን የው/ጉ/ሚ/ር ቃል አቀባይ ጽ/ቤት ለግዮን መጽሔት በላከው መግለጫ አስታውቋል፡፡

## በድሬዳዋ ሚሊኒየም ፓርክ በዛፍ ጥላ ስር የሙከጀላትና ጌድ ሆስት ምክክር ይካሄዳል

የሙከጀላትና ጌድ ሆስት ሐምሌ 24 ቀን 2011 ዓ.ም “ቤት ሳይፀዳ ደጅ አይጠረግም” በሚል ርዕስ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል፡፡ ዓለም አቀፍ ሞዴል ፈትያ እ.ኤ.አ፣ በ2019 በላስቬጋስ በተካሄደ የቁንጅና ውድድር የማህበራዊ ህይወት አሸናፊ መሆኗ ይታወሳል፡፡ ይህንን ሓላፊነቷን የትውልድ ከተማዋ በሆነችው ድሬዳዋ ለመጀመር አገር በቀል እውቀት ላይ የተመሰረተውን “የሙኩጀላትና ጌድ ሆስት ማስታወስ” ከትውልዱ ጋር ማገናኘት ተቀዳ ተግባርዋን አድርጋለች፡፡

ኡጋዞች፣ የሐይማኖት አባቶች፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ የድሬዳዋ ልጆች፣ ወጣቶች፣ ሴቶችን፣ በድሬ ከተማ ተወልደው ያደጉ የውጭ ሀገር ሰዎችና የመንግስት ባለስልጣናት በሚታደበሙበት፣፤በድሬዳዋ ከተማ ሚሊኒየም ፓርክ ውስጥ ባለ የዛፍ ጥላ ስር ፕሮግራሙ እንደሚካሄድም ሞዴል ፈትያ በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ አስታውቃለች፡፡

# እውን የበጎ አድራጎት ማህበር ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ ዊልቸር አስመረቀ!



በሴት አካል ጉዳተኞች ጤና እና ሥነ ተዋልዶ ላይ ትኩረት በማድረግ እንቅስቃሴ የጀመረው እውን የበጎ አድራጎ ማህበር ሰው ሰራሽ የሆኑ መርጃ ድጋፎችን ለአካል ጉዳተኞች ለማድረስና በበጎፈቃደኝነት ከሚያገለግሉ ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ ሆኖ የተሰራውን ዊልቸር ለማስመረቅ በጁፒተር ኢንተርናሽናል ሆቴል ልዩ ፕሮግራም አከናውኗል፡፡

ማክሰኞ ሐምሌ 23 ቀን 2011 ዓ.ም በተከናወነው በዚሁ መርሃ ግብር የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ወ/ሮ የአለም ፀጋዬ እና የአዲስ አበባ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ም/የቢሮ ሀላፊ በክብር እንግድነት የተገኙ ሲሆን፣ የመንግሥት ሥራ ሀላፊዎቹ የማህበሩን ዓላማዎች በእጅጉ አድንቀው አካል ጉዳተኞችን ለመደገፍ የተጀመረውን ስራ ለመደገፍ ቃል ገብተዋል፡፡

የእውን በጎ አድራጎት ማህበር ዋና ስራ አስፈፃሚ የሆነችው ጋዜጠኛ ማርታ ደጀኔ በዕለቱ ፕሮግራም ባደረገችው የመክፈቻ ንግግር ማህበሩ በሴቶች ጤናና ሥነ ተዋልዶ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራው በሀገራችን ለዚህ ብርቱ ጉዳይ የተሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ እንደሆነ ገልጻ በተለይም የህክምና ተቋማት ለሴት አካል ጉዳተኞች ምቹ እንዳልሆኑ አመልክታለች፡፡

“የሀገራችን ህክምና ተቋማት ከምርመራ አልጋቸው ጀምሮ ምቹ አይደሉም፡፡ የጤና ባለሙያዎቹም በአብዛኛው ስለ አካል ጉዳተኝነት ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ ዝቅ ያለ ነው፡፡ ሴት አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም የሰው ፍጡር አርግዘው የልጅ እናት መሆን ቢፈልጉም የህክምና ባለሙያዎች ግን ከማገዝ ይልቅ መከልከል ላይ አይሆንም ማለት ላይ ያመዝናሉ” ያለችው ጋዜጠኛ ማርታ ደጀኔ “እኔ አካል ጉዳተኛ ብሆንም የ3 ልጆች እናት ከመሆን ያገደኝ ነገር የለም” በማለት አካል ጉዳተኞች ወልዶ የመሳምን የተፈጥሮ ፀጋ እንዳያጣጥሙ የሚያደርጋቸው ነገር እንደሌለ ራሷን ምሳሌ አድርጋ አስረድታለች፡፡ ማህበሩ በተመሰረተ አጭር ጊዜ ውስጥ ታላላቅ ስኬቶችን ለማስመዝገብ የቻለ ሲሆን፣ በማህበሩ የተገጣጠመ አዲስ ዊልቸር በዕለቱ ፕሮግራም ተመርቋል፡፡

ለአካል ጉዳተኞች የእንቅስቃሴ ድጋፍ የሚሆነው ዊልቸር እንደ ምግብና መጠለያ ሁሉ መሠረታዊ መሆኑን የጠቀሰችው ጋዜጠኛ ማርታ ደጀኔ የአንድ ዊልቸር ዋጋ አሁን ባለው ገበያ ከ20 -25 ሺህ ብር የሚያወጣ ሲሆን፣ አብዛኛው አካል ጉዳተኛ ግን በችግር ውስጥ ያለ በመሆኑ ይህን ወጪ ሸፍኖ ዊልቸር የመግዛት አቅም የለውም፡፡ እውን በጎአድራጎ ማህበርም ይህን ችግር በማጤን ነው በዝቅተኛ ዋጋ በራሱ ወርክሾፕ የተገጣጠሙ ዊልቸሮችን ለማቅረብ እየሰራ ያለው፡፡

በዕለቱ መርሃ ግብር የተመረቀውን ዊልቸር የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስትሯ ወ/ሮ የአለም ፀጋዬ ጧፍ በመሸጥ ልጆቿን ለምታሳድግ አንዲት አካል ጉዳተኛ ገዝተው ስጦታ ያበረከቱላት ሲሆን፣ በዚህም አቅም ያላቸው የሌላቸውን የማገዝ ባህል እንዲያዳብሩ ተግባራዊ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# የእነ ብርጋዲየር ተፈራ እና የጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ የፍርድ ቤት ውሎ!!

ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በሀገራችን ከተከሰተው ሁኔታ ጋር በተያያዘ እጃቸው አለበት በሚል የተጠረጠሩ 57 ተከሳሾች ከእስር ተፈቱ፡፡ በዚህ መዝገብ 218 ተጠርጣሪዎች የተያዙ ቢሆንም ቀደም ሲል 103ቱ ጉዳያቸው ተጣርቶ መለቃቀቸው ይታወሳል፡፡ ቀሪዎቹ ችሎት ከቀረቡት መካከል ብርጋዴር ጀኔራል ተፈራ ማሞ፣ ኮሎኔል አለበል አማረና ኮሎኔል ባምላኩ ዓባይን ጨምሮ ሌሎች ተጠርጣሪዎች ይገኙበታል፡፡የተጠርጣሪ ጠበቆች ኮሎኔል አለበል አማረና ኮሎኔል ባምላኩ ዓባይ እስካሁን ተጨባጭ ማስረጃ እንዳልተገኘባቸው በምርመራ ቡድኑ መረጋገጡን ጠቅሰዋል፡፡

እንዲሁም ብርጋዴር ጀኔራል ተፈራ ማሞ የተፈጠረውን ችግር ለመመከት ሲሰሩ የነበሩ መሆናቸውን እየተካሄደ ባለው ምርመራ መረጋገጡንና እስካሁን ማስረጃ አለመገኘቱን ጠበቆቹ አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም በስም ተጠቃሾቹ በጉዳዩ የተሳተፉ አለመሆናቸው በተካሄደው ምርመራ እየታየ በመሆኑ ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ ሳይሰጣቸው መዝገቡ ተዘግቶ እንዲለቀቁ ችሎቱን ጠይቀዋል፡፡ ከተጠርጣሪ እስረኞች መካከል የመቁሰል አደጋ ያለባቸው ተጠርጣሪዎች ስማቸው ተዘርዝሮ ሕክምና እንዲያገኙ ችሎቱ እንዲያዝም ነው ጠበቆቹ የጠየቁት፡፡

ኮሎኔል አለበል አማረ በበኩላቸው “ከታሰርን ጀምሮ አመላካች ውጤት ባለመገኘቱ ቤተሰቦቻችን እየተጎዱ በመሆኑና የመንግሥት ሠራተኞች በመሆናችን ፍርድ ቤቱ ጉዳያችንን በአግባቡ መዝኖ ሊለቀን ይገባል” ብለዋል፡፡ ብርጋዴር ጀኔራል ተፈራ ማሞ ደግሞ “ችግሩ እንዳይሰፋና ወደ ከፋ ጫፍ ሁኔታ እንዳይሄድ ያስቆምኩት እኔ ነኝ” በማለት ለችሎቱ ተናግረዋል፡፡ “እስካሁን በምርመራ መዝገቡም ማስረጃ ማቅረብ አልተቻለም፤ ምንም በሌለ ጉዳይ መታሰሬ አግባብ ባለመሆኑ ልለቀቅ ይገባል” ሲሉም ችሎቱን ጠይቀዋል፡፡

መርማሪ ፖሊስ በበኩሉ የተጠርጣሪዎች ጉዳይ በጥንቃቄና በፍጥነት እየታየ ነፃነታቸው የተረጋገጠላቸው እየተፈቱ መሆኑን ለችሎቱ አስረድቷል፡፡ ይሁን እንጅ ከታሰሩት መካከል ቀጥታና በተዘዋዋሪ የተሳተፉ እንዲሁም ከችግሩ ነፃ የሆኑ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ በመጥቀስ፥ ጉዳዩ በሰውና በቴክኒክ ማስረጃ እንዲጣራ ተደርጎ ከወንጀሉ ንጹህ የሆኑ ሰዎች እንደሚፈቱ አስታውቋል፡፡

በተያያዘ ከሰኔ 15ቱ ሁኔታ ጋር በተያያዘ እጃቸው አለበት በሚል ተጠርጥረው ከታሰሩት ዜጎች መካከል አንዱ የሆነው ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ በጠበቃው ተማም አባቡልጉ በኩል ያቀረበው “አካልን ነፃ የማውጣት” ክስ ውድቅ ሆኗል፡፡

“የኛ ጥያቄ በሽብር የተከሰሰን ሰው የመርመር ሥልጣን የፌደራል ፖሊስ እንጂ የአዲስ አበባ ፖሊስ አይደለም ነገር ግን ሥልጣን ተሰጥቶኛል ካለ ፍ/ቤቱ ላይ ያቅርብ” የሚል አቋም ይዘው የተከራከሩት ጠበቃ ተማም ከችሎቱ የተሰጣቸው መልስ “ተጠርጣሪው ግለሰብ ከተያዘ በኋላ ፍ/ቤት ስለቀረበ በአካል ሊለቀቅ አይገባም” የሚል ውሳኔ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

# ኩዊንስ ኮሌጅ ከምርቃቱ በስተጀርባ ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑ ተገለፀ

ኩዊንስ ኮሌጅ ከ21 ዓመታት በላይ ማህበረሰቡን እያገለገለ የሚገኝ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሲሆን፤ ከምርቃቱ በስተጀርባ ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን ወ/ሮ ሰብለ ምሩፅ ሐምሌ 23 ቀን 2011 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ ኮሌጁ በተለያዩ ዘርፍ በቴክኒክና ሙያ እንዲሁም በዲግሪ መርሃ ግብር ያሰለጠናቸውን 5.007 ተማሪዎች ለ20ኛ ዙር ባስመረቀበት ወቅት ገልፀዋል፡፡

ኮሌጁ ገቢያቸው ዝቅተኛ ለሆኑና በተለያዩ የመንግስትና የግል ሰራተኛ ሆነው ለሚተዳደሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የክፍያ ቅናሽ በማድረግ፣ ለጥቂቶች ሙሉ በሙሉ ነፃ የትምህርት ዕድል በማመቻቸትም ውጤታማ ሆኗል፡፡ኩዊንስ ኮሌጅ 640 ተማሪ በነፃና በግማሽ ክፍያ ስኮላር በመስጠት ማስተማሩ በምርቃቱ ወቅት ተነግሯል፡፡

ደራሲና ገጣሚ ሠርክዓለም አልታዬ (ሪታ) አረፈች!!

ደራሲ፣ ገጣሚ፣ እንዲሁም የበጎ ሰው፣ ሠርክዓለም አልታዬ (ሪታ) በ1956 ዓ.ም ሚያዝያ 23 ቀን ተወልዳ በ55 ዓመቷ በቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል በህክምና ስትረዳ ቆይታ፣ ከዚህ ዓለም በድንገት ሐምሌ 24 ቀን 2011 ዓ.ም አርፋለች፡፡ በኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር በሂሳብ ሹም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሆና ለ5 ዓመት እና በንዑሳን ኮሚቴ ውስጥ አባል በመሆን መሬት እንዲሰጥ ካደረጉት ውስጥ ተጠቃሽ ነች፣ በሴት ደራሲያን ማህበር ለበርካታ ዓመታት አባል ሆና በሴት ደራሲያን ማህበር ለበርካታ ዓመታት አባል ሆና አገልግላለች፡፡

ሠርክዓለም አልታዬ(ሪታ) ከዚህ ቀደም ‹‹ ቀለበት፣ ሳዱላ፣ ያልተመረቀው ›› የሚል 3 መጽሐፍት ነበራት ለህትመት የተዘጋጁ ስራዎችም እንዳላት ጓደኞቿ ይናገራሉ፡፡ ልቦለድ ታሪኮችንና ግጥሞችን በሲዲ በማሳተም ፈር ቀዳጅና ለጋስ ነበረች፡፡ ሠርክዓለም አልታዬ የአንድ ወንድና የሶስት ሴቶች ልጆች እናት ነበረች ሥርዓተ - ቀብሯ ሐምሌ 26 ቀን 2011 ዓ.ም ጉለሌ የሚገኘው ጴጥሮስ ወጳውሎስ መካነ መቃብር በ7፡00 ሰዓት ተፈፅሟል፡፡

# የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት ያስተማራቸው በከፍተኛ ነጥብ ተመረቁ

ከአመታት በፊት ከደቡብ ወሎ ዞን የአምባሰል ወረዳ ነዋሪዎች ጋር በተደረገ ምክክርና ውይይት ቤተሰቦቻቸው የማስተማር አቅም የሌላቸውን 30 ታዳጊዎች ወስዶ ሲያስተምር የቆየው የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት በጎ አድራጎ ማህበር ዘንድሮ 16 ተማሪዎቹ በከፍተኛ ነጥብ ከዩኒቨርስቲዎች መመረቃቸውንና ደስታውን ከቤተሰቦቻቸው ጋር ለመጋራት በአምባሰል ወረዳ ውጫሌ ከተማ ደማቅ ፕሮግራም ማዘጋጀቱ ተገለፀ፡፡

በዘንድሮው ዓመት ከተመረቁት የሶሻል ሳይንስ 16 ተማሪዎቹ መካከል አንዷ በፊዚክስ ትምህርት ክፍል ባስመዘገበችው ከፍተኛ ውጤት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመምህርነት እንድትቀጥል መመረጧ ሲታወቅ የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት አስተምሮ ለቁም ነገር ካበቃቸው ከእነዚህ 16 ኢትዮጵያውያን መካከል ስምንቱ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተቀሩት ስምንቱ ደግሞ ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የመጀመሪያ ዲግሪቸውን እንደተቀበሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ውጫሌ ከተማ በሚገኘው የትምህርት ማዕከል የልጅነት እና የታዳጊነት ጊዜያቸውን ያሳለፉት እነዚህ ውጤታማ ዜጎች አሁን ያገኙትን ታላቅ ስኬት በማስመልከት የአካባቢው ህዝብና ቤተሰቦቻቸው በተገኙበት ለሚካሄደው “በቤተሰቦቸው ፊት የማስመረቅ ሥነ ሥርዓት” ዝግጅቱ ከሞላ ጎደል መጠናቀቁን የገለፁልን የድርጅቱ መስራችና ስራ አስኪያጅ ወ/ሮ መቅደስ ዘለለው ሲሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በአደራ ተረክቦ ካስተማራቸው 30 ኢትዮጵያውያንና አሁን ከተመረቁት ውጪ ያሉት 14 ተማሪዎች በቀጣዩ ዓመት የሚመረቁ መሆኑንና ተማሪዎቻቸው ያዝመዘገቡት የመመረቂያ ነጥብ ከ3.6 እስከ 3.9 የሚደርስ መሆኑ በእጅጉ እንዳኮራቸው ገልፀውልናል፡፡

የዚህ በጎ አድራጎት ማህበር መስራቿ ወ/ሮ መቅደስ ዘለለው ከዚህ ቀደም ከበርካታ ሀገራት እና የሽልማት ተቋማት የእውቅናና የውጤታማነት ሽልማቶችን ያገኙ ሲሆን የግዮን መጽሔት ዝግጅት ክፍልም በቀጣይ ዕትም እኒህን ታላቅ ባለ ራዕይ ስኬታማ እናት በእንግድነት የሚጋብዝ መሆኑን ከወዲሁ ለመግለፅ ይወዳል፡፡

# የአረንጓዴ አሻራው ሪከርድ፣ የሚያመጣቸው ሕዝባዊ ትሩፋቶች!

ሐምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም ሃገራችን ኢትዮጵያ ደማቅ ታሪክ ጽፋለች፡፡ ስልጣን ከያዙ አንድ ዓመት ከአራት ወር የሞላቸው የለውጡ ቡድን ፊታውራሪ አሁንም ከሚተቿቸውና ከሚቃወሟቸው እጅግ በላቀና በገዘፈ መልኩ፤ የበርካታ ሚሊዮኖችን ሕዝብ ድጋፍና አድናቆት ያስገኙላቸውን አኩሪ ተግባር እየፈጸሙ ይገኛሉ፡፡ ጎልማሳው ጠ/ሚ/ር በኢሕአዴግ ዘመን ካየናቸው መሪዎች በተሻለ መልኩ አዳዲስ ሐሳቦችን እያመነጩ፣ ከሕዝብ ጋር ህልማቸውን እውን ማድረጉን ተያይዘውታል፡፡

ገና በማለዳው የሃገሪቱን የፖለቲካና የሕሊና ዕስረኞችን በግፍ ከታሰሩበት ካቴና አላቀው፣ ነጻነታቸውን እንዲያውጁ አድርገዋል፡፡ ለሃገርና ለሕዝብ መብት፣ ዲሞክራሲን ለማስፈን የሚደረግና አንዱን አስበልጦ ሌላውን የማይገፋ እውነተኛ ትግል ጊዜውን ጠብቆ ዋጋ እንደሚያስከፍል ባሳየ ዕርምጃቸው፤ አምባገነኑ ስርዓት ከየመን ድረስ አፍኖ ያሰረውን አንዳርጋቸው ጽጌን፤ በብሔራዊ ቤተ መንግስት ጋብዘው፣ ክብርን ሲሰጡት አሳዩን፡፡

በሁለት የበርሃ ድርጅቶች አለመግባባት ከ20 ዓመት በላይ ተዘግቶ የቆየውን ኬላ በፍቅር የከፈቱት ጠቅላይ ሚኒስትር፤ የአንድ ወጣት ዕድሜ ያህል ተራርቀውና ተነፋፍቀው የከረሙ ጥንዶችን ሲያስተቃቅፉ፣ ወዲህና ወዲያ ሆነው ለመነጠል የተገደዱ እናትና ልጅን የደስታ እንባ አራጩ፡፡ የሕወሓት መራሹ መንግስት "የጥፋት አፍ ማሚሻ " የነበሩት እንደ አርበኞች ግንቦት ሰባትና ኦነግ ዓይነቶቹ ድርጅቶችም "አገራችሁ ቤታችሁ ነውና በሰላም ግቡ" ተብለው፣ በሩ ወለል ብሎ የተከፈተላቸው ፍቅርና አንድነትን በሚሰብኩት "የአረንጓዴ አሻራ" ደራሲና ዳይሬክተር በሆኑት በእኚህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ መሪ አማካይነት መሆኑ አይዘነጋም፡፡

በአጭሯ የስልጣን ዘመናቸው ዕርቅና ሰላም እንዲሰፍን ተግተው ከመስራት ባሻገር የአንድነትና ኢትዮጵያዊነት ስሜታችን እንዲጎለብት የደከሙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፤ ከሳምንታት በፊት በያዝነው ክረምት ወራት 4 ቢሊዮን ችግኞችን የመትከል መርሃ ግብራቸውን ይፋ አድርገው ነበር፡፡ የእዚህ ታሪካዊ ፕሮጀክት አካል የሆነውና በአንድ ቀን በርካታ ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል ሃገሪቱን በዓለም የክብር መዝገብ ላይ የማስፈር ዕቅዳቸውም ሐምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም ዕውን ሆኗል፡፡

በቢሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ እንዳላት የሚነገርላት ሕንድ በአስራ ሁለት ሰዓታት ውስጥ 66 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል የያዘችውን ሪከርድ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሓሳብና ጥሪ በስድስት ሰዓት ውስጥ አሳክቶታል፡፡ ኢትዮጰጵያውያን ከዳር እስከ ዳር በነቂስ ወጥተው የተገበሩት የችግኝ ተከላ ፕሮግራም፣ በፖለቲካ ልዩነት ውስጥ ያሉ ሰዎችንም አንድ ያረገበትን አጋጣሚ መመልከትም ተችሏል፡፡ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ በዋናነት የተቀመጠው አራት ቢልዮኑ ችግኝ ለታለመለት ዓላማ እስኪተከል ድረስ እንደሚቀጥል መነገሩ ተገቢ ቢሆንም ፤ በታሪካዊው ቀን በተቆፈረላቸው ጉድጓድ ውስጥ ተቀምጠዋል የተባሉት ከ350 ሚሊዮን በላይ ከሚሆኑት ችግኞች መሐል የተወሰኑት በትክክል የሚጸድቁበትንና ተከታታይ እንክብካቤ የሚደረግበት የዘመቻ ፕሮግራሞችም እግረ መንገድ ቢዘጋጁ የበለጠ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ማሰብም ያስፈልጋል፡፡

"ችግራችንን የሚነቅልልን እንጂ፣ ችግኝ የሚተክል መሪ አንፈልግም " በማለት ከኢትዮጵያዊነት ስነምግባር ባፈነገጠ መልኩ ይህንን የተቀደሰ ሃገራዊ ፋይዳ ያለው የልማት ፕሮግራም ከፖለቲካ ትርፍ ጋር ለማያያዝ በማሕበራዊ ሚዲያዎች ሲቀሰቅሱ የከረሙ ሰዎችም ወደ ህሊናቸው እንዲመለሱ፣ ቢያንስ "እንወክለዋለን" ለሚሉት ሕዝብ ተጠቃሚነት ማሰብ እንደሚገባቸው ሳንነግር አናልፍም፡፡ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ ንቅናቄ፤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ተደጋጋሚ ሁከቶች የተከሰተባቸው ስፍራዎችም ተሳታፊ ሆነው መታየታቸውም ይበል የሚያሰኝ ተግባር ነው፡፡

ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ "ከእኔ ክልል ውጣ" በሚል የወረደ አስተሳሰብ፣ ለመፈናቀልና ለስደት የዳረጉ፣ የበርካቶችን ሕይወትና አካል ያጎደሉት፤ የአምላክ ድንቅ ፍጡር ከሆነው የሰው ልጅ ውድ ሕይወት በላይ ችግኝ መትከሉ እንዴት ሊያሳስባቸው እንደቻለ ባይገባንም፤ በዚሁ ልክ የአስተሳሰብ አድማሳቸውን በማስፋት፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም ቦታ ተዋዶና ተፋቅሮ፣ እንዲሁም ተቻችሎ የመኖር መብቱን በማክበር ካለፈ ስህተታቸው የሚማሩበት መልካም አጋጣሚን እንደፈጠረላቸው መጠቆም ግድ ይላል፡፡ በመጨረሻም አረንጓዴ አሻራና ታሪካዊው ሪከርድ ይዟቸው የመጣቸው ይህን መሰሉን ማህበራዊ ትሩፋቶች በርካታ ናቸውና አጋጣሚውን በአግባቡ ልንጠቀምበት እንደሚገባ ለሁሉም ኢትዮጵዊ ጥሪ እናቀርባለን፡፡


**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ

አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2
የቤት ቁጥር 475

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
አለማየሁ ባዘዘው
ብሩክ መኮንን

**አዘጋጅ**
ፍቅርተ ተሾመ
ሙሉጌታ አክሊሉ

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ **(ከሲውዘርላንድ)**
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ፍፁም ንጉሴ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661 +251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ
0911223335/ 0911420506


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# “ካለንበት የመጠፋፋት ችግር እንደምንወጣ ተስፋ አደርጋለሁ”

## ደራሲና ዳይሬክተር አምለሰት ሙጬ




*ከ15 ዓመታት በፊት በአዲስ አበባ ኤግዚብሽን ማዕከል በተካሄደው የ”ሚስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ” ቁንጅና ውድድር፣ ዩኒቲ ኮሌጅን ወክላ በመሳተፍ የአሸናፊነትን ክብርን የተጎናፀፈችው አምለሰት ሙጬ፤ አሁን ለደረሰችበት የላቀ ስብዕና የበቃችው በበርካታ ሂደቶች ውስጥ አልፋ ነው። በሞዴሊንግ ሙያ ውስጥ ከነበራት ንቁ ተሳትፎ ባሻገር፣ በማስታወቂያ አምባሰደርነት፣ በተዋናይነት፣ በጋዜጣ አምድ አዘጋጅነት፣ በደራሲነት፣ በዳይሬክተርነት ዘርፍ ውስጥ ያበረከተቻቸው አስተዋፅዖዎችም በብዙሃን ዘንድ የሚታወቁና አድናቆትን ያስገኙላት ናቸው።*

*ከተወዳጁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) ጋር በጋብቻ ተጣምራ የሁለት ልጆች እናት ለመሆን የበቃችው ሁለገቧ አምለሰት ሙጬ፤ በቅርቡ በደማቅ ስነስርዓት አስመርቃ ለእይታ ካበቃችው “ምን አለሽ” የተሰኝ አዲስ ፊልሟ ጋር በተያያዘ ስሟ በስፋት እየተጠቀሰ ነው። ፊልሟን ለማስመረቅ በዚህ ወቅት ዙሪክ ከተማ የምትገኘው አምለሰትን የግዮን መጽሔቱ ፍቃዱ ማ/ወርቅ እንዲህ አነጋግሯታል።*

---

**ግዮን፡- የአዲሱ ፊልምሽ መጠሪያ “ምን አለሽ?” የሚል ነው፤ ስያሜውን እንዴት መረጥሽው?**

አምለሰት፡- ለመገበያየት ስትወጣ ምን አለሽ? ምን አለህ? የሚል የቆየ ልምድ አለን። ያንን ምሳሌ ወይም መነሻ ያደረግሁት በሀገር፣ በኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ ምን አለሽ? ብለህ ብትጠየቅ፣ “ይሄ፣ ይሄ አላት” ብለን ልንነግረው የምንችለው ነገር መኖር አለበት። የጎደለውን የምንሞላበት፣ ያለንን የምናመሰግንበት ዓይነት ነገር እንዲኖር፤ ጥያቄው እጅግ በጣም ያስፈልገናል ብዬ ስላሰብኩኝ ፊልሙን “ምን አለሽ?” ብዬዋለሁ።

**ግዮን፡- አዲሱ ፊልምሽ ቀረፃ ሲጀመር  ርዕሱ “ምን አለሽ ሃገሬ” ነበር፤ ዘግየት ብለሽ ፊልሙን ለዕይታ ስታበቂው ግን  “ምን አለሽ” ብቻ አለሽው ለምንድን ነው?**

አምለሰት፡- ትክክል ነህ። ሃገርን ብቻ ሳይሆን ሰው ማንነቱን፣ ራሱን ነው ማየት ያለበት። ሃገር ሲሆን ሩቅ ይመስለናል፤ እኛ አይደለንም ብሎ የሚያስብ ሰው አለና መልዕክቱ በትክክል ወደ ሰው እንዲገባ ስል ነው የቀየርኩት። ደግሞም ሰው ነው ሀገር ማለት። ራሳችንን፣ ማንነታችንን ስንጠይቅ ነው እንደ ሀገር ልንጠይቅ የምንችለው።

ምን አለሽ ሀገሬ? ስንል ተጠያቂ የምናደርገው ሃገርን ነው፤ ሃገር ማለት ሰው መሆኑን የማይረዳ ሊኖር ይችላል በሚል “ምን አለሽ” በሚል፤ እያንዳንዱ በተናጠል ሲጠየቅና ሁሉም ሰው ያንን መልስ መመለስ ሲችል ሀገርም ታድጋለች፣ በሚፈለገው መንገድም ትገነባለች።

**ግዮን፡-የታሪክ መሰረቱን ምን ዓይነት ጉዳይ ላይ ነው ያደረገው?**

አምለሰት፡- በዋነኝነት ሦስት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል። አንደኛው ድህነት ነው፣ ሁለተኛው ውበት ነው፣ ሦስተኛው ደግሞ ሩጫ ነው። ኢትዮጵያ በዓለም ሀገራት ውስጥ የምትታወቅበት ሦስቱ ነገሮች ናቸው ብዬ አስባለሁም፤ አምናለሁም።

ድህነታችን የሚካድ አይደለም፤ ውበታችንም በደንብ የሚታወቅ ነው። ሩጫችን ደግሞ በዓለም ላይ ስማችንን እያስጠራ ያለ ነገር ነው፤ የኢትዮጵያዊያን አትሌቶችን ስኬታማነት እንደ ተምሳሌትነት ወስደን ሁላችንም በተሰማራንበት መንገድ ብንሮጥ የማይቀየር ነገር የለም። እነዚህ ሰዎች በድህንት ብቻ የምትጠራ ሀገርን ስም እኮ ቀይረዋል። ስለዚህ መሮጥ የማሸነፍን ስሜት ይፈጥራል የሚል ዕምነት ስላለኝ እንደ ማሳያ ተጠቅሜበታለሁ፤ የፊልሙ ሀሳብም በዚህ ዙሪያ ነው።

**ግዮን፡- ፊልሙን ሠርቶ ለማጠናቀቅ ምን ያህል ጊዜ ወሰደ? ምን ያህል ሰዎችስ ተሳትፈውበታል?**

አምለሰት፡- ምን አለሽን ሰርቶ ለማጠናቀቅ ሦስት ዓመት ፈጅቶብኛል። በአጠቃላይ ይህ ስራ  ከአራት መቶ በላይ ሰዎችን አካትቷል። የውጭ ባለሙያዎች አሉ፣ የሀገር ውስጥ ባለሙያዎች አሉ፣ አንድ ላይ ተጣምረው ነው የሠሩት። ሰፊ ጊዜ ወስደን በመግባባትና በመረዳዳት ነው የሠራነው።

**ግዮን ፡- ቀረፃዎችን የት የት አካባቢዎች ነው ያካሄዳችሁት?**

አምለሰት፡- አብዛኛውን ሲን መርካቶ ነው የቀረፅነው፤ ሴታፖችንን ሶስት ቦታ ነው ያደረግነው። አንደኛው መርካቶ ሲሆን፣ ሁለተኛው አዲስ አበባ ስቴዲየም፣ ሶስተኛ ኒውዮርክ ስቴዲየም። በእነዚህ ቦታዎች ላይ ትኩረት ያደረገ የቀረፃ ሂደት ነው የነበረን።

**ግዮን፡- በፊልሙ ላይ የአንቺ ድርሻ ይበዛል። መሪ ተዋናይ፣ ደራሲና የዳይሬክተር እንዲሁም ፕሮዲዩሰር ነሽ። እነዚህን ነገሮች ጠቅልሎ መያዙ አይከብድም?**

አምለሰት፡- “ምን አለሽ” ላይ በድርሰት፣ ዳይሬክቲንግና በትወና ነው የተሳተፍኩት፤ ፕሮዲዩስ አላደረግሁም። ፕሮዲዩስ ማድረግ አልችልም፤ ፕሮዲዩስ ማድረግ ራሱን የቻለ ሌላ ሙያ ነው። በተለምዶ በእኛ ሀገር ሁሉን ነገር ስለምናያይዘው ነው እንጂ ፕሮዲዩሰርነት ብቻውን ትልቅ ሙያ ነው።

ፊልሙ የራሴ ፅሁፍ ስለሆነ ዳይሬክቲንጉ ብዙ አልከበደኝም። አክቲንጉም (ትወናው) ብዙ አላስቸገረኝም። ካራክተሯን የፈጠርኳት ራሴ ከመሆኑ አኳያ፣ ለአክቲንጉ የበለጠ ቅርብ እንድሆን አድርጋኛለች።

የእውነት ለመናገር ከዚህ በፊት የሰራሁባቸው ፊልሞች ላይ የተባልኩትን ብቻ ተቀብዬ ነበር የምሰራው፤ ከዛ በበለጠ ደረጃ እንደተወጣሁት  በርካታ ሰዎች ነግረውኛል። እኔም ልቤ የተሰማኝ እንደዛው ነው፤ ፊፅሞ አልከበደኝም።

**ግዮን፡- እዚህ ሃገር ውስጥ ፊልሙ በቋሚነት መታየት የሚጀምረው**

**መቼ ነው፡፡ አሁን ለማስመረቅ ከተዘጋጀሽበት ዙሪክ ከተማ ውጪ በባህር ማዶ ሌሎች የምረቃ ፕሮግራሞች አሉሽ?**

አምለሰት፡- በእዚህ፣ እዚህ ቦታ አስመርቃለሁ ብዬ የደመደምኩትና የያዝኩት ፕሮግራም የለም፡፡ ግን በአንዳንድ ታላላቅ ኢንተርናሽናል ፌስቲቫሎች ላይ ፊልሙ እንዲታይ ያነጋገሩኝ ሰዎች አሉ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እኔ በሰራሁበት ስታንዳርድ ሊያሳዩልኝ የሚችሉ በጣም ጥቂት ሲኒማ ቤቶች ናቸው ያሉት፡፡ ሁለተኛ እኛ ሃገር የፊልም ማሳየት በራሱ ከስርቆት አደጋ የተጠበቀ ነው ብለህ መደምደም አትችልም፡፡

እንዲህ ዓይነት ነገር ሲከሰት ደግሞ ስሜትህ ይጎዳል፡፡ ለፍተህበት፣ ደክመህበት ስራህ በማትጠቀምበት መንገድ ሕዝብ ጋር ሲደርስ በጣም ትጎዳለህ፡፡ በተወሰነ ደረጃ ሌላ ፊልም ፕሮዲዩስ ሳደርግ የምችልበት ገንዘብ መስራት አለብኝ፣ ደህና ነገር ላይ እንዲደርስ አንዳንድ ሁኔታዎችን እየሞከርኩ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ይሳካል ብዬ አስባለሁ፤ እሱን ነው እየጠበቅሁ ያለኹት፡፡

**ግዮን፡- በእኛ ሀገር ፊልሞች ወዲያው እንደተመረቁ ሲኒማ ቤቶች መታየታቸው ተለምዷልና ምናልባት ይህ የአንቺ አካሄድ ስራሽን በጉጉት ከሚጠብቀው ሕዝብ ጋር አያራርቅሽም?**

አምለሰት፡- የሚወድህና የሚያከብርህ ተመልካች ምንም ጊዜ ቢሆን ይጠብቅሃል፡፡ እኛ ራሱ ፊልሙን እየሠራን ነው ካልን እንኳን ሶስት ዓመት ሆኖናል፡፡ ይሄንን ሁሉ ጊዜ ራሱ በትዕግስት ጠብቆናል፡፡ ስለዚህ ተመልካቹ አሁን ያሉብንን የጥንቃቄ ክፍተቶች እስክንሞላ ድረስ የምናደርገውን ሁሉ በትክክል ይረዳል፡፡ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት ከፊልም ሰሪው የበለጠ ሆኗል ዕይታው፡፡ ማን ምን እንደሆነ በሚገርም መልኩ ነው አስተያየት የሚሰጥህና ስራዎችህን የሚያርምህ፡፡

**ግዮን፡- ፊልምሽ በብሔራዊ ቴአትር ሲመረቅ የነበረው የሕዝብ አስተያየት ምን ይመስላል? ባለቤትሽ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ በሰዓቱ ባለመኖሩስ ምን ዓይነት ስሜት አደረብሽ?**

አምለሰት፡- በምረቃ ስነ ስርዓቱ ላይ ይገኛል ብዬ አልጠበቅሁም፡፡ ምክንያቱም ረዥም ጊዜ የሚወስድ ስራ በውጭ ሃገር እንዳለው ስለማውቅ፣ ብሔራዊ ቴአትር ለማስመረቅ የሚሰጠው ቀንም የተወሰነ ከመሆኑ አኳያ አለመገናኘቱ እንዳለ ሆኖ ከበፊትም ሁለታችንም አውቀነው ስለነበር የመጠበቁ ነገር አልነበረኝም፡፡ ግን ሁኔታዎች ተመቻችተው ቢኖር ምረቃውን የበለጠ ያደምቀው ነበር፡፡

በተመልካች ረገድ ምረቃ ሥነ - ሥርዓቱ ላይ ተገኝተው ፊልሙን ያዩ ሰዎች በጣም ጥሩ አስተያየት ነው የሠጡኝ፡፡ እኔ ያላየሁበትን መንገድ ተመልክተው አዳዲስና ያልጠበቅኋቸውን ቆንጆ አስተያየቶች አድርሰውኛል፡፡ ከጠበቅኹት በላይ ሰው ወዶታል፡፡

**ግዮን፡- "ምን አለሽ" እስካሁን ከሰራሻቸው ፊልሞች በምን ይለያል?**



አምለሰት፡- እኔ እስካሁን አምስት ፊልም ሠርቻለሁ፡፡ እነዛ ፊልሞች የካራክተር መመሳሰል አላቸው አብዛኞቹ፤ የበለጠ ደግሞ ከአምለሰት (ከእኔነቴ) ጋር ነው የሚገናኙት፡፡

ይህቺኛዋ ካራክተር ግን ሌላ ናት፡፡ ሰላማዊት ትባላለች፣ እኔ እንኳን አላውቃትም፡፡ ያቺን ካራክተር ከተገናኘኋት በኋላ ለመለያየት ራሱ በጣም ብዙ ጊዜ ፈጅቶብኛል፡፡ ለመገናኘት የፈጀብኝን ያህል ጊዜ፣ ከውስጤ ለማውጣት ብዙ ተቸግሬያሁ፡፡

ወጣ ያለችና የመርካቶ ልጅ ካራክተር ነች፡፡ በጣም ኮንፊደንስ አላት፣ በተጨማሪ የራሷ የሆነ አቋም አላት፣ በምንም መልኩ ፈፅሞ ከእኔ ጋራ የማትገናኝ ናት፡፡ እንደዛ መሆኗ ደስ ብሎኛል፣ ትንሽ ሁኔታዋ ወጣ ያለች በመሆኗ የፊልም ነገር እንዲሰማኝ አድርጎኛል ስሜቱ፡፡ እኔን ከሚመስሉ ከበፊቶቹ ስራዎቼ ወጣ እንድል ስላደረገችኝ ካራክተሯን ወድጄያታለሁ፡፡

**ግዮን፡- በፊልሙ ውስጥ ያለችውን የሰላማዊትን ገጸ ባህሪ ለመላበስና በተክለ አቋም እሷን ለመምሰል ያደረግሽው ብርቱ ጥረት የጤና እክል ፈጥሮብሽ እንደነበር ተሰምቷል፡፡ በብዙ መልኩ ፊልሙ ፈታኝ ነገሮችም አሉበት ይባላል፤ እስኪ እነዚህን ነገሮች ንገሪን?**

አምለሰት፡- የፊልሙ ፈታኝ ነገር ካራክተሯ የፊዚካል ለውጥ ያላት መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪ መርካቶ በየቀኑ ሄጄ፣ እዛ አካባቢ ያለውን ኑሮ ለመላመድና ካራክተሩን ለማጥናት ብዙ ጊዜ ፈጅቶብኛል፡፡ ከስምንት ወር በላይ ነው አካላዊ ለውጥ ለማምጣት ኤክሰርሳይስ ያደረግኹት፡፡ በምግብ መገደብም አለ፤ ብዙ ፈታኝ ነገሮች ነበረበት፡፡

የመታመሙ ችግር ነበር፤ ከላይ የጠቀስ ኳቸው ነገሮች ተደጋግመው ፊልሙን ፈታኝ አድርጎታል፡፡ በየቀኑ መርካቶ እየሄድክ መዋሉ በራሱ ከቦታ አንፃር በጣም ከባድ ነበረ፡፡ ያንን ሁሉ ክሩው (የፊልም አባላት) ይዘህ ከጠዋት ጀምሮ ጸሐይ ላይ መዋል ያስቸግራል፡፡ "ምን አለሽ ተራ" አካባቢ እንደመዋላችን ነገሮች ፈታኝ ነበሩ፤ ግን በዛ ሰፍራ ደስታንና ፍቅርን ስለነበር የምናገኘው የሆነ ሰዓት ላይ እየለመድኩት በጣም ደስተኛ ሆኜ ነው የጨረስኩት፡፡

**ግዮን፡- የታመምሽውን ያህል ዋጋ ከፍሏል ፊልሙ? ውጤታማ ሆኛለሁ ብለሽ ታምኚያለሽ?**

አምለሰት፡- ውጤት እንግዲህ ከራስህ ነው የሚጀምረው አይደል? እኔ በጣም ረክቼበት፣ ተደስቼበት፣ አለኝ የምለውን ጉልበትና ሀሳብ በሙሉ፣ እንዲሁም አለኝ የምለውን ገንዘብ በጠቅላላ ሳልሸሽግ፣ ሳልቆጥብ ፊልሙ ላይ አፍስሼበታለሁ፡፡

የእዛን ያህል ውጤት ደግሞ አይቼበታለሁ፤ ደስ የሚል፣ ቆንጆ ፊልም ነው የሰራሁት ብዬ አስባለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ሰው ነው አይቶ የሚፈርደው፡፡ ግን እኔ የወደድኩትን ነው ለሰው መስጠት ያለብኝ፣ የጎደለ ነገር ለሰው አላቀርብም፡፡ ፊልሙ የእኔን ልብ ሞልቶልኝ ለሰው አቅርቤያለሁ፡፡

**ግዮን፡- ከፊልሙ ወጣ እንበል፡፡ በበጎ አድራጎት ተግባርስ ያለሽ ተሳትፎ ምን ይመስላል?**

አምለሰት፡- በግሌ ደስ ብሎኝ መሳተፍ የምፈልግባቸው የበጎ አድራጎት ተግባራቶች አሉ፡፡ ለምሣሌ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ውስጥ የሚማሩ ሴቶች፤ ሞዴስ ወይም የንፅህና መጠበቂያ በመቸገራቸው ብቻ፣ በየወሩ ለአንድ ሳምንት ከት/ቤት እንዳይቀሩ በራሴ ተነሳሽነት ከመቶ እስከ ሁለት መቶ ለሚደርሱ ተማሪዎች፣ በየዓመቱ ለአንድ ዓመት የሚሆናቸውን የንህፅና መጠበቂያ ድጋፍ አደርጋለሁኝ፡፡

አሁን በቅርቡ ደግሞ ከሜሪጆይ አስር ልጆችን ለማሳደግ ተረክቤ እዛው ባሉበት የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ለማድረግ ተስማምቼ እሱንም እያደረግሁ ነው፡፡ መኖር ማለት ለሌላውም ሰው ነውና ያንን ዓይነት ነገር ከልጅነቴ ጀምሮ ሳደርገው የኖርኩት በመሆኑ፣ ለራሴ ደስታ እንዲሰጠኝ ብዬ እንጂ እንደ ማድረግ አልቆጥረውም፡፡ ሰጪ እግዚአብሔር ነው፣ ምክንያት እንድሆን ስላደረገኝ እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ የራሴን ሐላፊነት እወጣለሁ፤ ግዴታዬም ስለሆነ፡፡

**ግዮን፡- "አረንጓዴ መሬት" የሚል ዶክመንተሪ ፊልም ከዓመታት በፊት ሰርተሽ ነበር፤ በዛ መንገድ ምን ያህል ወደፊት ሄደሻል?**

አምለሰት፡- ቀደም ሲል በዋናነት ማድረግ የፈለግኹት፣ ሰዎች ዛፍ ዝም ብሎ መትከል ብቻ ሳይሆን ለምንድን ነው የሚተከለው? ባይተከልስ ምንድን የሚፈጠረው? የሚሉትን ነገሮች እኔ ሳውቅና ሲገባኝ ቀሪው ሕብረተሰብም እንዲያውቅ ይጠቅማል ብዬ ነው ዶክመንተሪውን የሠራሁት፡፡

አረንጓዴ ነገሮች በአካባቢያችን ከሌሉ አዕምሮን ከማስጨነቅ ጀምሮ ብዙ ጉዳቶች ይደርሱብናል፡፡ ይሄንን ነገር ለማስተካከል በዘርፉ አመርቂ ሥራ ያከናወኑ ባለሙያዎችን እየጠየቅሁኝ ነው የአምስት ደቂቃ አጭር ዶክመንተሪ የሰራሁት፡፡ እኔ ማድረግ የምችለው፣ የፊልም ባለሙያ በመሆኔ ሌላውን ሰው ሊያነሳሳና ሊያሳውቅ የሚችል ነገር መስራት ብቻ ነው፡፡

*ቀሪውን በገጽ 27 ይመልከቱ*

# ወጣት

## “የለውጥ ምክንያት /የለውጥ እንቅፋት”

## (ቄሮ፣ ፋኖ፣ ኤጀቶ ፣ሄጎ፣ ዘርማ፣ ዬላጋ፣ ጉርማሾ...)

መላክ ቢ.

ደራሲ ስብሃት ገብረእግዚአብሄር መቼቱን ማርሴይ ፈረንሳይ ውስጥ ባደረገውና “ትኩሳት” የሚል ርዕስ በሰጠው መጽሃፉ ወጣት መሆንን ሲገልጸው “ጥሩ ነው ወጣት መሆን” ብሎ ይጀምራል።

“...ጥሩ ነው ወጣት መሆን። ገንዘብ ባይኖርህም ጤና ይኖርሃል። መልክ ባይኖርህም አንጎል ይኖርሃል። ዕውቀት ባይኖርህም ጉራ ይኖርሃል። ደስታ ባይኖርህም ንዴት ይኖርሃል። መጨቆን ቢበዛብህ ሪቮሉሽን (አብዮት) ታስነሳለህ። መኖር ቢያስጠላህ ወይም ቢያቅትህ ራስህን ትገድላለህ። ሰው ባያውቀውም ቅሉ ታሪክ ይኖርሃል። ወጣት ነህና...”

ስብሃት እንዳለው ወጣት ለአብዮት ቅርብ ነው። አብዮት ማለት ለውጥ ማለት ሲሆን ደግሞ ወጣትና አብዮት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ሆነው ይቀርባሉ። “ከብዙዎቹ የዓለም ሃገራት አብዮቶች ጀርባ የአብዮቱ ጠንሳሽ፣ ቀስቃሽ፣ አቀናባሪ እና መሪ በአብዛኛው ወጣት ሆኖ የሚገኘውም ወጣትነት በደልን የመሸከሚያ ጫንቃው ስስ፣ ለውጥ ፈላጊ ተፈጥሮው ደግሞ ጠንካራ በመሆኑ ነው” ይላሉ አንጋፋው ግብጻዊው የአልአህራም ጋዜጠኛ ዛይድ ሙስጠፋ።

በቅርብ ጊዜ የዓለማችን አብዮቶች ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስም ያለውንና ብዙዎቹን በብረት መዳፍ ስር የኖሩ የመካከለኛው ምስራቅ አረብ ሃገራት መንግስታት እንዳልነበሩ ያደረጋቸውን “የጸደይ አብዮት” ያስነሳው ቱኒዚያዊው ታሪቅ አልጠይብ ሞሃመድ ቡአዚዚ የተባለ የ26 ዓመት የጎዳና ነጋዴ ወጣት ነው። ስብሃት በመጽሃፉ “...መጨቆን ቢበዛብህ ሪቮሉሽን (አብዮት) ታስነሳለህ።መኖር ቢያስጠላህ ወይም ቢያቅትህ ራስህን ትገድላለህ” እንዳለው ሆነና ጭቆና የጠላው ቡአዚዝ ዴሴምበር 17 ቀን 2010 ራሱን በአደባባይ አቃጥሎ ገደለ። በዚያ የተነሳ የሃገሪቱን መንግስት የናጠና ከስልጣን ያስወገደው የቱኒዚያ አብዮት ተቀሰቀሰ። በዚያ መነሻነት ብዙ የአፍሪካ እና የመካከለኛው ምስራቅ ዐረብ ሃገራት አንዳንዶች የአረብ ጸደይ (Arab spring) ብዙዎች ደግሞ የጸደይ አበባ አብዮት (jasmine revolution) ብለው በሚጠሩት አብዮት ተናጡ። እንደግብጽና ቱኒዚያ ያሉ ሃገራት መንግስታቸው መርጋት ተስኖት ወደቀ። አምባገነኖቹ መሪዎችም በእስር ቤት ፍርግርግ ብረቶች ኋላ ዋሉ። እንደየመን እና ሊቢያ ያሉ ሃገራት ደግሞ በዚያ ጦስ በተመዘዘ ቀውስ ዛሬም ድረስ ላላባራ ቀውስ ተዳረጉ። ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ የአፍሪካ፣ የመካከለኛው ምስራቅ እና የሩቅ ምስራቅ ሃገራት እንደሱናሚ እያስገመገመ የገረመማቸውን የጸደይ አብዮት ወደሃገራቸው ላለማስገባት ሲዋትቱና ሲባንኑ ዓመታትን አሳልፈዋል። ቻይና እንኳን ስለዚህ አብዮት ወጣቶቿ እውቀት እንዳይኖራቸውና “ልምድ እንዳይቀስሙ” ብላ ጉግል jasmine የሚለውን ቃል ለሚያስገቡለት ቻይናውያን ደንበኞቹ ምንም አይነት መረጃ እንዳይሰጥ ይህንን ቃል ከመዝገበ ቃላቱ እንዲሰርዝ አድርጋው ቆይታለች። ከዓመት ላላነሰ ጊዜ የተካሄደው የግብጹ ተሃሪር አደባባይ ሰላማዊ ተቃውሞ በታሪክ የማይዘነጋ የወጣቶች አብዮት መገለጫ ሆኖም ቆይቷል። የጸደይ አብዮት ካበቃ ከብዙ ዓመት በኋላ ሱዳንን የናጣት እና የረጅም ዘመን ፕሬዚዳንቷን ኦማር ሃሰን አህመድ አልበሽርን ከስልጣን ያወረዳቸው በመሰረታዊ መነሻው የሃገሪቱ ወጣቶች ንቅናቄ ነው።

## ኢትዮጵያ

### “ወጣት በ66”

በሃገራችን ኢትዮጵያ ወጣቶች ያቀነቀኑት ቀዳሚ አብዮት የ1966ቱ በአፄ ሃይለስላሴ ዘውድ ላይ የተነሳው የተማሪዎች ተቃውሞ ነው። የዚያን ዘመን የተማሪዎች ተቃውሞ በመላው ሃገሪቱ አብዮት አቀጣጥሎ “የመኳንንት አገዛዝ ከእንግዲህ አከተመ” እስከተባለበት 1967 ዓ.ም ድረስ ተጉዟል። አብዮቱን ደርግ ጠልፎት ንጉሱን ከስልጣን አውርዶ ራሱን በመንበሩ እስኪሰይም ድረስ የተቃውሞው ፊት መሪዎች ወጣቶቹ ነበሩ።

...ስብሃት በመጽሃፉ “... መጨቆን ቢበዛብህ ሪቮሉሽን (አብዮት) ታስነሳለህ፤ መኖር ቢያስጠላህ ወይም ቢያቅትህ ራስህን ትገድላለህ” እንዳለው ሆነና ጭቆና የጠላው ቡአዚዝ ዴሴምበር 17 ቀን 2010 ራሱን በአደባባይ አቃጥሎ ገደለ...

የዘመኑ ወጣቶች ትግል ንጉስ አውርዶ ወታደር የመተካት አላማ አልነበረውምና በጊዜያዊ አስተዳደር ስም ስልጣን ላይ ቂብ ያለውን ደርግን ወደሲቪል መንግስት ለመቀየር መስዋዕትነትን የጠየቀ ትግል አድርገዋል። አልሳካ ሲልም በአብዛኛው በሃገር ፍቅር ስሜት እና በዘመኑ ማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተአለም የተጠመቁ እንደነ ኢህአፓ አይነት በወጣት የተሞሉ ፓርቲዎች ተመስርተው ከሰላማዊ እስከ ትጥቅ የደረሰ ትግል አድርገዋል። በዚህ ሳቢያም ደርግ በኢትዮጵያ ታሪክ ቀድሞም ያልነበረ እና ዳግምም ሊከሰት የሚችል የማይመስል ከባድ እልቂት ፈጸመ። የዚህ እልቂት ሰለባዎች ደግሞ የ “መሬት ላራሹ”ን መፈክር ይዘው ንጉሱን ከስልጣን ያወረዱት እና በስማቸው የተጠቀመውን ደርግን ለስልጣን አጋጣሚ ያበቁት ወጣቶች ናቸው።

ደርግ በቀይሽብር ዘመቻ የዘመኑን ወጣቶች አንገ ቢሰብረውም አሁንም ነፍጥ አንግተው ሊታገሉት አሲምባ በረሃ የወረዱትና አስቀድመውም ደደቢት በረሃ የገቡት ሁሉ ወጣቶች ነበሩ። እነዚያ የዚያ ዘመን ወጣቶች ናቸው ከ17 ዓመታት ትግል በኋላ በኢትዮጵያ ስልጣን ለመያዝና መንግስት ለመመስረት የበቁት።

### “ወጣት በ97”

ደርግ የኢትዮጵያን ወጣት አከርካሪ መትቶ በመላው ሃገሪቱ የፍርሃት ድባብ አንግሶ መግዛት የቻለው ለ17 ዓመታት ብቻ ነው። በሌላ ባለነፍጥ ከተሰቀለበት ስልጣን ላይ እስኪወርድ ድረስ በመላው ኢትዮጵያ የሰላማዊ ተቃውሞን ቀዳዳ ሁሉ ደፍኖ ኖሯል። ደርግን አውርዶ ራሱን ለስልጣን ያበቃው ኢህአዴግ ሲጀምር የ66ቱ ወጣት በኢትዮጵያ እንዲኖር ይመኘው የነበረውን ዓይነት ዴሞክራሲ ለማስፈን መጣሁ ብሎ ተፍ ተፍ ያለው ለጥቂት አመታት ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ ግን ራሱን ወደለየለት አምባገነንነት መዶል ሲጀምር አሁንም ተቃውሞ የቀሰቀሱት ወጣቶች ናቸው።

በኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን የወጣቱ ተቃውሞ በርካታ ጊዜ ብልጭ ድርግም ሲል ቢቆይም በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ▶

ጠንክሮ የታየውና በታሪክም የማይረሳ ስፍራ የያዘው የወጣቶች ተቃውሞ የተቀሰቀሰው በ1997 ዓ.ም ነበር። በዚህ ዘመን ኢህአዴግ በመላው ሃገሪቱ ያካሄደው ምርጫ ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜም በሰላማዊ መንገድ ስልጣን እንዲያስረክብ የሚያስገድደው ጊዜ መጣበት። ህዝብ በካርዱ ስልጣንን ከርሱ እንደወሰደበት ነገረው። ኢህአዴግ በምርጫ ተሸነፈ። ነገር ግን አስቀድሞም የአገዛዝ ዘመንን ለማርዘም እንጂ በባህሪው ዴሞክራሲን ኮሮጆ ውስጥ ከትቶ አፍኖ የኖረው ኢህአዴግ የምርጫውን ውጤት አልቀበል አለ። ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ምሽት ገና የምርጫ ጣቢያዎች ሳይዘጉ በፊት አስቀድሞ ምርጫውን ማሸነፉን አወጀ። ይህ የህዝብ ድምጽ መቀማት ጉዳይ አስቀድሞ ያስቆጣው ወጣቱን ነው። በመላው ሃገሪቱ ከባድ ተቃውሞ ተቀሰቀሰ። ኢህአዴግ እውነተኛ ማንነቱን ያሳየበትን ካባ ገልጦ መጣ። የደርግ ታናሽ ወንድም እንደሆነም አስመሰከረ። ለተቃውሞ በወጡ ወጣቶች ላይ ጥይት አዘነበ። ገደለ። አሰረ። ብዙዎችን በሽብር ወንጀል፣ ብዙዎችን ህገመንግስቱን በሃይል በመናድ ወንጀል፣ ብዙዎችን በአደገኛ ቦዘኔነት ወንጀል፣ ብዙዎችን በፈለገው እና በተለያየ ጊዜ በሚለዋውጠው የወንጀል ስም ከስሶ በየእስር ቤቱ አጎረ። ከዚያን ዘመን ጀምሮ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከኢህአዴግ ጋር ሆድና ጀርባ ሆነ።

## "ወጣት በ2010"

እነሆ በብረት ሃይል ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ቀጥቅጦ ለመግዛት አልሞ የኖረው ኢህአዴግ ከደርግ 10 ዓመት የበለጠ ጊዜ ስልጣን ላይ ቆይቶ የበረከተበትን ህዝባዊ ተቃውሞ ለመመከት ሙከራ አደረገ። በተለይም ህወሃትን በጽኑ ይቃወም የነበረው ኢትዮጵያዊ ወጣት በመላው ኢትዮጵያ የፖለቲካ ለውጥ እንዲመጣ መስዋዕትነትን ከፈለ። የኦሮሚያ እና የአማራ ወጣቶች ለዚህ ህዝባዊ ተጋድሎ መሰረቶች ነበሩ ቢባል ማጋነን አይሆንም። ኢህአዴግ ጥቂት ቢንገታገትም በ2010 ዓ.ም በወጣቶች ተቃውሞ መበርታት ሳቢያ ከውስጡም ተሰንጥቆ ለየለትና ራሱን በአዲስ መልክ ለውጦ መጣ። እነሆ በኢትዮጵያ ለውጥ ወይም ሽግግር ለሚባለው ጊዜ መቅረብ እና እውን መሆን እርሾው በየክልሉ የተካሄደው የወጣቶች ንቅናቄ ሆነ።

በጊዜው ይህ ወጣት የጥይት አረር ሲሳይ ሆኖ፣ በየእስር ቤቱ ታጉሮ እና ዳግም የነጻነት አየር በማይተነፍስበት የሽብር አዋጅ ተከስሶ ኑሮው ወህኒ ሲሆን ለውጥ መምጣቱ ግድ ሆነ። ብዙዎች "ወጣቱ ለለውጡ ምክንያት ሆነ" አሉ። ጥቂት ቆይተውም ይኸው የፈረደበት ወጣት ንቅል ብሎ ወጥቶ የጨፈረለትን አዲሱን የለውጥ አመራር እና አስተዳደር መተቸትና መገዳደር ሲጀምር ሲያዩ ደግሞ "ወጣቱ ለለውጡ እንቅፋት ሆነ" አሉ። እነሆ በአሁኑ ዘመን ወጣቱ ለውጥ አምጪም ለውጥ አደናቃፊም ተብሎ በሁለት ጽንፍ ስር የተፈረጀበት ጊዜ ላይ ነን።

ከ2010 ዓ.ም ቀደም ብሎ በነበሩት አንድ ሁለት አመታት በየቦታው ይካሄድ የነበረው የወጣቱ ትግል ዋነኛ መነሻ እንደቀድሞው በኢትዮጵያ ሳይሆን በብሔር መብት መከበር ላይ ያነጣጠረ ነበር። ተሸናፊው የህወሃት መንግስት በዘመኑ ኢትዮጵያን ለግጭት እና ለመለያየት ክፍት ያደረጋትን መዋቅር ሰርቶ የሄደ በመሆኑ በራሱ ዘመን የፈጠራቸው ወጣቶችም ያንኑ የተሰመረውን መስመር ተከትለው ተቃውሞውን አፋፋሙት። ሁሉም ወጣት በብሔር ተደራጀ። ቀዳሚ አጀንዳውም ኢትዮጵያ መሆኗ ቀርቶ ብሔር ሆነ። የብሔር መብት ተከበረባት በተባለችው ኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር መብት አስከባሪ ኢ-መደበኛ ንቅናቄዎች ተፈጠሩ። የህወሓትን አስተዳደር የተቃወሙ የገዛ እህት ድርጅቶቹ በሚያስተዳድሯቸው ክልሎች ውስጥ የወጣት ንቅናቄዎች ተፈጠሩ። ዛሬም ድረስ የተለያዩ የፖለቲካ ጥያቄዎቻቸውን ከማቅረብ ያልቦዘኑት ወጣቶች በየጊዜው በሚያስነሷቸው አብዮቶች፣ ተቃውሞዎች እና ራሳቸው በሚወስዷቸው ግብታዊ እርምጃዎች ሳቢያ ከለውጡ አስተዳደር ጋር አይንና ናጫ እየሆኑ ነው።

እስኪ ያልተቋረጠ የብሔር ትግል እያደረጉ የሚገኙትን የወጣት ቡድኖች እና እነዚህን ቡድኖች እንደ ኢ-መደበኛ መብት አስከባሪ ሃይል እያየ ዝም የሚላቸውን የየክልሉን ፓርቲ ግንኙነት እንዳስስ።

## "ቄሮ ኦሮሞ"

በኢትዮጵያ በህዝብ ብዛትም ይሁን በቆዳ ስፋት ቀዳሚ የሆነው ኦሮሚያ ለዘመናት የሃብት ብዝበዛ እና የአስተዳደር በደል እንዲሁም የከፋ ጫና ሰለባ ሆኖ ቆይቷል። በጊዜው በስልጣን ላይ የነበረው አመራር ሳይቀር ኦሮሞን እንደኦነግ እያሰበ እና "እዩት የሚያደርገውን" ብሎ እያሳየ ወደስልጣን መንበር እንዳይጠጋ በሩቁ ይከልለውም ነበር። ይህ መረገጥ እና የኦሮሞ ብሔር መረሳት ያንገበገበው ወጣት ቄሮ በሚል ስም ተደራጅቶ (ጀዋር መሃመድ 'ያደራጀሁት እኔ ነኝ' ይላል) በመላው ኦሮሚያ ከባድ ህዝባዊ ተጋድሎ ማድረግ ጀመረ።

"...ጥሩ ነው ወጣት መሆን። ገንዘብ ባይኖርህም ጤና ይኖርሃል። መልክ ባይኖርህም አንጎል ይኖርሃል። ዕውቀት ባይኖርህም ጉራ ይኖርሃል፤ ደስታ ባይኖርህም ንዴት ይኖርሃል፤ መጨቆን ቢበዛብህ ሪቮሉሽን (አብዮት) ታስነሳለህ፤ መኖር ቢያስጠላህ ወይም ቢያቅትህ ራስህን ትገድላለህ፤ ሰው ባያውቀውም ቅሉ ታሪክ ይኖርሃል፤ ወጣት ነህና..."

ቄሮ የመላው ኦሮሞ ወጣቶች ድምጽ ሆነ። በጊዜው የነበረው የኦሮሞ ብሔር የስልጣን ውክልና ማነስ እና ሃገር የመምራት ስፍራ በኮታ እንኳን እንዳይደርሰው መደረጉ ኦሮሞ በሃገሪቱ ካለኝ ሰፊ የቆዳ ስፋት እና የህዝብ ብዛት አንጻር በተገቢ መልኩ ለስልጣን አልበቃሁም ብሎ እንዲነሳ አደረገው። በዚህም መላው ኦሮሚያን በተደራጀ እና በእቅድ በሚመራ ሁኔታ በታላቅ ህዝባዊ ተቃውሞ አጥለቀለቃት። በመላው ኦሮሚያ በተደራጀ እዝ እየተመራ ተቃውሞውን በኢሬቻ በዓል ላይ ሁሉ ማካሄድ ጀመረ። አስቸኳይ ጊዜ ቢታወጅም፣ ቢተኮስም፣ ቢገደልም ቄሮ የኦሮሞን መብት ለማስከበር ነውና ዋና አላማው የመጣውን ሁሉ ለመቋቋም ደረቱን ሰጠ። ኢህአዴግ በኦሮሚያ የሆነው ነገር የማይቋቋመው መሆኑን ሲያውቅ ወደሌሎች አቅጣጫዎች ለመዞር ሙከራ ቢያደርግም ሁሉም ቦታ ተመሳሳይ ሁኔታ ስለገጠመው ወደውስጡ መመልከት ግዴታው ሆነ።

የህወሃት አስተዳደር ከስልጣን ተወግዶ እንደአብዛኞቹ ፍላጎትም ዶክተር ዐቢይ ስልጣን ይዘው ኢህአዴግ አዲስ ፓርቲ ሆኖ ወደህዝቡ መጣ። ኦሮሞ ወደስልጣን መምጣቱ፣ በተለይም ከለውጡ መሪዎች ቀዳሚው ለማ እና ዐቢይ መሆናቸው ግን ለቄሮ እምብዛም ያስደሰተው አይመስልም። በመላው ሃገሪቱ ለዶክተር ዐቢይ ድጋፍ ሰልፍ ሲደረግ በኦሮሚያ ግን በተጠበቀው መልኩ አልተካሄደም። መንገድ ሲዘጋና ፈተና ሲያሰርቅ የነበረው ቄሮ በስርዓቱ ላይ ጫና አምጥቶ ከኦሮሞ ህዝብ የወጡ ጓዶች ስልጣን ይዘው እንኳን ቄሮ በአብዛኛው በሃገሪቱ በመጣው ለውጥ ከስደት ወደሃገር ቤት የገባውን ኦነግን መደገፍ የበለጠበት መስሎ ነበር። በተለይም ኦነግ ከመንግስት ጋር የገባውን ቃል አላከበረም በሚል ጥርስ ሲናከስ እና ብሎም ግጭት ውስጥ ገብቶ አሁን ድረስ በጦር መሳሪያ ሲታኮስ ቄሮ ድጋፉ ከፓርቲ ለኦነግ፣ ከሃገር ደግሞ ለኦሮሚያ ብቻ ሆኖ ተቀምጧል። በአንዳንድ ወቅትም በኦሮሞ ክልል የሚኖሩ የሌላ ብሄር ተወላጆችን በሃይል በማፈናቀል፣ ከባድ የሰብዓዊ መበት ጥሰትን በማድረግ፣ ግለሰቦችን ቤትና ንብረት በመዝረፍ እና በማቃጠል እንዲሁም እስከመግደል እና ዘቅዝቆ እስከመስቀል የደረሰ ተግባር የሚፈጽሙ ወጣቶችንም ይዞ የሚጓዝ መሆኑ ብዙዎች ከለውጥ ምክንያትነት ይልቅ በለውጥ እንቅፋትነት እንዲያዩት አድርጓቸዋል።

ያም ሆኖ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መከፈት ወይም ለውጥ እንዲመጣ እና የተከለከሉ መብቶች እንዲፈቀዱ ከዚያም አልፎ የኦሮሞ ብሄር መብት እንዲከበር አጥብቆ የታገለውና አሁንም በሙሉ ቁመናው እየተንቀሳቀሰ ያለው ይኸው የወጣቶች ቡድን ቄሮ ነው። ለዚህም ነው ለለውጥ ምክንያትም ሆኖ ሳለ በሌላ በኩል ለኦነግ ድጋፍ በመስጠት የዶክተር ዐቢይን አስተዳደር አጣብቂኝ ውስጥ በመክተቱ የለውጡ እንቅፋትም ሆኗል ተብሎ የሚተቸው። በየትኛውም መነጽር ግን ቄሮ የቆመው ለኦሮሞ ህዝብ እንጂ ለዶክተር ዐቢይ አለመሆኑን በብዙ መንገድ ማሳየት በመቻሉ ብዙዎች አድናቆታቸውን የሚቸሩት የወጣቶች ንቅናቄ ነው።

## “ፋኖ አማራ”

በኢትዮጵያ የትጥቅ ትግል ታሪክ ውስጥ ለጀግና ታጋዮች የሚሰጠው ፋኖ የሚለው ስም ወደፊት የመጣው ከ1966ቱ አብዮት እና ያንን ተከትሎ ከመጣው የተቃውሞ ፖለቲካ ንቅናቄ ጋር ተያይዞ ነው። በዘመኑ “ፋኖ ተሰማራ፣ እንደሆቺ ሚኒ እንደ ቼ ጉቬራ” የሚለው የትግል መዝሙር ብዙ ወጣቶችን በወኔ ከነበረው ስርዓት ጋር እንዲታገሉ ያደረጋቸው ነበር። ፋኖ ዛሬ በአማራ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል ለማስቆም በወጣቶች የሚቀነቀን ብሔርተኛ ቡድን ነው።

ልክ እንደኦሮሞው ቄሮ ሁሉ አማራውም የኢህአዴግን የሃይል አገዛዝ ተቃውሞ በመላው አማራ ከበድ ያለ ንቅናቄ ያደርግ የነበረ የወጣት ሃይል ነው። በተለይም በጎንደር የተጀመረው የፋኖ ተቃውሞ ወደባህር ዳር ከዚያም ወደ ደሴ ሲሸጋገር በዚያው ልክ ስርዓቱ ይህንን የወጣት ተቃውሞ ለማብረድ እስከግድያ የደረሱ ከባድ እርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል። ፋኖ በሚያጥለቀልቅ ተቃውሞ ቀድሞ የነበረውን ህወሃት /ኢህአዴግን ሲቃወም እና የአማራ ብሔርተኝነትን እያራመደ የተጨቋኝነት ትርክት ውስጥ ሲገባ በዚያው መጠን ቁጭት ያንገበገባቸው የአማራ ልጆች ስርዓቱን በትጥቅ ጭምር ታግለውታል።

ስርዓቱ በአዲስ መልክ ብቅ እንዲል ያደረገው በኦሮማራ የተቀነቀነው የፖለቲካ ጥምረት ውጤት በመሆኑ ፋኖም እንደትግል አቀጣጣይ የነበረው ድርሻ ከፍ ያለ ነው። በተደጋጋሚ ጊዜ መላው አማራን ያጥለቀለቀ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ፣ ኢህአዴግን ከተቃወመ ማናቸውም አካል ጋር ጭምር በመሰለፍ ይህ ስርዓት ተወግዶ አማራም እንደብሔር የራሱን መብት ማስከበር የሚችልበትን እድል ለመፍጠር የወጣቶቹ ቡድን ብዙ አስተዋጽኦ ነበረው። ብአዴን ኋላ አዴፓ እስከመባል ያደረሰው የአማራነት ካባ ድጋፉ የወጣቱ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። ፋኖ ዛሬ ተመስርቶ በመላው አማራ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘውንና የአማራነት ስነልቦናን እና ብሔርተኝነትን አጠንክሮ የሚራመደውን አብንን የወለደ የወጣቶች ንቅናቄም እንደሆነ ይነገራል። በብዙዎች ዘንድ ለዛሬው የፖለቲካ ለውጥ ግዙፉ ድርሻ ውስጥ የፋኖ እጅ ሰፊ እንደሆነ የሚታመንበትን ያህል ይህንን የወጣቶች እንቅስቃሴም አዲሱን ለውጥ ለመቃወም የሚያኮበኩብ ሃይል አድርጎ የሚስልም አልጠፋም። ዛሬ ዛሬ ግን ፋኖ ብዙም ድምጹ የማይሰማ ቡድን ሆኗል። ምናልባትም አብን የወጣቶቹን ንቅናቄ ተክቶ ፊት ስለሚቀርብ ይሆን ?

## “ሄጎ ሶማሌ”

የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት የነበረው አብዲ ኢሌ ያቋቋመው የወጣቶች ቡድን ነው። ይህ ቡድን መሰረታዊ አወቃቀሩ ለሶማሌ ህዝብ መታገል ሳይሆን የአብዲ ኢሌን ለውጥ የማደናቀፍ ዋነኛ አጀንዳ ማስፈጸም ብቻ ነው። አብዲ ኢሌ ሶማሌን የመገንጠል ማስፈራሪያውን ይዞ ሃገር ሲያምስ ሄጎ ቀዳሚ ተግባሩ በሶማሌ የሚኖሩ ኦሮሞዎችን ማሳደድ ነበር። በአሰቃቂ ሁኔታ መታወቂያቸውን እያየ ብቻ ከሶማሌ ክልል ኦሮሞዎችን አጸዳቸው። ከዚያ በኋላም አብዲ ኢሌ በቀቢጸ ተስፋ ላይ በነበረበት ወቅት የመንግስት ሃይሎች ከብበውታል ሲባል የተንቀሳቀሰው ጅግጅጋን እና ድሬዳዋን አምሷል። ያ ብቻም ሳይሆን በጅግጅጋ የሚኖሩ የሌላ ብሔር ተወላጆችን ገድሏል፣ በከባድ ሁኔታም ዘርፏል፣ ደፍሯል እንዲሁም አሰቃቂ ጉዳት አድርሷል። ሄጎ አብያተ ክርስቲያናትን ሲያቃጥል እና እንደሩዋንዳ በዘር ፍጅት ጥፋት ላይ ሲሰማራ አብዲ ኢሌ ታሰረ። ከዚያ በኋላ የክልሉ ልዩ ሃይል ሲበተን ሄጎም በዚያው እንደጉም በንኖ ጠፋ። እንደፋኖ እና ቄሮ ለለውጥ የተደራጁ የወጣት ንቅናቄዎች ባሉባት ሃገር ሄጎ ለጥፋት እና ለዘር ማጽዳት ወንጀል ሲባል ብቻ ተደራጀ። የለውጥ እንቅፋት ነበር።

## ‘ኤጀቶ ሲዳማ’

በቅርቡ ከተቋቋሙ እና ስማቸው በደቡብ ክልል ከገነነ የወጣት ንቅናቄዎች አንዱ የሲዳማን ክልል የመሆን ጥያቄ ይዞ ተነሳው ኤጀቶ አንዱ ነው። ኤጀቶ የሲዳማን ክልል መሆን ጥያቄ ሲያከረው ራሴ ባለቤት ነኝ ብሎ ቁጭ አለ። ክልልነቱን ከመንግስት መጠየቅ ብቻ ሳይሆን በክልሉ የሚኖሩ የወላይታ እና አማራ እንዲሁም ጉራጌ ብሔር ተወላጆች ላይም ተከታታይ ጥቃት ፈጸመ። ኤጀቶ በተለይ በወላይታ ተወላጆች ላይ ያደረሰው ዘግናኝ ጉዳት እና የዘር ማጽዳት ተግባር የቡድኑን ‘ለውጥ አደናቃፊነት’ በጉልህ የሚያሳይ ነው። ኤጀቶ በሃገሪቱ ሊመጣ የሚገባውን ሁሉም ብሔር በሃገሩ በሰላም የመኖር እና ሰርቶ የማፍራት ለውጥ በብርቱ ጎድቶታል። በሁለት ተከታታይ ጊዜ በፈጸመው ዘግናኝ ድርጊትም መሪው ታስሯል። ኤጀቶ ደኢህዴንን ከሃዋሳ በማባረር ባንዲራውን አወርዶ በማቃጠል እና የራሱን በመስቀል አለቃ አድርጎ የኖረ ቡድን ነው። ሲዳማን ክልል የማድረግ እንቅስቃሴ ሌላ ብሔርን በማፈናቀል እና ዜጎችን በመግደል እንዲከወን የሚጥር ቡድን የትግል ሳይሆን የበቀል ቡድን ነውና በየትኛውም ስርዓት ውስጥ የሚበረታታ አይሆንም።

## “ዬላጋ ወላይታ”

ይህ የወጣቶች ቡድን በወላይታ ክልል የመሆን ጥያቄ ላይ በቅርብ ጊዜ የጎላውን ንቅናቄ በማድረግ ላይ ያለ ነው። ዬላጋ በወላይታ የረጅም ዘመን የሃገረ መንግስት ትርክት ውስጥ የብሔሩን ታላቅነት በማወጅ ከዚህ ቀደም የነበረው የክልልነት ደረጃ ተጨፍልቆ ዞን የሆነበትን ምክንያት በመቃወም በተለይም ወላይታ እንደብሔር በሲዳማ የደረሰበትን ከባድ ጥቃት በማውገዝ ብሔሩ በራሱ ላይ የሚተማመን እና የራሱን እድል በራሱ ለመወሰን የሚችል እንዲሆን ሰላማዊ በሆነ መልክ ንቅናቄ የሚያደርግ ቡድን ነው። ዬላጋ ደኢህዴንን መግለጫ ከመቃወም እና ክልል ለመሆን የቀረበውን ጥያቄ ከፍ አድርጎ ከመታገል ያለፈ በሌሎች ብሔሮች ላይ ለተፈጸመ ጥቃት እጁ አለበት የሚል ጥቁር ነጥብ አልታየበትም።

## ‘ካፋ ጉርማሾ’

ካፋ ከዘመነ ምኒሊክ በፊት የነበረውን የሃገረ መንግስትነት ታሪክ በማስመር ዛሬ ክልል የመሆን መብት ሲያንስበት እንጂ እንደማይበዛበት እየጠቀ ነው። በዚህ ጥያቄ ውስጥ የካፋ ጉርማሾ ወጣት ወሳኙ አንቀሳቃሽ ነው። እጅግ ሰላማዊ እና ጥያቄውን ለውጥ ከመደገፍ እና ከማስቀጠል ጋር አያይዞ የሚያቀርብ የወጣቶች ንቅናቄ መሆኑንም አስመስክሯል። በክልሉ ካሉ የሌላ ብሔር ተወላጆች ጋርም ምንም አይነት ግጭት ውስጥ ያልገባ መሆኑ አላማውን ለማሳካት ስሙን በመጥፎ የማግዘፍ ራዕይ እንደሌለው ማሳያ ነው።

## “ዘርማ ጉራጌ`

ስለዘርማ ከላይ ከተባለው ያለፈ ብዙ የሚባል ነገር የለም። ዘርማ በጉራጌ የክክልነት ጥያቄ ላይ መሪ አቀንቃኝ ነው። ጉራጌ ከቀቤና ጋር ባለው ያለመግባባት ግጭት ውስጥ ይገባል የሚል ስጋት ቢኖርም ፣ ከዚህ ቀደም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ወልቂጤ ሄደው ከገሰጹት በኋላ እርቅ አወርዷል። ከዚያ በኋላ የታየበት ችግር የለም። ነገር ግን አሁንም በሁለቱ ብሄሮች የክልልነት ጥያቄ ልዩነት ላይ ግጭት ሊቀሰቀስ እንደሚችል ማሳያዎች ቢኖሩም ጉዳዩ በቀደመው መንገድ በውይይት ያልቃል የሚል እምነትም አለ።

## ወጣት፣ የለውጥ ምክንያት ወይስ እንቅፋት?

ለውጥ ተብሎ በተለምዶ እየተጠራ ያለው በኢህአዴግ ውስጥ የተከሰተው የፖለቲካ መከፈት ቢሆንም ለዚህ ጽሁፍ ግን ለውጥ በኢትዮጵያ የኖረ የመንግስት አገዛዝ ልምድ ኢ ዴሞክራሲያዊነት ሰብዓዊ መብት ጥሰት እና ሙስና እንዲሁም ጠባብነት እና የብሔር ጥላቻ ተወግዶ አንድነት የሚመጣበት መንገድ ነው። በዚህ ስሌት ከላይ የጠቀስናቸውም ይሁኑ ሌሎች የወጣት አደረጃጀቶች እንደ የባህሪያቸው የብሔራቸውን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ የቆሙ ቢሆኑም በአንድ አጋጣሚ ብቅ ብሎ እንደጠፋው አይነት የኦሮማራ አይነት ግንኙነትም አንዱ ከሌላው ጋር ተሳስሮ የአንዲት ሃገር ምስረታ መሰረት የመሆን እድልም ይፈጥራል።

ለውጥ በወጣት የሚቀነቀን እና በወጣት ትግል የሚመጣ ቢሆንም መሪዎች ብዙውን መንገድ ወዳልታሰበ ስፍራ መምራታቸው አዲስ ነገር አይደለም። ያም ሆኖ በሃገሪቱ የሚመጣ ለውጥን በአንድ ሃሳብ ሆኖ ማቀናጀት የሚችለው ለውጥ የሚመራው አካል ነውና ከባዱ ሃላፊነት ያለው እሱው ላይ ነው። አብዲ ኢሌ እንዳደራጃቸው አይነት የጥፋት ቡድን ሳይሆን ጭቆናንና አፈናን በመቃወም የሚደራጁ የለውጥ ሃይሎች የተሻለ ቀን እንዲመጣ የሚሰሩ እንጂ የከፋ ቀን እንዲመጣ የሚጥሩ አይሆኑም። በሂደት ግን ጠባብ አስተሳሰብ፣ በብሔር የታጠረ ምልከታ እና አርቆ አለማሰብ፤ እንዲሁም በፖለቲከኞች መጠለፍ ውስጥ ሲገባ ወጣቶች በነሲብ በሚነዱበት ንቅናቄ ውስጥ ጥፋት እንደማይከሰት ማረጋገጫም የለም። የሆነው ሆኖ የወጣት ንቅናቄ በተፈጥሮው መነሻ ምክንያቱ የለውጥ ምክንያት እንጂ የለውጥ እንቅፋት እንዳልሆነ ግን ጅምሮቹ የሚመሰክሩት ነው። ማጠቃለያዎቹ ግን በጥሩ እጅ እስካልተያዙ እና መጠቀሚያ እስከሆኑ ድረስ ወደየትኛውም ጫፍ ለማምራት የሰፋ እድል አላቸው።

# የሆቴሎች ደረጃ በኢትዮጵያ!
# "ሆቴሎቻችን የት ላይ ናቸው?"

በዝግጅት ክፍሉ

በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሆቴል ኢንዱስትሪ የ113 ዓመት ዕድሜ ያለው ነው፡፡ ከነሙሉ ክብርና ሞገሱ መሐል ፒያሣ ላይ የቆመው እቴጌ ጣይቱ ሆቴልም የመጀመሪያውና ፈር ቀዳጁ ሆኖ በታሪክ ድርሣን ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

ግርማዊት እቴጌ ጣይቱ ብጡል የዘመኑን መኳንንትና ሹማምንት ለክብራቸው በማይመጥን ቦታ (ቤት) መገኘት አጢነው፣ ይህም በንጉሳዊ የአገር አስተዳደር መልክ ላይ አንዳች ጥቁር ጥላ እንደሚያሳርፍ በመረዳታቸው፤ ከዚህም አልፎ በዘመኑ በስራና በጉብኝት ምክንያት ወደ አገራችን የሚመጡ የውጭ አገራት ዜጎች በአገራቸው የለመዱትን ዓይነት ዘመናዊ የሆቴል አገልግሎት ለማግኘት የሚገጥማቸውን ችግር በማየታቸው፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ይህ ሁኔታ በአገራችን መልካም ገፅታ ላይ የሚኖረውን አፍራሽ ተፅዕኖ በመረዳታቸው ነበር በ1898 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ዘመናዊ ሆቴል እውን ያደረጉት፡፡

እቴጌ ጣይቱ ከባለቤታቸው ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ጋር ተማክረው ከውጭ ሀገር የመጡ የዘርፉ ባለሙያዎችን በአማካሪነት ቀጥረው እቴጌ ጣይቱ ሆቴልን ሲከፍቱ ሆቴሉ የት ጋር መሆን አለበት ከሚለው መሠረታዊ መነሻ ሀሳብ ጀምሮ አገልግሎቱ በምን መልክ ዘመናዊና ምቹ መሆን አለበት እስከሚለው ድረስ በብዙ እንደተጨነቁበት በበርካታ የታሪክ ድርሳናት ሰፍሮ ይገኛል፡፡ በጊዜው አገራችንን የጎበኙና በስራው ተሳታፊ የነበሩ የውጭ አገራት ተወላጆችም በየማስታወሻዎቻቸው ያሠፈሩት ምስክርት ዛሬም የታሪክ ማጣቀሻ ሆኖ በክብር ይነበባል፡፡

በአስተሳሰብ ረገድ ዘመናቸውን የቀደሙ እንደነበሩ ተደጋግሞ የተነገረላቸው አፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ ዘመናዊ የሆቴል አገልግሎትን በዚያ (ኋላቀር?) ዘመን ሲያስጀምሩ እጅግ ብዙ ፈተናዎች ገጥመዋቸው እንደነበር ይነገራል፡፡ ከሁሉም በላይ የጊዜው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ስለዘመናዊ የሆቴል አገልግሎት የነበረው ግንዛቤ አናሳ መሆኑ፣ በተለይም ክብሩን እንዲያስጠብቅ የታሰበለት ሹማምንትና መኳንንት ስለ ሆቴል አገልግሎት ያለው ግምት የተጠበቀውን ያክል ሆኖ አለመገኘቱ ንጉሡና ንግስቲቱን ከባድ ፈተና ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል፡፡

ይሁንና ሁሌም ጥበብና ማስተዋል ተለይቷቸው የማያውቀው ጥንዶቹ "በመላ በዘዴ" እያደረጉ ከመኳንንትና ሹማምንቱ አልፎ የተቀረው ሰፊ የሀገሪቱ ዜጋም ስለ ዘመናዊ ሆቴል አገልግሎት እንዲያውቅና የሆቴል ተጠቃሚ እንዲሆን በማስቻል ምንግዜም የማይረሳ ታላቅ አኩሪ ተግባርን በብቃት ለመወጣት ችለዋል፡፡ ይህ ስኬታቸውም ሀገራችን ዛሬ ለደረሰበችበት የሆቴል ኢንዱስትሪ ዕድገትና ታላቅ ኩራት




እንደመነሻ ሆኖ ዝንተ ዓለም በታሪክ ሲወሳና ሲወደስ ይኖራል፡፡

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሆቴል ሀብታም ናት፡፡ በአንዳንዶች ዕይታ ደግሞ እንደውም ሆቴል የተትረፈረፈባት ሀገር ተደርጋ እስከመቆጠር ደርሳለች፡፡ ከአዲስ አበባዎቹ ዘመናዊ ሆቴሎች ባሻገር በመላ ሀገሪቱ (በክልሎች) ያሉትን ሁሉ ቆጥሮ ለመጨረስ እስኪያቅት ድረስ ኢንዱስትሪው በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቷል፡፡

ባለፉት ጥቂት አመታት የተገነቡና አገልግሎት መስጠት የጀመሩ ሆቴሎች እጅግ በርካታ የመሆናቸውን ያክል በቀጣይ ጊዜ ሊከፈቱ ታስበው በግንባታ ላይ ያሉትም በቁጥር እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ ከህንፃ ዲዛይናቸው ጀምሮ እስከሚሰጡት አገልግሎት ድረስ አንዱ ከአንዱ የተለየ፣ ያማሩና ሀገርን የሚያኮሩ መሆናቸውም ሀገራችንን በብዙ መልኩ ተጠቃሚ አድርጓታል፡፡ በተለይም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጽ/ቤት መገኛ፣ የተመድ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና መ/ቤት መቀመጫና የሌሎች በርካታ አለም አቀፍ ተቋማት ዋና ቢሮ ሆና በማገልገል ላይ በምትገኘው መዲናችን አዲስ አበባ ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ዘመናዊ ሆቴሎች አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸው ለአገራችን ሁለተንተናዊ ተጠቃሚነት የላቀ ሚና እንዳላቸው ይታመናል፡፡ ለአመታት ቁጥራቸው ላይ አተኩረን መኖራችን ግን የጥራታቸውን ወይም የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃቸውን እንድንዘነጋው አድርጎን ቆይቷል፡፡ ይህ ደግሞ ሆቴሎቻችን ለአገር ከሚሰጡት ጥቅም ባልተናነሰ የሚኖራቸው ጉዳትም ከፍተኛ በመሆኑ በአገር ገፅታና በመልካም ኢትዮጵያዊ ማንነታችን ላይ የራሱን ጥላ ሲያሳርፍ ሊታይ ችሏል፡፡ ከዘመናዊ የሆቴልነት ስያሜያቸው ባሻገር ውስጣዊ አደረጃጀታቸውንና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራታቸውን መፈተሽ ላይ እንድናተኩርም ጊዜው በራሱ ግድ የሚልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

የአገራችንን ሆቴሎች የአገልግሎት አሰጣጥ የመፈተሽና የመገምገም ስልጣን ያለው የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት የጀመረው ከዓመታት በፊት ሲሆን፣ ከአገር ውስጥና የውጭ አገራት የሆቴል ባለሙያዎች ጋር በመሆንም በ2007 ዓ.ም የአዲስ አበባ ሆቴሎችን ፈትሾ የሚገባቸውን ደረጃ ሰጥቷል፡፡ በወቅቱ የደረጃ ምዘናና ፍተሻ የተደረገባቸው 250 ሆቴሎች አለም አቀፍ መስፈርቶችን መነሻ ያደረገ ደረጃ የተሰጣቸው ሲሆን ደረጃው ከ1 እስከ 5 ኮከብ ያለውን የጥራትና ብቃት ማረጋገጫ ለሆቴሎቹ የሰጠ ነበር፡፡ ከ250 ሆቴሎች መካከል የ5 ኮከብ ደረጃን ያገኙት 3 ብቻ (ሸራተን አዲስ፣ ኢሊሌ፣ ራዲሰን ብሉ) የመሆናቸው ጉዳይ ግን በወቅቱ በስፋት ሲያነጋግር የቆየ ነበር፡፡

ሚኒስትሩ ዘንድሮም ለሁለተኛ ጊዜ ባደረገው ግምገማና ምዘና ለ88 ሆቴሎች በአገር አቀፍ ደረጃ ከ1-4 ኮከብ ያለውን ደረጃ ሰጥቷል፡፡ በደረጃ ምዘናው ከተሳተፉ 159 የሀገራችን ሆቴሎች መካከል መስፈርቱን አሟልተውና ለደረጃ ምዘናው ብቁ ሆነው የተገኙት 88 ብቻ ሲሆኑ ከዚህም ውስጥ ለ83ቱ ብቻ ነው ከ1-4 የኮከብ ደረጃ የተሰጠው፡፡


በያዝነው ሣምንት መጀመሪያ ይፋ የሆነው የሆቴሎች ኮከብ ደረጃ ምደባ ዝርዝር መግለጫ እንደሚያሳየው ከሆነ ደግሞ ሀገራችን ዛሬም ባለ 5 ኮከብ ደረጃን የሚያሟሉ ሆቴሎችን በብዛት ለማፍራት የታደለች አይደለችም፡፡ ከአመታት በፊት በተካሄደው ምዘና ከ250 ሆቴሎ ውስጥ ባለ 5 ኮከብ ክብርን ያገኙት ሶስት ብቻ መሆናቸው ሲያስገርመን የቆየ ቢሆንም ዘንድሮ ይባስ ብሎ ለዚህ ክብር የበቃ አልተገኘም፡፡

የሆቴል አብዮት የፈነዳባት የምትመስለው ሀገራችን ባለ 5 ኮከብ ደረጃን ያሟሉ ሆቴሎችን በብዛት ለማግኘት አልታደለችም፡፡ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትሯ ዶ/ር ሂሩት ካሳው ደረጃው ይፋ በሆነበት ሥነ ሥርዓት እንዳሉት ይህን የሆቴሎች ደረጃ ለመስጠት የተፈለገው ሆቴሎቻችን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የመሆን አቅም ላይ የደረሱ መሆናቸውን ለማረጋገጥና ከአለምና ከአህጉር የሆቴሎች ይዘት ጋር በማነፃፀር የት ላይ መሆናችንን ለመረዳት ሲሆን፣ የተገኘው ውጤት ግን የሚያኮራ ሊሆን አልቻለም፡፡

41 የአገር ውስጥና የውጭ አገራት የሆቴል አገልግሎት ባለሙያዎች የተሳተፉበት የዘንድሮ የሆቴል ደረጃ ምደባ ሥራ በዋናነት ለመመዘኛ ግብዓትነት ያዋላቸው ንፅህናቸውን፣ ውበታቸውን፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል አደረጃጀታቸውን፣ በእሳትና በሌሎች አደጋዎች ጊዜ የሚያገለግል የደህንነት መጠበቂያ አማራጮቻቸውንና የመስተንግዶ ምቾታቸውን ሲሆን በእነዚህ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን በተከተሉ ፍተሻና ምዘናዎች አልፈው ባለ 4 ኮከብ ማዕረግን ለማግኘት የቻሉት 12 ሆቴሎች ብቻ ናቸው፡፡ የተቀሩት 12ቱ ባለ ሶስት፣ 13ቱ ባለ ሁለት፣ 27ቱ ባለ አንድ ኮከብ ደረጃ ነው ያገኙት፡፡ ይህ በርግጥ ብዙ አያኮራም፡፡ በሀገራችን የተገነቡና አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ ሆቴሎች ቁጥቻቸው እጅግ ብዙ ቢሆንም የጥራትና ምቾት ደረጃቸው ግን ደረት የሚያስነፋ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስፖርት

# የግብፅ አፍሪካ ዋንጫ



ከፍቅሩ ኪዳኔ

የአፍሪካ አገሮች የጠለቀ ጥናት ሳያደርጉ ልዩ ልዩ የስፖርት ውድድሮች እናዘጋጃለን በማለት ቃል ይገቡና ግዜው ሲደርስ ጉድ ይፈላል፡፡ ካሜሩን የአፍሪካ ዋንጫን አዘጋጃለሁ ብላ ሳይሳካላት ስለቀረ በግብፅ ተተክታለች፡፡ ኢትዮጵያም "ቻን" የተባለውን የአፍሪካ ዋንጫ አዘጋጃለሁ ብላ እንዲሁ በወሬ ግዜውን ካሳለፈች በኂላ፤ እውነተኛውን ምክንያት ከመግለፅ ፋንታ የፌደሬሽኑ ፕሬዝዳንት አገራችን ምርጫ ስለምታዘጋጅ ነው በማለት መቃገፐት ቀጠለ፡፡

በኢትዮጵያ ስፍራ ካሜሩን ተተካች፡፡ አሁን በቅርብ የተፈፀመውን የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ያዘጋጀችው ግብፅ በፀጥታ ችግር የተጎዳች መሆኑ በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው፡፡ በየስፍራው ቦምብ ማፈንዳት ቱሪስቶችንና ሰላማዊ ሕዝብ መፍጀት ላይ ታጥቀው የተነሱ ወንጀሎች በብዛት ያሉባት አገር ሆናለች፡፡ ዳሩ ግን ያገሪቱ መሪ ፕሬዝዳንት አል ሲሲ የአፍሪካ ሕብረት ድርጅት ግዚያዊ ፕሬዚዳንትም ስለሆኑ የአፍሪካ ዋንጫ ማዘጋጀት ስላማራቸው አስፈላጊው ዝግጅት እንዲደረግ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ባለፉት ዓመታት ውስጥ የግብፅ ቡድኖች የሚጫወቱት በባዶ ስታዲየም ውስጥ ነበር፡፡ እርስ በራሳቸው በመፋለጥ የብዙ ሰው ሕይወት ስለጠፋ ፀጥታን ለማስከበር የተገኘው ፈሊጥ በባዶ ስታዲዮም ግጥሚያ በማከናወን ስለሆነ ነው፡፡ ኢትዮጵያም በዘር ምስቅልቅልዋ የጠፋ ስለሆነ ባዶ ስታዲየም ውስጥ ማጫወት ጀምራለች፡፡

ግብፅ የአፍሪካ ፉትቦል ኮንፌዴሬሽንን ከኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ደቡብ አፍሪካ ጋር በመሆን የመሰረተችው እስካሁን አምስት ግዜ የአፍሪካ ዋንጫን ውድድር ማዘጋጀትዋ ነው፡፡ ኢትዮጵያም ሶስት ግዜ አዘጋጅታለች፤ አዲስ አበባ በ1962 - 1968 - 1976 ዓ.ም፡፡ የግብፅ መሪ ወታደር እንደመሆናቸው መጠን የጦር ኃይሉ በዝግጅቱ ፈላጭ ቆራጭ ነበር፡፡ ለምሳሌ አራት ጀነራሎች ጡረታ የወጡ የፀጥታ አስከባሪ ኩባንያ በማቋቋም፤ አራት ሺ በሜዳ ውስጥ የሚያገለግሉ ሠራተኞች ቀጥረዋል፡፡ በሰማይ ላይ ብቻውን የሚበረውን ድሮን የሚሉትን መሳሪያ ኩባንያው ተከራይቶ ተጠቅሞበታል፡፡ በካይሮ ከተማ ብቻ ወደ አስር የሚጠጉ ስታዲየሞች ሲኖሩ ዋናዎቹ የጦር ኃይሉ ናቸው፡፡

በፀጥታ ችግር የተነሳ ግጥሚያዎቹ በተጀመሩበት ዕለት ተመልካቾች ከሶላት በፊት ስታዲዮም መሄድ ሲኖርባቸው ቢያንስ አምስት ግዜ ይፈተሹ ነበር፡፡ የቴሌፎን ባትሪ፣ ሽቶ በብልቃጥ ይዞ መግባት ክልክል ነበር፡፡ ግብፅና ዙምባብዌ ሲጫወቱ 75ሺ ተመልካች ነበር፡፡ ኮንጎ ከኡጋንዳ ሲገጥም 1ሺ ሰው ነበር፡፡ ግብፅ ከውድድሩ ከወጣች በኂላና ፕሬዚዳንት አል ሲሲ የፌዴሬሽናቸውን ባለሥልጣኖች በሙሉ እንዲሰናበቱ ካዘዙ በኂላ ወደ ኳስ ሜዳ የሚሄድ ሰው ጠፋ፡፡ ስታዲየሞቹ ዘጠና በመቶ ባዶ ነበሩ፡፡ ግጥሚያዎችን የሚመለከቱት ከተካፋይ አገሮች የመጡት የተወሰኑ ነበሩ፡፡ የመግቢያ ቲኬት ዋጋ 150 ብር 450 ብር 780 ብር ነበር፡፡ ይሄም ሆኖ ስታዲዮም የሚገቡት የጦር ኃይሉ ባልደረቦች በነፃ ነበር፡፡

ውድድሩ በተካሄደበት ስምንት ስታዲዮ ሞች ውስጥ ፀጥታ ለማስከበር 120 ሺ ወታደሮች ተሰማርተው ነበር፡፡ ከካይሮ ቀጥሎ ትልቁ ከተማ ከኢትዮጵያ ጋር በታሪክ የተሳሰረው አሌክሳንደሪያ ነው፡፡ ዓፄ ምኒልክ የመጀመሪያውን ትምህርት ቤት አዲስ አበባ ላይ ሲከፍቱ፤ የቀጠሩዋቸው አስተማሪዎች የአሌክሳንደሪያ ተወላጆች የሆኑ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ነበሩ፡፡ በዚያን ወቅት የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ የአሌክሳንደሪያ ጳጳስ ነበሩ፡፡ እ.አ.አ በ1950 ውስጥ ነው የራሳችን ፓትሪያርክ ያገኘነው፡፡ የዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ ትምህርት ቤትም ሆነ ተፈሪ መኮንንና ሌሎችም እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ ድረስ ያስተምሩ የነበረው በፈረንሳይኛ ቋንቋ ነው፡፡ እንዲያውም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ስላልነበረ ብዙዎች ማለትም እንደ ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ አካለወርቅ ሐብተወልድ፣ ክፍሌ ዕርገቱ፣ ኢያሱ መንገሻ፣ ዋቅጅራ ስርዳ የመሳሰሉት ከፍተኛ ባለስልጣኖች አሌክሳን ድሪያ ሊሴ ከጨረሱ በኂላ ነው ወደ ፈረንሳይ አገር ትምህርታቸውን ለመቀጠል የሄዱት፡፡ ሌሎቹ ወደ ቤሩት ሲያመሩ፤ አቶ ማሞ ታደሰ ግን ካይሮ ተምረዋል፡፡

አሌክሳንድሪያ ብዙ ግሪኮች ይኖሩባት የነበረች ከተማ ስለሆነች በከተማዋ ውስጥ የነበሩ የስፖርት ቡድኖች፣ በኦሎምፒያኮስ ክለብ ጋባዥነት እየመጡ አዲስ አበባ ይጫወቱ ነበር፡፡ የኦሎምፒያኮስ ክለብ ዘበኛ የዝነኛው አርቲስት የሙሃመድ አህመድ አባትን እያስፈቀድን፤ የጉለሌ ልጆች ኳስ መጫወቻችን እዚያ ነበር፡፡ አሌክሳንድሪያ ከተማ ውስጥ ያለውን ስታዲዮም እ.አ.አ በ1920 ውስጥ በራሱ ገንዘብ የአፍሪካን ጨዋታ ለማዘጋጀት ያሰራው የግሪክ ተወላጅ የሆነው የኢንተርናሽናል ኦሎምፒክ ኮሚቴ አባል የነበሩት መሲዬ ቦላንካ ነበሩ፡፡ እሳቸውም ከልዑል ራስ ተፈሪ መኮንን ጋር እ.አ.አ በ1924 በፓሪስ ከተማ በተከናወነው የኢሎምፒክ ጨዋታ አማካይነት ተገናኝተዋል፡፡ ግብፅ በመላው ዓለም የታወቀችው በ138 ፒራሚድዋ ነው፡፡ ነገር ግን በቁመታቸው አነስ ይበሉ እንጂ ጎረቤታችን ሱዳን 220 ፒራሚድ አላት፡፡ የሱዳን ሚሊቴር ዲክታተሮች እንደ ግብፆቹ ዲክታተሮች ለቱሪዝም በር ስላልከፈቱ

**በፀጥታ ችግር የተነሳ ግጥሚያዎቹ በተጀመሩበት ዕለት ተመልካቾች ከሶላት በፊት ስታዲዮም መሄድ ሲኖርባቸው ቢያንስ አምስት ግዜ ይፈተሹ ነበር፡፡ የቴሌፎን ባትሪ፣ ሽቶ በብልቃጥ ይዞ መግባት ክልክል ነበር፡፡ ግብፅና ዙምባብዌ ሲጫወቱ 75ሺ ተመልካች ነበር፡፡ ኮንጎ ከኡጋንዳ ሲገጥም 1ሺ ሰው ነበር፡፡**

አንዳንዴ ሙቀቱ 50 ዲግሪ መድረሱ ካልሆነ በቀር ሌላ የሚታወቅ ነገር ያላት የጦርነቱ ብዛት ነው፡፡ የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መዳበራችንን ምልክት ሰጥተዋል፡፡ በፌስ ቡክ አማካይነት 30 ሚሊዮን የሚደርስ መልዕክት ተለዋውጠዋል፡፡ ዋናዎቹ ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ጋና፣ ሴናጋልና አልጄሪያ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ኢንተርኔት አገልግሎት መቼ እንደሚዘጋና እንደሚከፈት ጠንቋይ መጠየቅ ስለሚያስፈልግ ፌስቡካቸው ለሚማሰል ሳይቸገሩ አልቀሩም፡፡ ከኳስ ጨዋታው በስተጀርባ የአፍሪካ ፉትቦል ኮንፌደሬሽን መሪዎች ንትርክ በጣም አሳዛኝ ሆኗል፡፡

በመጀመሪያ ነገር በሞሮኮና በግብፅ መንግሥታት የገንዘብ ዕርዳታ የተመረጠው የማዳጋስካር ተወላጅ አህመድ በመባል የሚታወቀው አፍሪካን ሲያዋርድ ከርሟል፡፡ የአሜሪካ መንግሥት ቪዛ ከልክሎት የነበረው፣ በፈረንሣይ ፖሊስ ተይዞ የተመረመረው፣ የጽሕፈት ቤቱን ሰራተኞች ለማባለግ የሞከረው፣ የድርጅቱን ገንዘብ በመዝረፍ ላይ የሚገኘው አህመድ የፊፋ ፕሬዘዳንት የሆነው የማፊያ ሲስተምን የሚከተለው የጣሊያን /ስዊስ ተወላጅ ኢንፋቲኖ ሊያድነው እየጣረ ነው፡፡ አፍሪካ ራስዋን ማስተዳደር ስላልቻለች የፊፋ ዋና ፀሐፊ የሆነችው፣ የሴነጋል ተወላጅ ተንኮለኛ፤ ለስድስት ወር የአፍሪካን ፉትቦል ኮንፌደሬሽንን እንድታስተዳድር ተወስኗል፡፡ ኢንፋቲኖን ከሴኔጋሉዋ ፋትማ ጋር ያስተዋወቀው አህመድ ነው፡፡ ስለዚህም ለፊፋ ሥነ ምግባር ኮሚቴ አህመድን በመክሰስ ደብዳቤ የፃፉት ሁሉ ጉዳያቸው እንዳይታይ ዕንቅፋት የተደረደረ ይመስላል፡፡ አንድ የላይቤሪያ ተወላጅ የፋትማን መሾም የተቃወመው የኢንፋቲኖ ረዳት ማስጠንቀቂያ ሲሰጠው ስላላረፈ አስር ዓመት ከእግር ኳስ አገልግሎት እንዲርቅና አምስት መቶ ሺ የስዊስ ፍራንክ እንዲከፍል ፊፋ ወስኖበታል፡፡ እኛ ያባረርነው ጣሊያን እንደገና ተመልሶ አፍሪካን ያተራምሳታል፡፡

መከራው በሙስና የተመረዘ የእግር ኳስ ፌደሬሽን ፕሬዚደንቶች መብዛት ነው፡፡ ሁሉም ችግረኛ ስለሆነ በቀላሉ ይሰግዳል፡፡ ጠንካራዎቹን በምርጫ እንዲወድቁ ያደርጋሉ፡፡ ኢንፋቲኖ ያቋቋመው የማፊያ ቡድን 32 ድምፅ አፍሪካ ውስጥ አለው፡፡ አፌን እከፍታለሁ የሚለውን በዶላር ይዘጉታል፡፡ የአፍሪካ ኮንፌደሬሽን መሪዎች ማዳጋስካር፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ሞሪታኒያ፣ ቻድ፣ ሞሪሺየስ ናቸው፡፡ አህመድ ደሞዙ አርባ ሺ ዶላር በወር፤ የቀን አበሉ ደግሞ አራት መቶ አምሳ ዶላር ነው፡፡ የካፍ ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎች በዓመት ስልሣ ሺ ዶላር ያገኛሉ፡፡ በፊፋ ሥራ አስራኪያጅ ኮሚቴ ውስጥ ያሉት በዓመት ሶስት መቶ ሺ ዶላር፤ የቀን አበል አምስት መቶ ዶላር ያገኛሉ፡፡ ብዙዎቹ ለምርጫ የሚወዳደሩት አፍሪካን ለማገልገል ሳይሆን ራሳቸውን ለመጦር ነው፡፡ አህመድ ባቅሙ ለፌዴሬሽን ፕሬዚደንቶች ሀያ ሺ ዶላር በዓመት ሰጥቷል፡፡ ለዚህ ነው ስለ ስነ ምግባር ሲነሣ "ተወኝ ልጆቼን ላሳድግ" የሚለው የበዛው፡፡ ይሄ ሁሉ ውርደትና ዘረፋ በኢሣ ሃያቱ ግዜ አልነበረም፡፡ በአቶ ይድነቃቸው ግዜማ ፊፋም ራሱ ገንዘብ አልነበረውም፡፡ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ፉክክር በበዛበት ዘመን ነው ፊፋ ቢሊየነር ሆኖ ለነ አሕመድ መቀለጫ ገንዘብ የሚሰጠው፡፡ አይ አፍሪካ የተበደለ አህጉር ነው፡፡ ክብሩን የሚጠብቅ በፉትቦል ዓለም ውስጥ ጠፍቷል፡፡

# ኢሕአዴጎች ኢትዮጵያን ማስተዳደር ካልቻሉ…?



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

በዚህ ጽሑፍ ማቅረብ የምፈልገውን አስተያየት በሁለት ክፍል ከፍዬ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡ የመጀመሪያው ኢሕአዴግ 28 ዓመት ሙሉ ሃገሪቱን በየትኛው የኢኮኖሚና የሀብት መሰረት ሊያስተዳድር ቻለ? የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ አሁን ወደ ፊት ለመራመድ ምን አይነት ችግር ገጠመው በሚል፡፡

እንደሚታወቀው ኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን እንደመጣ ደርግ አቋቁሟቸው የነበሩ ኮርፖሬሽኖችን፣ የልማት ድርጅቶችን በማፈራረስ ስራ ነበር የተጠመደው፡፡ ኢሕአዴግ በመርሕ ደረጃ "ኢትዮጵያ" የምትባልን ሃገር እንደ ዮጎዝላቪያ ከካርታ ላይ ለማጥፋት ዋነኛ ዓላማው ስለነበር፣ እነዚህን መስሪያ ቤቶች ሁሉ በማፈራረስ ወደ ክልል ለመውሰድ ሌት ተቀን ደከመ፡፡

የሚያሳዝነው ስንት ቢሊዮን ብር ወጥቶባቸው፣ የተጠኑ (በቀድሞ ሶሻሊስት አገሮች ትብብር ጭምር) ሰነዶች ከየመስሪያ ቤቱ ወጥተው እንዲጣሉ ተደርጓል፡፡ በዚያን ዘመን ደግሞ ሶፍት ኮፒ የሚባል ነገር ባለመኖሩ፤ ያ ሁሉ ሀብት የስኳርና የቆሎ መጠቅለያ ሆኖ ተወገደ፡፡

በወታደራዊ መሥክም ደርግ "መከድ" የሚባል የወታደራዊ ትጥቅ እና ቴክኖሎጂ እንዲያመርት ያደራጀው መሥሪያ ቤት እንዲበተን ተደርጎ፣ ንብረቶቹም አብዛኛው በሻዕቢያ እንዲዘረፍ ተደርጎ ነበር፡፡ ባሕር ሐይል መሥሪያ ቤት ደግሞ የነበረው ሰነድ ሁሉ በጭነት መኪና ተጭኖ፣ ቆሼ ተራ እንዲቃጠል ነበር የተደረገው፡፡

ይህ ሂደት ከ1983 — 2000 ዓ.ም ድረስ ሲካሄድ ቆይቶ፣ ከሁለት ሺን ዓ.ም ጀምሮ እነዚህ መስሪያ ቤቶች እንደገና መቋቋም ጀመሩ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ምን እንደሆነ መረጃው ባይኖረኝም፤ ክልሎች ማንም የማያቃቸው መንግሥታት በመሆናቸውና ምንም ዓይነት ተግባር መፈፀም ባመቻላቸው፣ ሁሉም ነገር ቀጥ ብሎ ለረጅም ጊዜ መቆየቱና በተጨማሪም የምርጫ 97 ሁኔታ የፈጠረው ድባብ ኢሕአዴግ ሐሳቡን ለመቀየር ሊያስገድደው እንደቻለ መገመት ይቻላል፡፡

ኢሕአዴግ የፌደራል መንግስት የልማት ተቋማትን ለማፈራረስ ተግቶ ሲሰራ እጅግ መተኪያ የሌላቸው ታላላቅ ምሁራን የትም ተበትነው የቀሩ ከመሆኑም በላይ፤ እነሱ በስራ ላይ ቢቆዩ ኖሮ፣ ሊተኳቸው ለሚችሉ አዳዲስ ምሁራንን እውቀታቸውን ሲያስተላልፍ በመቅረታቸው፤ አሁን ለደረስንበት አዘቅት ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳበረከተ መገመት ብዙም አያሳስብም፡፡

ኢሕአዴግ ሊያፈራርሳቸው ከነበሩ መሥሪያ ቤቶች አንዱና ያልተሳካለት ደግሞ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ነበር፡፡ በወቅቱ እኔም እዚያ አካባቢ እሰራ ስለነበር፣ ያለውን ሁኔታ በቅርበት ለመከታተል እድል አጋጥሞኛል፡ ፡ የድርጊቱ ዋና አስተባባሪ አቶ ስዬ አብርሃ የነበረ ሲሆን፤ የጀመረው ስራ በአሜሪካኖች ከፍተኛ ተቃውሞ ስላስነሳበት ሳይሳካላት እንደቀረ መረጃው አለኝ፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ኢሕአዴግ ለ17 ዓመታት አገርን ወደ ፊት ሊያራምዱ የሚችሉ በርካታ ኮርፖሬሽኖችን በማፈራረስ ተግባር ላይ ተጠምዶ የነበረ ሲሆን፤ የጫካው ቡድን መጀመሪያ ስልጣን ይዞ ከነበረበት ጊዜ አንስቶ፣ እጅግ በርካታ እርዳታዎችን ያገኝ የነበረ በመሆኑ ሕልውናውን ለማስቀጠል እንደደረጃው መጠቀም የግድ ይላል፡፡

ቀስ በቀስ ደግሞ ቻይና ከአሜሪካኖች ጋር ያልተግባባችበት አንድ ጉዳይ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ቻይና በእጇ ላይ ከፍተኛ የሚባል የዶላር ክምችት እየተጠራቀመ ሲመጣ፣ ይህንን ገንዘብ አሜሪካኖች እንዲወስዱና በምትኩ ለቻይና ወርቅ እንዲሰጦ በቻይና መንግስት ለአሜሪካ የቀረበ ጥያቄ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ጥያቄ በክንግረሱ ውድቅ በመደረጉ፤ ቻይና ይህንን ገንዘብ ወደ አፍሪካ ለማዞርና ለአፍሪካ ኢኮኖሚ በብድር እንዲቀርብ ለማድረግ፣ የኮሚኒስት ፓርቲው በመወሰኑ የቻይና ገንዘብ በገፍ ወደ አፍሪካ መጉረፍ ጀመረ፡፡

በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያም ይህንን ገንዘብ በብድር መልክ በከፍተኛ መጠን ማግኘት በመቻሏ እጅግ በርካታ ግንባታዎች ተካሂደዋል፡ ፡ ነገር ግን እነዚህ ግንባታዎች አብዛኞቹ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች በመሆናቸው፤ በራሳቸው አቅም ብድራቸውን የመክፈል ብቃት አልነበራቸውም፡፡ ገንዘብ ሊያመጡ የሚችሉትም ፕሮጀክቶች በሙስናና ብቃት ባለው ምሁር፣ መመራት ባለመቻላቸው ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ፤ በእዳ ውስጥ ተዘፍቀው አገሪቱን ወደ ከፋ ሁኔታ እየመሩዋት ነው፡፡ አሁን ደግሞ አብዛኛው ኢትዮጵያ የወሰደቻቸው ብድሮች የመክፈያ ጊዜአቸው ደርሷል፡፡

ከቻይና የወሰድነውን ገንዘብ የሚያበድረው የቻይና EXIM BANK ብድሮች እዳ የመክፈያ ወቅታቸው ሲደርስ፤ ክፍያ ካልተከፈለ፣ ለሌሎች ሳላለቁ ፕሮጀክቶች ገንዘብ የሚለቀቅበት አሰራር ስለሌለው፤ በአሁኑ ጊዜ የምናያቸው አንዳንድ ፕሮጀክቶች ሳይጠናቀቁ ቀጥ ብለው ቆመዋል፡፡ ብዙ የአፍሪካ ሃገሮች እንደኛው ብድራቸውን መክፈል ባለመቻላቸው፣ ወደቦቻቸውንና ሌሎችንም ንብረቶቻቸውን ለቻይና በማስረከብ ላይ ናቸው፡፡

> እያየናቸው ያሉ ችግሮች እየተባባሱ እንጂ እየተሻሻሉ ሊሄዱ የሚችሉበት ምንም ዓይነት ተግባር እየተከናወነ ባለመሆኑ ሃገሪቷን የሚጠብቃት እጅግ የከፋ ሁኔታ ነው ቢባል ትክክል ይመሥለኛል፡

መንግስት "መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች ይንቀሳቀሳሉ፣ እዳው ከተከፈለ በኋላ እነዚህ የቆሙ ፕሮጀክቶች ይንቀሳቀሳሉ" የሚለው አስተሳሰብ ብዙም የሚያስኬድ አይመሥለኝም፡ ፡ ምክንያቱም ሃገራችን ያለው የፖለቲካ አለመረጋጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰበት የሄደ በመሆኑ፤ የውጭ ባለሀብቶች በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር አውጥተው፣ ወደ ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ይመጣሉ የሚል እምነት የለኝም፡፡ የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ መንግስት የፖለቲካውን መድረክ ለማጥራት ምንም ዓይነት ጉዞ አልጀመረም ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የፖለቲካው ችግር መጥራት የሚችለው በዋናነት የሕገ መንግስት የማረም ተግባር ሲጀመር ነው፤ በዚህ አቅጣጫ የተጀመረ ምንም የሥራ እንቅስቃሴ የለም፡፡

በሌላ አነጋገር አሁን እያየናቸው ያሉ ችግሮች እየተባባሱ እንጂ እየተሻሻሉ ሊሄዱ የሚችሉበት ምንም ዓይነት ተግባር እየተከናወነ ባለመሆኑ ሃገሪቷን የሚጠብቃት እጅግ የከፋ ሁኔታ ነው ቢባል ትክክል ይመሥለኛል፡፡

ሐሳቤን ለማጠቃለል፤ ኢትዮጵያ ባለፉት 28 ዓመታት እንደ መንግስት መቀጠል የቻለችው፣ እንደ ቻይና ያሉ ሃገሮች ፊታቸውን ወደ አፍሪካ በማዞራቸውና ከፍተኛ የሚባል ገንዘብ በማፍሰሳቸው ሲሆን፤ አሁን ግን ይህ ሁኔታ ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ በእጅጉ የጠበበ ነው፡፡ ወቅቱ በድር በገፍ የሚገኝበት ሳይሆን፣ እዳ የሚከፈልበት በመሆኑ፡፡ ፈረንጆች (Spill over effect) እንደሚሉት አባባል ማለት ነው፤ ይህ ማለት የአንድ አገር ሀብት ሞልቶ ሲተርፍ ለሌሎች አገሮች የልማት //////////// ተፈጠረ እንደማለት ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ግን ኢሕአዴግ ዙሪያው ገደል ሆኖበታል፤ ሁኔታውም ከቁጥጥር ውጭ እየሆነበት ነው፡፡ ሕገ መንግስቱን ለመንካት ብቃት ካጣ፣ ሌላ የሀብት ምንጭ ማግኘት ካልተቻለ፣ የሃገሪቱን መሠረታዊ የሆኑ ወጪዎችን ማለትም እንደ ነዳጅ፣ መድኃኒት፣ የመሠሉ ምርቶችን መግዛት ካልተቻለ፤ በኔ ግምት ኢሕአዴጎች እርስ በርሳቸው ወደሚባሉበት ደረጃ የሚሄዱ ይመስለኛል፡፡ ለዚህም በቂ ዝግጅት እያደረጉ እንደሆነ በየቀኑ የምንሰማው ነው፡፡ ኢሕአዴግ አፈጣጠሩ በቡድን ስሜት የተዋቀረ በመሆኑና ሃገራዊ ምንም አጀንዳ የሌለው በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ ነገር ለድርጅቱ የትርፍ ጊዜ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም መጪው ጊዜ በእኔ እይታ ጥሩ ጊዜ ይሆናል የሚል እምነት ባያሳድርብኝም፤ ዕድሜ ይስጠንና የሚሆነውን አብረን ለማየት ያብቃን እላለሁ፡፡

# አንደበት



“አሁን 16 ባንኮች አያስፈልጉንም፡፡ ምክንያቱም ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ባንኮችን የሚመሩ ሰዎች የሉንም፡፡ የባንክ መሪዎች የሉንም እኮ፡፡ ገበያ ውስጥ የሉም፡፡ ባንኮች ካፒታላቸውን በጠቀስኩት ደረጃ እንዲያሳድጉ መንግሥት ይህንን ነው ማለት የሚችለው፡፡ ሌላ ነገር ማድረግ የለበትም፡፡ ጊዜ ሰጥቶ የንግድ ባንኮች ካፒታል ከአሁን ጀምሮ እስከ ሦስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ አምስት ቢሊዮን ብር መሆን አለበት ነው ማለት ያለበት”

አቶ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ
/የኅብረት ባንክ ቦርድና የዳያስፖራ ትረስት ፈንድ ቦርድ ሰብሳቢ/
ሪፖርተር ጋዜጣ ሐምሌ 21 ቀን 2011 ዓ.ም



“የውጭ ኃይላት አሉ የምንለው፣ እስካሁን በየቦታው በታየው እንቅስቃሴ መሰረት ነው፡፡ “ወያኔ ገንዘብ እየሰጠ ያነሳሳል” የሚባልበት ሁኔታ አለ፤ በሀዋሳ ከተማ መዋዕለ ነዋይ ያፈሰሱ ሰዎች አሉ ይባላል፡፡ ቀደም ብሎም ቅር የሚያሰኙ እንቅስቃሴዎች ነበሩ፡፡ ይህን መንግሥት መከታተል ሲኖርበት ይህን ባለማድረጉ ጉዳቱ የከፋበት ጥፋት ሊፈፀም ችሏል፡፡ እንቅስቃሴዎቹ እስከነበሩ ድረስ፣ “ማን ነው ይህን የሚያደርገው? ተብሎ፣ በቡድን ሆነው የሚንቀሳቀሱትን መለየት ይቻል ነበር፡፡ ሂደቱን ማን ነበር በገንዘብ የሚረዳው? የሚለውን ወደፊት በምርመራ የምናየው ይሆናል፡፡ ነገር ግን፣ እኛ የውጭ ኃይል አለ ብለን እንገምታለን፡፡”

ዶክተር አየለ አሊቶ /የሲዳማ አርነት ንቅናቄ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል/
ኢትዮጲስ ጋዜጣ ሐምሌ 21 ቀን 2011 ዓ.ም



“የብሔር ማንነት ቅቡልነትን አግኝቶ እውነታው፣ በመረጃ የተደገፈና የተያዘ ጉዳይ ቢሆንም ግን የተቀመጠ መረጃና ማስረጃ የለም፡፡ ዝም ብሎ ተተረጎመ ግን የመረመረው ሰው የለም፡፡ ይህ አስተሳሰብ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ማንም ለምርምር ጥረት አላደረገም፡፡ ይህ የብሔር ማንነት አስተሳሰብ ቅኝ ገዥዎችም ለመከፋፈል በጣም የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነበር፡፡ በተለይም ፋሺስት ኢጣሊያ የሚጠቀምበት ተንኮል የተሞላበት አስተሳሰብ ስለመሆኑ የታሪክ እውነታ ያስረዳናል፡፡”

አቶ ሰብስቤ አለምነህ /‹‹ የብሔር ማንነት ቅዠት ›› መጽሐፍ ደራሲ
አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሐምሌ 20 ቀን 2011 ዓ.ም



“እርግጥ በደንብ አላይም፣ የሰው ቅርፅ ይታየኛል እንጂ ማንነት አልለይም፡፡ ብርሃን ይታየኛል፡፡ የመኪና መንገድ ማቋረጥ አልችልም፡፡ ቅርብና ሩቅን መገመት ያዳግተኛል፡፡ ራቅ ያለ ቦታ ለመሄድ ስፈልግ በሰው እገዛ ነው፡፡ በተረፈ ሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ግቢን እና መኖሪያ ቤቴን ራሴን ችዬ ነው የምንቀሳቀሰው”

አርቲስት ኬሮስ ኃይለሥላሴ
ታዛ መጽሔት ሐምሌ 2011 ዓ.ም



“….. አጋጣሚው ለእኔ ብቻ ሳይሆን ወደፊት በዳኝነት፣ በአትሌትነት፣ በተጨዋችነት፣ በብሔራዊ ቡድን ደረጃ በተናጠልም በቡድንም የሀገርን ስም ማስጠራት፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ነገር ማሳየት ማለት ምላሹ ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ በግልፅ አይቼበታለሁ፡፡ ለካ ብቻዬን አይደለሁም…… የኢትዮጵያ ህዝብ በእ ያንዳንዱ እንቅስቃሴዬና ስኬቴ ጀርባ አለ እንድልም አድርጎኛል፡፡”

በአምላክ ተሰማ /ኢንተርናሽናል አልቢትር/
ሀትሪክ ጋዜጣ ሐምሌ 24 ቀን 2011 ዓ.ም

# አባባል

- አምላክ ምንም ነገር ያለፋይዳ ወይም ያለ ግብ አያከናውንም፡፡ የማንኛውም እንቅስቃሴ መድረሻ ግብ የተሻለ ወይም የበለጠ የተዋበ መሆን አለበት፡፡
- ራስህን ለማግኘት ምርጡ መንገድ ለሌሎች በማገልገል ራስህን መርሳት ነው፡፡
- ለልጅህ ጥበብን መስጠት አንድ ሺኅ የወርቅ ቁራጮች ከመስጠት ይሻላል፡፡
- መልካም ቀን የጠበቀ መልካም ቀን ያገኛል፡፡
- ጤና ያለው ተስፋ አለው፤ ተስፋ ያለው ደግሞ ሁሉም ነገር አለው፡፡
- መልካም ሰዎች ይገደላሉ፤ ሞት ግን ስማቸውን ሊገድለው አይችልም፡፡
- እውቀት ወይም ማወቅ የሚጀምረው ከመደነቅ ነው፡፡

# ግጥም

## የቆሎ ተማሪው፣

ሀሁና አቡዲዳ መልክተ ዮሐንስ፣
ከዚያም ውርድ ንባብ ደጋግሞ ሲከልስ፣
የቆሎ ተማሪ ደስታው አያድርስ፣
ያንደኛ ደረጃ የቄስ ትምሕርቱን፣
እንዳረጋገጠ በንባብ ብቃቱን፣
ደረጃው ጨምሮ ወንጌልን ሲጀምር፣
ሀሁ ተማሪዎች ይሰጡታል ክብር፡፡
የቆሎ ተማሪው ትምርቱን ለመግፋት፣
ግዴታ ይሕወቱን ነብሱን ለማቆየት፣
ወይ ዘኬ ወይ ቁራሽ መለመን አለበት፡፡
እናም ፋታ ሲያገኝ መንደር ወጣ ብሎ፣
ውሻ ሲያሯሩጠው እንደምንም ችሎ፣
እግሩ ላይ ተነክሶ የግዱን ሲያነክስ፣
በጣም ከተጎዳም ደሙ እንደ ጉድ ሲፈስ፣
ጭብጦም ተገኘ ወይም ትንሽ ቆሎ፣
ይቀማምስና ወስፋቱን ሸንግሎ፣
ከታዛው ይደርሳል እንደምንም ብሎ

ግዴታው አድርጎ ይሄን ሁሉ ችግር፣
የቄስ ትምሕርቱን ለመጨረስ ሲጥር፣
ዳዊትን ደጋግሞ ሲገባ ማኅሌት፣
ምስጋና ይቸራል በተማሪዎች ፊት፡፡

ኋላም ከፍ ብሎ ሲጀምር ድርሳናት፣
ዲግሪ እንደማለት ነው በቄስ ትምርት ቤት
ወደፊት ተራምዶ ጥበብ ሲመረምር፣
ቅኔ ዘረፋና ነጠቃ ሲጀምር፣
ፒ ኤች ዲ ያዘ ይባላል መምሕር፡፡
የቆሎ ተማሪው ሕልሙ ተሳክቶለት፣
መስቀሉን ሲጨብጥ ሲሆን ንሰሐባት፣
ወደኋላ ሄዶ ያለፈውን ሕይወት፣
እራሱ ለራሱ በትዝታ ስሜት፣
ሁሉ ነገር አልፎ ወይ እድሜ
መስታወት፣
ይህን አሳየኸኝ ብሎ በመደሰት፣

***አታኩራቸው ተጫኔ (1997 ኅዳር ወር)***

# የፎብያ አይነቶች

ገንዘብን መፍራት - ክሬማቶ ፎቢያ
ት/ቤትን መፍራት - ዲዳስካሌይኖ ፎቢያ
መጠጥ መፍራት - ዲፕሶ ፎቢያ
ሞትን መፍራት - ኔክሮ ፎቢያ
ሆስፒታልን መፍራት - ኖስኮ ፎቢያ
ወፍን መፍራት - ኦሪንቶ ፎቢያ
ቴክኖሎጂን መፍራት - ቴክኖ ፎቢያ
ሐይማኖትን መፍራት - ቲዎ ፎቢያ
አደጋን መፍራት - ትራውማቶ ፎቢያ
ውሃን መፍራት - ሀይድሮ ፎቢያ

# ስለ ቀለማት

**ቀይ፡-** ኃይልና ኃይለኝነትን ያሳያል፡፡ ለአንድ ድርጊት ያነሳሳል፤ ፍርሃትን ያስወግዳል፡፡ የምግብ ፍላጎትን ይጨምራል፡፡
**ጥቁር፡-** ጥልቅ መልዕክት አለው፡፡ የጥልቅ እውቀት ደረጃ ምልክት ነው፡፡ ሚስጥርን ይገልፃል፣ ኃይልን አምቆ ይይዛል፣ ኃያል አዕምሮን፣ ሥልጣንን እና አዋቂነትን ብቃትን እና ዳኝነትን ያሳያል፡፡ በቦታ እና በጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ ሲውል ጥልቅ ሀዘንን ያሳያል፡፡
**ሰማያዊ፡-** የውቅያስና የሰማይ ቀለም ነው፡፡ እውነተኛነት፣ ታማኝነት፣ መንፈሳዊነት፣ የአዕምሮ ኃይልን ያመላክታል፡፡ ሰማያዊ ቀለም ስንመለከት ሰውነታችን ስሜትን የሚያረጋጋ ንጥረ ነገር ያመነጫል፡፡
**ብርቱካን፡-** ሳቅ፣ ጨዋታ፣ ሙቀትና ሞቅታን ያሳያል፡፡ የምግብ ፍላጎትን ይጨምራል፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ያነሣሣል፤ ለስራ ያነቃቃል፡፡
**ቡናማ፡-** መረጋጋትንና ቀረቤታነትን ያንፀባቃል፤ የተፈጥሮአዊ መልክ መግለጫ ነው፤ ሙሉነትና ስርዓት ጠባቂነትን ያንፀባርቃል፡፡



# «ጥሩ ሥራ ሁሌም ፈተና ይበዛዋል»

## ቀኛዝማች ኃይሉ ቃለወልድ

**በ**ቀድሞው ሸዋ ክ/ሀገር, በአሁኑ ጉራጌ ዞን፣ ሶዶ ወረዳ "ክስታኔ" ከሚባል ስፍራ፣ በ1942 ዓ.ም ነው የተወለዱት ቀኛዝማች ኃይሉ ቃለወልድ፡ ፡ በ"ቃለወልድ የፕላስቲክ ውጤቶች ፋብሪካ" ውስጥ ባለቤትና ዋና ሥራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ ቀኛዝማች ኃይሉ ቃለወልድ፡፡ የ6 ልጆችንና 14 የልጅ ልጆችን አይተዋል፡፡ የእንግዳችን ቀኛዝማች ኃይሉ የሕይወት ጉዞን የግዮን ጋዜጠኛ ሙሉጌታ አክሊሉ እንዲህ ያስቃኘናል፡፡

**ግዮን፡- ቀደም ሲል የተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ ምንድን ነበር?**

ቀኛዝማች ኃይሉ፡- ንግድን በወጣትነት ዘመኔ የጀመርኩት ቢሆንም፣ ቢዝነሱ እያደገ እስከ ኢንፖ`ርተር ደርሼ (ከውጭ አስመጪነት) እየሰራሁ፣ የጃንሆይ መንግሥትን ጥሎ ደርግ ስልጣን ሲይዝ፣ የመንግስት ኮርፖ`ሬሽን በሚል እስከ ቀበሌ ድረስ ሥራው በመንግስት ቁጥጥር ስር ሆነ፡፡ በጊዜው የብዙዎች ንብረት እየተወረሰ ነበር፡፡ ያለችኝን ገንዘብ ለሃገሬ ምን ላይ ላውለው? በማለት፤ በ1974 ዓ.ም አነስተኛ ደረጃ ኢንዱስትሪን በተጠና መልኩ ለማቋቋም ወሰንኩ፡፡ የኢትዮጵያ የግል ኢንዱስትሪ የሚያቋቁም የመንግሥት አካል ስለነበር አላቂና ቶሎ ሊሸጥ የሚችል ማምረቻ ማሽን በማስመጣት የመጀመሪያውን የካርቦን ወረቀት ማምረቻ "ዘንባባ ካርቦን የወረቀት ፋብሪካ" በሚል በ1975 ዓ.ም ቦታ ይገኘ፣ በ1978 ዓ.ም ሥራውን ማካሄድ ጀመርኩ፡፡

በወቅቱ የኢንዱስትሪ ሚ/ርና ዘመቻ መምሪያው ለወርልድ ባንክ ሰዎች እንደ ሞዴል የእኔን ፋብሪካ እና ያኮና ኢንጅነሪንግን ያስጎበኙ ነበር፡፡ በ1981 ዓ.ም የሚክስድ ኢኮኖሚ አዋጅ በመውጣቱ፤ ቢሮው ሥራ ሲጀምር የምንዛሬ እጥረት ስለነበር ከውጭ ካርቦን ማሰመጣት ተጀመረ፤ ይሁንና ከውጭ የሚመጣውና በሀገር ውስጥ የሚመረተው ከፍተኛ የዋጋ ልዩነት ነበረው፡፡

**ግዮን፡- በወቅቱ አንድ ፋብሪካ ለማቋቋም ምን ያህል በጀት ይጠየቅ ነበር?**

ቀኛዝማች ኃይሉ፡- ከ480 ሺህ መብለጥ የለበትም፡፡ ለግል ባለሀብት ከዚያ በላይ ከሆነ አይፈቀድለትም፡፡ በወቅቱ የተጠጋጋ ገንዘብ ቀርቦም ፈቃድ ከወሰድኩ በኂላ "እንዴት ተፈቀደለት?" በሚል መጠነኛ ችግር ተፈጥሮ ነበር፡፡ ይሁንና ሚክስድ ኢኮኖሚ ሲታወጅ ወደ 3ሚሊዮን ብር ከፍ ተደረገ፡፡ የጥሬ ዕቃ በማጣታችንና ኢህአዴግ በ1983 ዓ.ም መላው አዲስ አበባን በመቆጣጠሩ፣ እንዲሁም ሻዕቢያ ነፃ ሀገር በማለት ኤርትራን በመያዙ፤ በአብዛኛው ኢትዮጵያዊያንን የሚያዙት እነርሱ ስለነበሩ "ትራንዚት" ተብሎ የፈለጉትን ዕቃ በሞምባ በኩል አምጥተው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ቀረጥ የሚሸጡበት አሰራር ነበር፡፡ በተፈቀደልኝ የውጭ ምንዛሬ የገዛሁት ዕቃ አሰብ ላይ እያለ፣ እነሱ ብዙ ዓይነት ካርቦኖችን ቀድመው አምጥተው ከተማውን አጥለቀለቁት፡፡ በዚህ ምክንት የእኛ ምርት መወዳደር ስላልቻለ ፋብሪካችን ያለ ስራ ቆመ፡፡ ያመረተነውን ካርቦን በአብዛኛው በኪሳራ የተሸጠ ሲሆን፣ እስካሁን ሳይሸጥ የተቀመጠም አለ፡፡

**ግዮን፡- ከዚህ በኂላ ነው የፕላስቲክ ማምረቻ ፋብሪካውን ያቋቋማችሁት?**

ቀኛዝማች ኃይሉ፡- በትክክል፡፡ "ገርጂ እርግብ ኢንተርናሽናል" በሚል ስያሜ የፕላስቲክ ፋብሪካውን በ1990 ዓ.ም ከባንክ ተበድሬ ነበር ያቋቋምኩት፡፡ በጊዜው ወደብ ላይ የነበረው የኢትዮጵያኖች ዕቃ በመወረሱና ፋብሪካው የመጀመሪያውን ዙር እየሠራ፣ ለ2ኛው ዙር የታዘዘው ጥሬ ዕቃም በዚህ ምክንያት በመውሰዱ፣ በተጨማሪም የባንክ ዕዳ ባለመክፈሉና "ኤክሳይስ ታክስ" በሚል በፕላስቲክ ዕቃዎች ላይ ከፍተኛ ቀረጥ በመጣሉ ብዙ ችግር ተፈጠረብን፡፡ በዚህ መልክ ብዙ ፈተናዎች ቢገጥሙንም እየታገልን በመስራት ከ20 ዓመት በፊት ነው ህንፃ ሰርቼ ይህንን ድርጅት ያቋቋምኩት፡፡

**ግዮን፡- ምን ዓይነት ነገሮችን ነው ፋብሪካው የሚያመርተው?**

ቀኛዝማች ኃይሉ፡- ከትላልቅ ምርቶቻችን መቀመጫ ወንበር፣ የማቡኪያ በርሜል፤ የአትክልትና የለስላሳና አልኮል መጠጥ መያዣ ሣጥን፣ ባልዲዎች፣ የዘርግ ሰሃን፣ ጀሪካኖችና ኩባያዎች የመሳሰሉትን በገጠሪቱ ኢትዮጵያም ሆነ በከተማ ላሉ ነዋሪዎች የሚሆኑ ምርቶችን በጥራት አምርተን፤ መርካቶ ባለ የመሸጫ መጋዘናችን እናከፋፍላለን፡፡ ከፋብሪካችን መጥተው ምርቱን የሚገዙም አሉ፡፡ ግቢው 200 ሜትር ካሬ ቦታን የያዘ ሲሆን፣ ፋብሪካው ኤል ሼፕ ሆኖ ተሰርቶ የቆመ ህንፃ አለው፡፡ ግራውንድ ፕላስ 2 መጋዘኖችም አሉን፡፡

**ግዮን፡- የፕላስቲክ ምርቶች ቀደም ሲል ከየት ነበር የሚመጡት?**

ቀኛዝማች ኃይሉ፡-በአብዛኛው ከኬኒያ ነበር የሚመጡት፤ እነዚህን ምርቶች ማስቀረት መቻላችን የውጭ ምንዛሪ ከሃገር እንዳይወጣ አድርገናል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሥራ ዕድልን ለወገኖቻችን ፈጥረናል፡፡ በተጨማሪም አዲስ ቴክኖሎጂን ወደ ሃገር ውስጥ በማስገባታችን ተጠቃሚነታችን ሰፊ ነው፡፡ ንፁህ ጥሬ ዕቃ ተጠቅመን ጥራት ያለው ምርት ከክብደት ጋር ማቅረባችን ስኬታማ እንድንሆን አድርጎናል፡፡

ብዙዎች ምርቶቻቸውን ያሳሱታል፣ የእኛ ሞልድ ግን አያሣሣም፡፡ በእርግጥ የዋጋ ልዩነት ቢፈጥርም ጥራትና ተጠቃሚው ሁልጊዜ ደስ ብሎት የሚጠቀምበትን ዕቃ እናቀርባለን፡፡ ለምርታችን ግብዓት የምንጠቀመውን ጥሬ ዕቃ ከሳዑዲ አረቢያ፣ ከኮሪያ፣ ከታይዋንና ከተለያዩ አውሮፓ ሃገራት ዋጋ አወዳድረን እንገዛለን፡፡

**ግዮን፡- በሰሩት ሥራ ውጤታማ ነኝ ይላሉ?**

ቀኛዝማች ኃይሉ፡- ባለኝ ነገር ሁሌም ደስተኛ ነኝ፡፡ ብዙዎች ሥራ ፈትተው ባለበት ወቅት፣ ለበርካታ ሰዎች የሥራ ዕድል ፈጥሬ፣ እራሴንና ቤተሰቤን እየረዳሁ በመኖሬ ውጤታማ ነኝ፡፡ እግዚአብሔር ብዙ ነገር እንደረዳኝ አምናለሁ፤ ራሴ ተጠቃሚ ከመሆኔ ባሻገር ለሀገሬም የምችለውን እያደረግሁ ነው፡፡

**ግዮን፡- ማህበራዊ ሓላፊነትን ከመወጣት አኳያስ ምን ሰርተዋል?**

ቀኛዝማች፡- በገጠር አካባቢ የወፍጮ አገልግሎት ባለመኖሩ ወፍጮዎችን አቋቁሜያለሁ፡፡ ለአካባቢው ማህበረሰብ ርቀት ተጉዘው የሚያገኙትን አገልግሎት በቅርብ አግኝተው ድካማቸውን በመቀነስ ረገድ ሓላፊቱን ተወጥቻለሁ፣ የ12 ኪሎ ሜትር ▶

መንገድ ሌሎችን በሊቀ-መንበርነት እየመራሁና በገንዘብም እያገዙ ከ15 ዓመት በፊት መንገድ አሰርቻለሁ፤ ይህንን ለማድረግ ስምንት ዓመት ፈጅቶብኛል፡፡ ለማህበረሰቡ የባህር ዛፍ በመስጠት እንዲተክሉ ከማድረግ በተጨማሪ ገንዘብም ረድቼያለሁ፡፡ የዕምነት ተቋማትን በመሥራትና ሥራውን በመከታተል፤ ኢህአዴግ በገባበት ጊዜ የነበረውን ችግር ለመፍታት ጉዳዩ እስከ ጠ/ሚኒስትሩና ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲፈፀም አድርጌያለሁ፡፡ ትልቁ ፀጋዬ ደግሞ ሰውን ማስታረቅ በመሆኑ ማህበራዊ ሓላፊነቴን ለመወጣት ተጠቅሜበታለሁ፡፡

በክስታኔ ውስጥ የነበረውን ያለመግባባት እርቀ - ሰላም እንዲሰፍን አድርጌያለሁ፡፡ ለአካባቢዬ ማህበረሰብ፣ ለቤተሰቦቼና ለቅርብ ወዳጆቼ ዕገዛ በማድረጌ “ነፃ አውጪ” የሚል ስም ሰጥተውኛል፡፡ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በመሥራትና ጉዳዮችን በመፈፀም ልማት እንዲካሄድ አድርጌያለሁ፡፡

ከትውልድ አካባቢዬ ወጣ ስንል ከመ ቄዶኒያም ሆነ ከሌሎች ተቋማት በአቅሜ እሰራለሁ፡፡ ከሜሪጆይ ጋር እስከ ሀዋሳ ድረስ አብሮ በመሄድ የአረጋዊያኖችን መንደር በመጎብኘት፣ የተቋቋመውን ቤተ መጻህፍት በማየት፣ ቤቶቹን እድሳት በማድረግ፣ ለአረጋውያኖቹም ሆነ ለወጣቶቹ የሚያ ስፈልጋቸውን ድጋፍ በመስጠትና የጠቅላላ ጉባኤው አባል በመሆን ሰፊ ተሳትፎ አድርጊ ያለሁ፡፡ ከማመርተው ምርት በመላክ አሁንም እያገዝኩ ነው፡፡

በመጀመሪያ “ኢትዮጵያዊያን፣ በኢትዮጵያዊያን” በሚል ነበር ፕሮግራሙ የተጀመረው፡፡ በ1996 ዓ.ም ከ 5 ሰዎች ጋር በመሆን ገንዘብ በማዋጣት፤ በኤች አይ ቪ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ 200 ልጆችን ከ2 ሞግዚቶች ጋር በማድረግ ምግብና መጠጥ በቤቴ አዘጋጅቼ፣ ለሕጻናቱ ልብስና የትምህርት መሳሪያ በማሰበሰብ ለሜሪ ጆይ ፈር ቀዳጅ በመሆን ነው የጀመርነው፡፡ በዕለቱ ለ4 ልጆች የሥራ ዕድል ሰጥቼያለሁ፡፡ “በቀጣዩ በዓል 10 ልጆች ባሉበት ድጋፍ እሰጣለሁ” ብዬ ቃል በመግባት የጀመርኩትን ሲስተር ዘቢደር በውጭ ያሉ ኢትዮጵያዊ ዲያስፖራዎች አግዘዋት፤ እሷም በካናዳ፣ አሜሪካና አውሮፓ እየተዟዟረች የተጀመረው ሥራ አጠንክራ እዚህ በማድረሷ አደንቃታለሁ፡፡

**ግዮን፡- የኢትዮጵያን ወቅታዊ ፖለቲካ እንዴት ይገልጹታል?**

ቀኛዝማች ኃይሉ፡- እኔ የቢዝነስ ሰው እንጂ ፖለቲከኛ አይደለሁም፡፡ የሀገሬ ሰው “ባናርስም እናጠምዳለን” ይላል፡፡ ከምንሰማው፣ ከምናነበው፣ ከምናየው ፖለቲካ የቁማር ጨዋታ በመሆኑ ያጋጠመውና የሚበላው ዕድለኛ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ በቁማር መበላት፣ መጣላትና መደባደብ የተለመደ ነው፡፡ ፖለቲካ በሰለጠኑት አገሮች በሰለጠነ ሁኔታ እየሄደ ነው፡፡ መሪው እየተሰደበና ክፉ ነው እየተባለ በሚዲያው ሁሉ እየተነገረ ይመረጣል፣ ጥሩ ነው የተባለው በድምፅ ብልጫ ሊወድቅ ይችላል፡፡ እንደ እኛ አገር በጉቦና በዘመድ መጨመላለቅ የለም፡፡ ለሀቅ ተብሎ ይሰራል፡፡ የአፍሪካ ፖለቲካ የመሣሪያ ፖለቲካ ነው፤ በመሳሪያ መውጣትና መውረድ አስቀያሚ ነገር ነው፡፡ ወደ ሥልጣን ከወጡ በኋላ የሚሰሩት ለራሳቸውና በቅርብ ለሚያውቁት (ለቤተሰባቸው) ነው፡፡ የሃገራችን ፖለቲካ ዥንጉርጉር ነበር፡፡

በጃንሆይ ስለ ፖለቲካ የሚያገባውም፣ ያልነበረ ግሩፕ ሁሉ “ምርጫ” ከተባለ ይመረ ጣል እንጂ ግንዛቤው አልነበረውም፡፡ ደርግ ደግሞ “እኔ ብቻ በምልህ ወደፊት አቅጣጫ ተጓዝ” አለ፡፡ በፖለቲካው ምክንያት በመቶ ሺኅ የሚቆጠሩ ልጆቻችንና ወንድሞቻችን ኢህአፓ ተብለው አልቀዋል፡፡ ኢህአዴግ ደግሞ በቀጥታ ሳይሆን እንደ ኤድስ አመንምኔ ነው፡፡ ሁሌ ፍርሃት ነው፣ ያስቀመጣቸውም ከላይ እስከታች ፈሪዎች በመሆናቸው ሲበላም፣ ሲዘርፍም…ዝም ነው ያሉት፡፡ እሱ በጠላትነት ሲፈርጅህ ደግሞ ምስክር ተገኘም አልተገኘም በሰበብ አስባቡ እስር ቤት ይወረውርሀል፡፡

ፖለቲካ ውስጥ የሌለንበት እንኳ አድጦን ብንናገር እንፈራለን፡፡ ወይ በገቢዎች ወይ በሌላ “አንድ ለአምስት” ተብሎ በደህንነት ይጠቃል፡፡ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ በንግግሩ የሃይማኖት አባቶችን አስተምሮ አስታርቋል፣ ሁሉንም አስተምሯል፡፡ የአሁኑ ፖለቲካ ዥንጉርጉርና ቁማር በመሆኑ ወዶና ፈቅዶ ተጫውቶ “ለምን እበላለሁ” ብሎ አምባጓሮ ይፈጥራል፡፡ አገርና እግዚአብሔር የሚፈቅደውን ሥራ እየሠራን፣ በንስሃ ብናልፍ እግዚአብሔር ይታረቀን ነበር፡፡ የፖለቲካ ሽኩቻው ስለሚሸተኝ፣ እኔም ልተንፍስ ብዬ ነው የምናገረው፡፡

**ግዮን፡- የቀኝ አዝማችነት ማዕረግን እን ዴት አገኙት?**

ቀኛዝማች ኃይሉ፡- በጃንሆይ ጊዜ ማዕረጉ የሚሰጠው በልማት ነበር፤ በወቅቱ በጀነራል ይልማ ሺበሺ አስተባባሪነት ቀኛዝማች የተባሉ ሰዎች ሁሉ ኮሚቴ አቋቁመው፤ በመላው ኢትዮጵያ እየዞሩ ሲዳማ ክ/ሀገር ሄደው አገሩን አቅንተዋል፡፡ ከሲዳማ፣ ጉጂ፣…. በጋብቻ በሚዜነት፣ በክርስትና በመተሳሰብ ልማትን አብሮ በማድረግ የተለያዩ ቦታ እየሠሩ ክስታኔዎች (ጉራጌው) ለመስቀል ወደ ቤተሰቡ በመግባት፤ በአካባቢው ያልነበረን ቤት ሰርቶ ከተማ በመመስረት ያቆዩ ናቸው፡፡

በወቅቱ ከዓለም ገና እስከ ሆሳዕና መንገድ ሰርተው ጃንሆይ “ቆንዳልቲቲ” (ሱታን) የተሰኘች ትንሽ ከተማን ጎብኝተው ቀኛዝማች፣ ግራዝማች በማለት የተለያዩ ሰዎችን ሾሙ፡፡ ሌሎች ያንን መንገድ የሠሩ ሰዎች የ10 ሺኅ ብርና የወርቅ ሚዳሊያ እውቅና ተሰጣቸው፡፡ ይህንን የሚያደርገው የጃንሆይ የበጎ አድራጎት

**ባለቤቴም በርካታ ሥራዎች ስለሰራች “እቴ” የሚል ቅፅል ማዕረግ ሰጥተዋታል፡፡ “ቀኛዝማች” ሲባል ተደግሶ ህዝብ መብላት አለበት በሚል ልጆቼ ደግሰው፤ በ1997 ዓ.ም የግንቦት ምርጫ አካባቢ ብዙ ድንኳን ቀርቦ ከገጠርና ከከተማ ሰው ተጠርቶ፣ ሌላ ካባ ተደርቦ በጋሻና ጦር አቀባበል ተደርጎልኝ ቀኛዝማችነቱ በይፋ የተለመደ ጥሪ ሆነ**

ድርጅት ነበር፡፡ ቀኛዝማችነት ተካ የተባሉት ጅማ ላይ የቡና ምርት አምራች ሲሆኑ ፣ በድሉ ደግሞ ህንፃ ሲሰራ “ቀኛዝማች በድሉ” የሚል ስምና ሰዓት በአልሚነታቸው ሸልመዋቸዋል፡፡

እኔ ደግሞ ከጢያ እስከ አሞቴ መንገድ በመስራቴና፣ ፖለቲካዊ የሆነ ችግርን ራሴን ለመስዋዕትነት እስከ ማዘጋጀት ለከፈልኩት ዋጋ፣ በቤተ ዕምነትና በአካባቢዬ የራሴን አስተዋፅኦ በማበርከቴ ነው የተሰጠኝ፡፡ በእኛ አካባቢ ማህበረሰብ ይህንን ስታደርግ ነው ቀኛዝማች የምተሰኘው፡፡ ጥር 21 ቀን የእመቤታችን የቅድስት ማሪያም የእረፍቷ ቀን፤ በጊዜው ድልድይ ሣይሰራ በበቅሎ ወደ ቦታው ሄዴን ታቦት ዞሮ ሲቆም፤ በ103 ዓመታቸው ያረፉት አባት ዕድሉ እንዲሰጣቸው ጠይቀው፣ እኔ የሰራሁትን ሥራዎች ለህዝቡ በጣፈጠ ቋንቋ ዘርዝረው “ከቀኛዝማችነት ማዕረግ በበለጠ ሰርቷል፣ የልማት ሥራ ላይ ጉልህ ቦታ አለው፤ ለህይወታችን የተቃጣ ፈተናን በመጋፈጥ ከሌሎች ጋር ሆኖ አድኖናል፣ ስለዚህም ኮሚቴው “ቀኛዝማች” በሚለው ማዕረግ እንዲጠራ ወስኗል በማለት መልዕክት አስተላለፉ፡፡ ህዝቡ በእልልታና በጭብጨባ፣ ካህናቱ በሽብሸባ ተቀብለው፣ ካባ ተደርቦልኝ፣ በወቅቱ ደንግጬና ፈዝዤ ብዙዎች እየሳሙኝ ወደቤቴ ባልጠበቅሁት ሁኔታ ተመለስኩ፡፡

ባለቤቴም በርካታ ሥራዎች ስለሰራች “እቴ” የሚል ቅፅል ማዕረግ ሰጥተዋታል፡፡ “ቀኛዝማች” ሲባል ተደግሶ ህዝብ መብላት አለበት በሚል ልጆቼ ደግሰው፤ በ1997 ዓ.ም የግንቦት ምርጫ አካባቢ ብዙ ድንኳን ቀርቦ ከገጠርና ከከተማ ሰው ተጠርቶ፣ ሌላ ካባ ተደርቦ በጋሻና ጦር አቀባበል ተደርጎልኝ ቀኛዝማችነቱ በይፋ የተለመደ ጥሪ ሆነ፡፡

አንዳንዶች ማዕረጉ “ከፍ” ይበል ቢሉም ይሄም ከብዶኛል፤ የተሰጠኝ የባለፈውን ሥራ በመሥራቴ ሳይሆን ለወደፊቱ ጥሩ እንድሰራ የሚያደርግ ነው፣ ለሀገር መሥራትና ማልማት ለመወደሻ ሳይሆን ለእግዚአብሔርም ለህዝብ የሚሆን ሥራን በትክክል መስራት ማለት ነው፡፡ ብዙ ኢትዮጵያዊ እዚያ ስላለ በማገዜ፣ ኢትዮጵያን ያገዝኩ ያህል ይሰማኛል፡፡ መንግሥት በሚያደርገው የልማት ሥራ ስሳተፍ ኢትዮጵያን እንዳገዝኩ ነው የማምነው፡፡ የብሔር አካሄድ ቀርቶ በፍቅር እንድንኖር ፀሎቴ ነው፡፡

**ግዮን፡- ማስተላለፍ የሚፈልጉት መዕልክት ካለ ዕድሉን እንስጥዎት?**

ቀኛዝማች ኃይሉ፡- ሁሉም የሃይማኖት አባቶች፣ በየቤተ-ዕምነቶቹ ለሃገራችን ይፀልዩ፣ ህዝቡን በበቂ ሁኔታ ስለሠላም፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ደህንነት ያስተምሩ፡፡ ሽማግሌዎች ወጣቱን ምክር ይለግሱ፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ቁጥር መብዛቱ ላይ ሳይሆን ሰላምና አንድነት ላይ ትኩረት ሰጥተው ያስተምሩ፡፡ ወጣቶች ነገ የምትረከቧት አገርን አልሚትና ለእናንተና ለልጆቻችሁ አስተላልፉ፣ የዛሬ ሠላም የእናንተም ነው፡፡ ፖለቲካን ለፖለቲከኞቹ፣ ግብርናውን ለገበሬው፣ የአክቲቪስትነት ሥራ ለአክቲቪስት እንተው፡፡ ጸሐፊያን ስለ ሃገር መልካም መልካሙን ጥሩ ፃፉ እላለሁ፡፡ አንድ እንጨት ብቻውን አይነድምና ጠ/ሚ/ር ዐቢይን እንጠብቅ፤ እናግዘው፤ ሲያጠፋ እንውቀሰው(እንምከረው) ለእርሱ ሁላችንም እንፀልይ፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

# የጋዜጣ የሕትመት ታሪክ፤ በኢትዮጵያ!



ብሩክ መኮንን

በ ኦክቶበር 1863 ዓ.ም ነው በምስራቅ አፍሪካ የመጀመሪያ የማተሚያ ቤት በዘመነ አፄ ቴዎድሮስ በላዛሪስት አባት ሎሬንዞ ቢያንቻኒ አማካይነት ቀይ ባህርን ተሻግሮ ወደ ኢትዮጵያ ምድር የዘለቀው፡፡ በጊዜው ምጽዋ ላይ ነበር ይሕ አነስተኛ የሕትመት ማሽን የተተከለው፤ ወደ ሀገረ አበሻ የማተሚያ ማሽኑን ያስገቡት የካቶሊክ ቄስ ራሳቸውን የአፄ ቴዎድሮስ ማተሚያ ኃላፊ በማድረግ ስራ ጀመሩ፡፡

ከረን ላይ በ1864 እስከ 1987 ዓ.ም ባሉት አመታት በላዛሪስት ሚስዮናውን አማካይነት የተዘጋጀውን የግዕዝ አማርኛ መዝገበ ቃላትን ለማዘጋጀት ተጠቅመውበታል፡፡ በ1885 የስዊድን ሚስዮናውያን ከምፅዋ ወደብ አቅራቢያ ምንኪሎ በተባለ ስፍራ አነስተኛ ማተሚ ቤት ከፍተው ነበር፤ ይኸው አነስተኛ ማተሚያ ቤት በኋላ ላይ ወደ አስመራ ተዘዋውሯል፡፡

በኢትዮጵያ የሕትመት ታሪክ ውስጥ በመጀመሪያ በግሪክ፣ በሶሪያና አረብ ቋንቋ የተጻፉ የሃይማኖት ጽሁፎችን በነፃ ትርጉም ወደ አማርኛ በመተርጎም፤ የቅዱሳንና የመላዕክትን ገድል የሚያወሱ ጽሁፎች ይታተሙበት ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የታተሙ ጽሁፎች በኢትዮጵያ የሕትመት ኢንዱስትሪ ዕድገት ውስጥ የራሳቸውን አሻራ ቢተውም፤ ለኢትዮጵያ የጋዜጣ ኢንዱስትሪ እድገት ያበረከቱት አስተዋፅኦ ግን እጅግ ውስን ነበር፡፡

የታወቁ መጸሐፍት በእጅ ፅሁፍ ከዘመን ወደ ዘመን የተሻገሩ በርካታ ሥራዎች መኖራቸውን ማንም የሚስተው ሀቅ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሕትመት ውጤቶች መታየት የጀመሩት፣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው፡፡

ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎች ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት በኢትዮጵያ ነገስታት በየቤተመንግስቶቻቸው ቅጥር አጠገብ ባሉ ከፍታ ቦታዎች ላይ ነጋሪት በመጎሰም፣ አዋጅ በማስነገር ነበር ከሕዝብ ጋር ይገናኙ የነበሩት፡፡

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ጋዜጣ የመገናኛ ብዙኃን አሰራር የተጀመረው በአፄ ሚኒልክ የስልጣን ዘመን፣ ከ1889 እስከ 1913 ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን፤ ከዘመናዊ ትምህርት መጀመር ጋር ዘመናዊ የማተሚያ የሕትመት ሥራ የሚሰሩ ተቋማት ሊቋቋሙ ችለዋል፡፡

በዚህ መልክ ለመጀመሪያ ጊዜ የጋዜጣና መጽሔት መልክ ያላቸው የሕትመት ውጤቶች መታተምን በመጀመር ፋና ወጊው በሐረር ይገኝ የነበረው የፍራቺስኮ ሚስዮናውን አባ በርናንድ ፍራንቼካ አማካይነት ከፊንጀንት ኩባኒያ በገዙት እና ሐረር ላይ በተከሉት የማተሚያ ማሽን አማካይነት በ1890 ዓ.ም በአማርኛና በፈረንሳይኛ ቋንቋ ይታተም የነበረ የስጋ ደዌ በሽታን ለመከላከል የሚካሄድ ዘመቻን የሚያወሳ de La lepruserice de Harrur የተሰኘ ዜና መጽሔት የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የህትመት ውጤት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ዓመታት ላይ በአዲስ አበባ ከተማ በቀይ ምስል በኢጣልያኖች ከምፅዋ ወደብ አቅራቢያ ናኩራ በተባለ ደሴት ለአመታት ታስረው የተፈቱት የኤርትራ ተወላጅ አርበኛ፣ ከአድዋ ድል ማግስት ጀምሮ በምንሊክ ቤተ መንግስት ባለሟል የነበሩት ብላታ ገብረ እግዚአብሔር አማካይነት ይዘጋጅ የነበረው "ዜና መጽሔት" ነው በኢትዮጵያ የጋዜጣ ታሪክ ውስጥ ቀዳሚውን ስፍራ የያዘው፡፡

ብላታ ገብረ እግዚአብሔር በእጃቸው በመፃፍ እያባዙ፣ በየሳምንቱ ያሠራጩት የነበረው አምሳ ቅጂ ብቻ ይታተም የነበረው በራሪ ዜና መጽሔት፤ በአፄ ምንሊክ ዙሪያ የነበሩ ፊውዳል መሳፍንት፣ መኳንንትን የሚተችና ለሀገሪቱ አንድነት እንዲሁም ዘመናዊ ስልጣኔ አስፈላጊነት የሚሰብክ እንዲሁም በተለያዩ ችሎቶች የተሰጡ ፍርዶች እና ብይኖች ላይ ትችት የሚያቀርብ በንጉሱና በተወሰኑ መኳንንት ዘንድ እጅግ ተወዳጅ ለመሆን የበቃ የሕትመት ውጤት ነበር፡፡

ይህንንም ተከትሎ በ1902 ዓ.ም በግሪካዊው ነጋዴ በእንድሪስ ኤካቫዲ አዘጋጅነትና አሳታሚነት አፄ ምንሊክ "አዕምሮ" ብለው የሰየሙት ባለ አራት ገጽ አማርኛ ሳምንታዊ ጋዜጣ መታተም ጀመረ፡፡ በእጅ እየተፃፈ ለወራት ይሰራጭ የነበረው አዕምሮ ጋዜጣ ከወራት በኋላ ግሪካዊው እንድሪያስ ኢካቫዲ የማባዢያ አነስተኛ ማሽን በማግኘታቸው፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቅጂው ከ24 ወደ 200 አደገ፡፡

በወቅቱ አነስተኛና በእጅ የሚሰሩ የማተሚያ ማሽኖች ወደ ሀገር መግባት በመ ጀመራቸው የአእምሮ ጋዜጣ በሀገሪቱ በወቅቱ ስለማዕከላዊ የመንግስት አስተዳደር ስርዓት እንዲሁም ሀገራዊ ማንነት ዜግነት ላይ ማዕከል ያደረጉ ፅሁፎች ይታተሙ ጀመር፡፡

በ1921 ዓ.ም በአልጋወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን አማካይነት በአሁኑ አ.አ.ዩ ወይንም በቀድሞ የገነተ ልዑል ቤተ መንግስት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከጀርመን ሀገር ባስመጡት አማርኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋ ፊደላትን የያዘ በእጅ የሚዘወር "ብርሃንና ሰላም" የሚል ስያሜ የሰጡትን ማሽን በመትከል በይፋ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤትን መሰረቱ፡ ፡ ይህ ማተሚያ ቤት ዘግየት ብሎ ትልቁ የመንግስት ማተሚያ ቤት ለሆነው ብርሃንና ሰላም ትልቅ መሰረት ሆኗል፡፡

ለረዥም አመታት ሲንገዳገድ የቆየው አዕምሮ ጋዜጣ ከሕትመት ውጭ ሆነ፡፡ መታተም ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ለአመታት ያለማቋረጥ ሲታተም የቆየው በየአስራ አምስት ቀኑ ለንባብ ይበቃ የነበረው፣ በፈረንሳይኛ ቋንቋ የሚዘጋጀው ኩሪየር ዲ ኢትዮጵያ የተሰኘው ጋዜጣ ነው፡፡

በ1923 ዓ.ም ሌሎች አራት የተለያዩ የማተሚያ ማሽኖች የተተከሉባቸው ማተሚያ ቤቶች ሥራ ጀመሩ፡፡ በ1924 አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን በአውሮፓ ሀገራት ያደረጉትን ጉብኝት አጠናቀው ወደ ሀገር እንደተመለሱ፤ የአክሱም ተወላጁና በአስመራ በሚገኘው የስዊድን ሚሲዮን የተማሩት ገብረክስቶስ ተክለሃይማኖት አዘጋጅነት በየሳምንቱ ሐሙስ ለንባብ የሚበቃው የብርሃንና ሠላም ጋዜጣ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት እየታተመ ለገበያ መቅረብ ጀመረ፡፡


በየሳምንቱ ሐሙስ በሁለት ፈረሰኞች አማካይነት በመላው አዲስ አበባ ይሰራጭ የነበረው "ብርሃንና ሠላም ጋዜጣ" በኮፒ ብዛቱም 500 ደርሶ ነበር፡፡ በዚሁ ዓመት በዚያው በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ለአመታት ተቋርጦ የነበረው አዕእምሮ ጋዜጣ በእንድሪያስ ካቫዲስ አሳታሚነት እንደገና እየታተመ መሰራጨትም ጀመረ፡፡

የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በወቅቱ አልጋወራሽ ራስ ተፈሪ የሀገሪቱ ንጉሰ ነገስትነት ለመቆናጠጥ ያደረጉት የሥልጣን ጉዞ ወቅት ልዩ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያቸው ይጠቀሙበት ነበር፡፡ የቤተ ክህነት ሰዎች ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ጽሑፎችን ከማሳተም በሻገር ስለ አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን የአመራር ጥበብ፣ ሊቅነትና ታላቅነት ለመስበክ ይገለገሉበት ነበር፡፡

እስከ ኢጣልያ ወረራ ድረስም ሆነ ከዚያ በኋላ አጼ ኃይለስላሴ የመገናኛ ብዙኃን የስልጣን እና የመንግስትን ኃያልነት ማረጋገጫ መሳሪያ መሆኑን በመረዳት የመገናኛ ብዙሃንን ጋዜጣ፣ ራዲዮና በኋላ ላይ ቴሌቪዥንን በራሳቸው ታማኞች ጥብቅ ቁጥጥር ስር እንዲቆይ አድርገዋል፡፡

የኢጣልያ ጦር ከኢትዮጵያ ተባሮ የወጣበት ዋዜማ ላይ ጆርጅ ስቲር የተባለ ታዋቂ ጋዜጠኛ በእንግሊዝ የጦር አውሮፕላኖች ከሰማይ የሚበተን "ባንዲራችን" የተሰኛ በራሪ ጋዜጣ አሳትሞ በማሰማራት የፀረ ፋሺስት ትግል ውስጥ የጎላ ድርሻ ተጫውቷል፡፡ ይህንም ተከትሎ በ1935 ዓ.ም የኢጣሊያን ጦር ከአድዋ ተሸንፎ መውጣት አንደኛ አመትን የድል በዓል መከበር ምክንያት በማድረግ በአማርኛና በአረብኛ ቋንቋ የሚዘጋጅ "ባንዲራችን" የተሰኘ ሳምንታዊ ጋዜጣ እየታተመ ለአመታት በስርጭት ላይ ቆይቷል፡፡

# “ኢትዮጵያዬ ብንረሳሽ ቀኝ ትርሳን”



ተሾመ ሺፈራው

ቀጥሎ የምታነቡት ልብወለድ አይደለም፤ እየፈጀን ያለው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ትኩሳት ለማቀጣጠል የፈጠርኹት “ማጣፈጫ” የምናብ ድርሰትም አይደለም፡፡ ይልቁንም እንደ ሀገር፣ እንደ ህዝብ የደረስንበትን ብሔራዊ ፈተና እንደ ብርሃን አምድ ቦግ አድርጎ የሚያሳየን እውነተኛ ገጠመኝ እንጂ፡፡ “የብሔርተኝነትን” ትራጄዲ ጎን፤ ገፅታ የምናይበት መስታወት ነው፡፡ የዚህ አሳዛኝ ታሪክ ባለቤትና ሠለባ እኔ በምኖርበት ሠፈር “በመንደርተኝነት” የማውቀው፣ ማህበረሰቡ “ዝቅተኛ” ብሎ ደረጃ ባወጣለት የስራ መደብ ውስጥ በመስራት መከረኛ እንጀራውን የሚያበስል ወጣት ነው፡፡

በካርል ማርክስ የስራ መደብ አገላለፅ “ወዝ - አደር” መሆኑ ነው፤ ካሬታ አንስቶ-ሲሚንቶ ተሸክሞ እንጀራውን የሚጋግር የቀን ሠራተኛ፡፡ ጨርቁን በድሮው የአዲዳስ ሻንጣ ሸክፎ፣ ሃገር ባቀናው ‘ዳፍ’ አውቶቢስ ተሳፍሮ፣ ከጎዠም አዲሳባ የገባው ይሄ ምስኪን ወጣት ዘመኑ የወለደው “የብሔርተኝነት” ዱላ ካረፈባቸው “እልፍ” ኢትዮጵያውያን አንዱ ሆኗል፡፡ የሚያሳዝነው እኮ ይሄ የሆነው የዓለም ዓቀፍ አስተሳሰብ ተፅዕኖ አለባት በምትባለው “ሜትሮፖሊታን ሲቲ” እያልን በምንደሰኩርላት አዲስ አባባ መሆኑ ነው፡፡ እናም ከዚያ ጉልበት መጣጭ ከሆነ የቀን ስራው ሲመለስ አንድ ማታ ያጫወተኝ፣ ይሄው የእንቁላል ፋብሪካ ሰፈር ልጅ የምረሳው፤ የሚረሳም አይደል፡፡

ይሄ ወጣትና እንደሱ የተሻለ ህይወት ፍለጋ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለ ሃገራት /ክልሎች/ ኑሯቸውን አዲ’ሳባ ያደረጉ የባለታሪኬ የስራ ባልደረቦች በአንድ የግል የግንባታ ህንፃ ስር ነው የሚሰሩት፡፡ እነዚህ የአዲስ አበባን ኑሮ መቋቋም ያቃተው ‘ፍራንካ’ እየተከፈለው በወጣትነት የጨለመ ህይወቱን ለመካስ፣ ወዙን በቀን ስራ የሚያፈሰው ባለታሪኬ እና መሠሎቹ አድራጊ ፈጣሪ የሚባል “አለቃ” አላቸው፡፡ በእነሱው አገላለጽ “ካቦ” (ጠርናፊም ይባላል) የሚሉት፤ መግቢያና መውጫ ሰዓታቸውን ተነቦ በተጣለ ጋዜጣ ምልክት የሚያደርግ ተቆጣጣሪያቸው፡፡ ሩጫ በሚፈልገው ዓለም ዓቀፍ “ሚኒማ” መግባቱን /መጨረሱን/ መሀል ሜዳ ላይ ቆሞ ሰዓት እንደሚቆጣጠር የአትሌት አሠልጣኝ አይነት፣ ዲስኮ ሰዓቱን ይዞ የነዚህ ወዛደሮችን መግቢያ-መውጫ ሰዓት በትኩረት የሚከታተለው ይሄው ካቦ ተብየው የሚያሳየው የበላይነት ስሜት መቸም ቃላት ሊገልፁት አይችሉም፤ ጦም ከማደር የማይተናነስ ክፍያ ከምታስገኘው ከዚች እንጀራ የሚነቅልም፤ የሚተክልም እሱ ነዋ፡፡

ለዚህ የሚያሳፍር ታሪክ መነሻ የሆነው ይሄው “ካቦ” ተብየው፤ የዕለት ተግባራቸውን እየከወኑ ሳሉ “ባለታሪኬን” ይጠራውና ከሌሎች “ወዛደሮች” ራቅ አድርጎ ይወስደዋል፡፡ አንድ ቀላል ጥያቄ ልጠይቅህ ይለዋል፤ ይሄው ካለበት ቦታ አንፃር ሰው ይሠራል፤ ሰው ያፈርሳል የሚባልለት ዋናው ተቆጣጣሪ፡፡

## “ምንድን ነው?” ይላል ወጣቱ

## “ብሔርህ ምንድን ነው?..... ማለት ከየት ነው?”

ግራ የተጋባው ይሄው ምስኪን ወጣት “አማራ” ብሎ በቅንነት ይመልሳል፡፡ “በቃ! አመሠግናለሁ..... ጥያቄዬን መልሰህልኛል!” ብሎ ወደ ሽቀላው እንዲመለስ አደረገው፡፡ የብሔሩ /ማንነቱ/ መጠየቅ ስሜቱን የረበሸው ባለታሪኩ “ለምን?” በሚል ጥያቄ ተጨነቀ፤ የሚገርመው ከዚህ እንጀራውን ሊያሳምር ከጎጃም ሲሮጥ ከመጣው ምስኪኑ የእንቁላል ፋብሪካ ልጅ በስተቀር ሁሉም የቀን ሠራተኞች ኦሮሞኛ ተናጋሪዎች ናቸው፡፡ ለካ ድንገት ሰርጎ ከገባው ከዚህ ምስኪኑ ባለታሪክ በቀር ሁሉም ሠራተኞች ድሃ የኦሮሞ ልጆች ናቸው፤ ይሄ ደግሞ የሆነው ዋና ተቆጣጣሪ ተብየው ኦሮሞ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ቀን በኋላ በዚህ ባለታሪክ ላይ ሁኔታዎች በፍጥነት መቀያየር

> ...እኛ ኢትዮጵያዊያን በደም መደባለቃችን፤ በስጋ ሀረግ መተሳሰራችን ክፉ ቀንን ማሸገር የማይችል ሆኖ ይኸው ላለፉት ብዙ ክረምትና በጋዎች ሲሰራ የነበረው “ስጋን-ከስጋ የሚያቆራርጥ” የፖለቲካ ደባ ሰለባዎች መሆን መጀመራችን በአደባባይ እያየን፤ እየሰማን ነው...

ቀጠሉ፡፡ “የእኔ በኦሮሞዎች መካከል መገኘት የከነከነው አለቅየው ፊቱ እየተለወጠብኝ ሄደ ይላል ባለታሪኩ ፡፡ ይለይልህ ብሎ ነው መሠል ተመሳሳይ የሽቀላ ስራ እየሠራን ለእኔ ከሚከፈለው መቀነስ ጀመረ፡፡ የቀነሰብኝ ብር ወገኖቼ ለሚላቸው ልጆች እየጨመረ ሲከፍላቸው በአይኔ-በብሌኑ ያዝኹት” እያለ እንባ በአይኖቹ ቆብ ዙሪያ እየቋጠሩ፣ እልህ እየተናነቀው አጫወተኝ፡፡

## እና ምን ወሰንክ አልኩት?

የዚህን ጥያቄ መልስ በስተመጨረሻ እንመለስበት፡፡

ልብ በሉ ጎበዝ! እንግዲህ ይሄ ታሪክ የሆነው ከዓለም ስልጣኔ ርቀው ካሉት በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ቀበሌዎች ውስጥ አይደለም፤ ከዚሁ መሀል አዲስ አበባ እንጂ፡፡ የበቃ-የነቃ ንቃተ ህሊና ማህበረሰብ አለበት በምትባለው “አራዳ ዘር የለውም” በሚባልላት ታላቋ አዲ’ ሳቤ ውስጥ ነው፡፡ እንግዲህ እናት አገር ኢትዮጵያ ከዚህ ደርሳለች፡፡

እኛ ኢትዮጵያዊያን በደም መደባለቃችን፣ በስጋ ሀረግ መተሳሰራችን ክፉ ቀንን ማሸገር የማይችል ሆኖ ይኸው ላለፉት ብዙ ክረምትና በጋዎች ሲሰራ የነበረው “ስጋን-ከስጋ የሚያቆራርጥ” የፖለቲካ ደባ ሰለባዎች መሆን መጀመራችን በአደባባይ እያየን፤ እየሰማን ነው፡፡ እንዲህ ኢትዮጵያዊነት “አፈር-ድሜ” ገብቶ ሀገር ጭንቅ - ምጥ ውስጥ ሆና ስትንቦጫረቅ የፓን አፍሪካን’ ፍልስፍና ስታቀነቅን የነበረችውና የአፍሪካዊያኑ ኩራት የሚሏት ኢትዮጵያ፣ እንኳንስ ለአፍሪካውያን ቀርቶ የራሷን ልጆች በአንድ የኢትዮጵያዊነት ሐረግ ማስተሣሠር አቅቷት በዓለም አደባባይ ስትታማ ስንሰማ፤ ቀደም ሲል በታዘብነው በካቦው አይነት መንደርተኛ አስተሳሰብ ሀገሪቱ ተጥለቅልቃ፤ በማንነታችን የምንሰፋፈር እና ትንሽና ትልቅ ብሔር በሚል ትልቅን ሃገር ወደብዙ ትንንሽ መንደሮች ለማሸጋገር በፖለቲካ ድር የምንጠላለፍ ዜጎች ሆነን ሀገር ስትጨነቅ፣ አዎ! በዚህ ሰዓት ሀገር ሰው ያስፈልጋታል፡፡

ኢትዮጵያዊነት ተቆርጦ ሊጣል ከስሩ-ከመሰረቱ ‘በብሔርተኝነት’ ስለት እየተገዘገዘ ባለበት በዚህ የመአት ሰዓት፣ በፖለቲከኞቻችን መንደር ዙሪያ፤ በቤተ-መንግስቱ ቅፅር አካባቢ ይደረግ የነበረው የብሔር ፖለቲካ የቁማር ጨዋታ እንዲህ ወደታችኛውና ለአንድ ሃገር ህልውና መሆን የመጨረሻ ወሳኝ በሆነው ሰፊው ህዝብ ውስጥ ብሔርተኝነት ሰርሰሮ ገብቶ አንዱ በሌላው ጣት መቀሳሰር ከጀመረ ሃገር እየጠፋች ለመሆኑ ትልቁ ምልክት ነው፡፡ በዚህ ሰዓት ሀገር ሰው የሆነ “ሰው” ትፈልጋለች፤ “ኢትዮጵያዬ ብረሳሽ ቀኜ ▶

▶ ትርሳኝ" የሚለውን ወርቃማ ሐረግ ከስርቻው ስር አውጥቶ፣ በአደባባይ ብቅ የሚል "ጀግና" ሰው፤ ስር በሠደደና ጽንፍ በሌለው የሀገር ፍቅር ስሜት/ምክንያት/ እነሱው ሞተው "ኢትዮጵያን" ባፀኗት የቀደምት አርበኞች መንፈስ የሚነሳ "የቁርጥ ቀን" ልጅ በባትሪ እያሳሰች ነው እናት ሀገር ኢትዮጵያ፡፡ የኢትዮጵያን ወርድና ቁመት የሚያሳንስ ሲገጥም፣ ታላቁን የሀገር ምስል የሚያደበዝዝ ጉድ ሲከሠት ጀግኖች ከጥልቅ እንቅልፋቸው፤ ከግዙፍ ዝንጋኤቸው ነቅተው ልትወድቅ ያለችውን ሃገር ተረባርበው እያነሱ፤ ልትፈርስ ያለች ኢትዮጵያን ሆ ብለው እየሰሩ ነው ከዛሬ ያደረሷት፤ ሀገር እውነተኛ ልጇን ለይታ በምታውቅበት፣ ባንዳና አርበኛዋን በምትለይበት ሰዓት "ኢትዮጵያዬ ብንረሳሽ ቀኝ ትርሳን" ብሎ መነሳት ግድ ይላል፡፡

ከፋሽስት ወገን ያልሆኑ፤ ከኢትዮጵያዊነት ጋር ግን የተኳረፉ፣ ኢትዮጵያዊነት ከማንነት አይበልጥም ብለው ታጥቀው በተነሱ ፖለቲከኞቻችን ምክንያት ውጥንቅጥ ውስጥ የገባውን ብሔራዊ አንድነታችንን አጽንተን ወደቀጣዩ የትውልድ ጅረት ሳይቋረጥ እንዲፈስ ለማድረግ በአደባባይ "ኢትዮጵያዬ ብንረሳሽ ቀኝ ትርሳን" ብለን የምንነሳበት "ፔሬድ" ላይ መድረሳችን መራራ ሀቅ እየሆነ ነው፡፡ ብቻ በጀግና አርበኛ ልጆቿ ቆራጥነት ይሁን ወይ በማናየው ስውር መለኮታዊ እጅ፣ ይህች ሃገር ተጥላ አትጣልም፡፡ በተለያዩ ዘመናት ከሚመጣበት ሰው ሰራሽ "መቅሰፍት" ኢትዮጵያ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ ብለው ቆርጠው በሚነሱ /በተነሱ/ ተቆርቋሪ ልጆቿ ምክንያት፤ ከዚያ 'መቅሰፍቷ' በትአምር እየዳነች 'ሃገር የመሆን' ልምምድን አዳብራለች፡፡ ይታወቃል፤ በተለያየ ትውልድ ውስጥ ከውጭም-ከውስጥም ከሚነሳባት መከራ ጋር ግብግብ ገጥማ 'ሀገርነቷን' ጠብቃ የቀጠለችው እናት ሃገር ኢትዮጵያ፤ በተለይ-በተለይ ደግሞ ከ1928 —1933 ዓ.ም የነበረውን ኢትዮጵያን ለማዳን የተደረገውን ያን የጀግንነት ዘመን ታሪክ ወደኋላ ሄደን ማስታወስ ይህን ሀሣብ ያጠነክርልናል፡፡ በጣሊያኖች ተመልሶ መምጣትና በንጉስ ነገስታችን ስደት / አንዳንዶች ለትህትናው ሲሉ የአውሮፓ ጉብኝት ይሉታል/ መካከል ያለው የሃገራችን ብሔራዊ ሁኔታ አሁን ካለችው ኢትዮጵያ ጋር በዘመን እንጂ በሁኔታ ይመሳሰላል፡፡ መቸም ያ የአምስት አመታቱ የሮማውያን ዕድሜ ትንሽ ተራዝሞ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ያለችው ኢትዮጵያ ፈፅሞ እንደማትኖር ለማወቅ፤ ያኔ የሞሶሎኒ እንደራሴዎች ኢትዮጵያን ለማስተዳደር አንጠልጥለው ያመጡትን "ሜኒፌስቶ" ማየት በቂ ነው፡፡

አንድ ማኅበረሰብ /ሃገር/ ለዘላለም በአንተ ጫማ ስር እንደወደቀ እንዲቀር በማኅበረሰቡ መካል ስንጥቅ ፈጥረህ ከፋፍለህ ግዛው የሚለውን የቅኝ ገዢዎች ፍልስፍና ይዘው የመጡት የፋሽስቱ ልዑካን፣ በብሔር እና በሃይማኖት የተከፋፈለች ኢትዮጵያን አፍርሶ ለመስራት ገና በጥዋቱ "ተፍ-ተፍ" ማለትን እንደጀመሩ፤ "ኢትዮጵያዬ ብንረሳሽ ቀኝ ትርሳን" ብለው ከተነሱ የቁርጥ ቀን ልጅ ከሆኑ ኢትዮጵያውያን ጋር የገጠማቸውን ግብግብ ታሪክ አሳምሮ አስቀምጦታል፡፡

የዓድዋውን ሽንፈት ሊያወራርዱ አስል ተው የመጡት የጣሊያን "ሶልዳቶዎች" ሃገር ሊከፋፍሉ ሲሮጡ መድረሳቸው ከገባቸው ኢትዮጵያውያን አርበኞች ሳይውሉ ሳያድሩ ነበር ንቅናቄ የጀመሩት፡፡ ከንጉስ ነገስቱ ሠራዊት ጋር እንደዬው ለአመል ያክል በውጫሌ በኩል በመታኮስ በዙም 'ክፉ' ሣይገጥመው ምኒልክ ቤተ መንግስት ሰተት ብሎ የገባው የጣሊያን ጦር፤ የንግስና ቆይታው 'የዛፍ ላይ እንቅልፍ' አይነት ነገር ነበር የሆነበት፡፡ ኢትዮጵያን ከመፈራረስ የታደጉት ዘመኑ ያበቀላቸው አርበኞች ጀብዱ መቸም የሚረሳ አይደለም፡፡ የቻለ፣ ከፊት-ለፊት ቦንብ እየወረወረ፣ ያልቻለው በየክፍለ-ሀገራቱ በደፈጣ ውጊያ ጣሊያኑን ምቾት በመንሳት፣ ጣሊያን ሆየ "እግሬን በሰበረው" ብሎ በመጣበት እግሩ ወደ ሃገሩ እንዲፈረጥጥ የተገደደው በነዚያ የቁርጥ ቀን አርበኞች ነው፡፡

እናም ያለማንም ቀስቃሽ፤ ያለንጉስ ትዕዛዝ፤ ራሱ ወታደር-ራሱ የጦር አዋጊ ሆኖ ኢትዮጵያን ከፋፍለው ሊገዙ ከመጡት የሞሶሎኒ አሽከሮች ጋር ትንቅንቅ የገጠሙት አርበኞቻችን፤ ጣሊያንን ከምኒልክ ቤተ-መንግስት ገፍትረው፤ የእናት ሃገር ኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ በክብር አውለበለቡት፡፡ በሮማ ፖለቲከኞች እና በአንዳንድ ባንዳ አሻጥር ምክንያት ልትጠፋ የነበረችን ኢትዮጵያ "ከአንቺ በፊት እኛ" ብለው በመነሳት ከቅኝ ገዥ ጦር "ነፃ" አውጥተው የኢትዮጵያን እድሜ የቀጠሉ…

ከፈረሰኛው ባልቻ አባ ነፍሶ እስከ በርኸኛው በላይ ዘለቀ፣ ከመንዜው ሀይለማርያም ማሞ እስከ ባላንባራስ ራስ አበበ አረጋይ፤ ከትግሬው ጦር አዝማች ራስ ካሳ ኃይሉ እስከ ደብረሊባኖሱ አባት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፣ ከዮጎዝላቪያዊው አዶልፍ ፓርል ሳክ እስከ የአብ-ዳህላኩ ልጅ አብርሃ ደቦጭ ድረስ ለእኛ ብሔራዊ አንድነት በጀግንነት የሞቱ የቁርጥ ቀን ልጆች ናቸው፡፡ አዎ ሀገር አስታዋሽ በፈለገችበት ጊዜ፤ ሀገራቸውን ያስታወሱ፣ ሀገር ያልረሱ "ብንረሳሽ ቀኝ ትርሳን" ብለው ሃገር የታደጉ ብሔራዊ ጀግኖቻችን ናቸው፡፡ ወደ አሁኗ፤የዛሬዋ ኢትዮጵያ ስንመለስ ከጣሊያን የዳግም ወረራ ዘመኗ ኢትዮጵያ ጋር ትቀራረባለች፤ በዚህ እውነታ ስለተማመንን፤ ያው ልክ እንደዛንጊዜዎቹ አይነት ስለኢትዮጵያ አንድነት የሚነሱ ጀግኖች እንደሚያስፈልጉንም እግረ መንገዳችንንን እንስማማለን ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ከቅኝ ገዢዎቻችንን ባልተናነሰ መጠን፣ ሊከፋፍለን ታጥቆ የተነሳብንን የዛሬውን የብሔር /የአካባቢያዊነት ፖለቲካ/ በቡቃያው ዕድሜ ካልታረመ ከአመታት በኋላ ኢትዮጵያ የምትባለው ሃገር ብዙ ሀገር መሆኗ አይቀሬ ጉድ ነውና፡፡ አሁን፤ በተጨባጭ የምናይ- የምንሰማቸው የብሔርተኝነት በሽታዎች /ምልክቶች/ ወደዛ ስጋት እያንደረደሩን ነው፡፡ እስኪ የባለታሪኬን የመጨረሻ መልስ እንስማ

## "እና ምን ወሰንክ?" አልኹት

"እውነቱን ልንገርህ፤ በማንነቴ ተንቄ፣ ጠግቤ ከማድር፣ ማንነቴን አስከብሬ ጦም ባድር እመርጣለሁ፡፡ እንዴት አማራ፣ ኦሮሞ እየተባለ ከአንተ ደምዎዝ እየተቀነሰ ለሌሎች ሲከፈል እያየህ ልትሰራ ትችላለህ? የማላውቀው የብሔርተኝነት ዘር ነው የተዘራብኝ፤ ልቤን አመጸኛ አድርገውብኛል " አለኝ፡፡

ከዚህ በላይ መናገር አልቻለም፤ የሆነ እንባ አይሉት እልህ ነገር ከደረቱ ሾልኮ ሲወጣ ከአፉ በሚወጡት የተቆራረጡ ቃላት ማወቅ ይቻላል፡፡ እንዳለውም ይሄ የብሔር ሰላባ የሆነው የቀን ሰራተኛ፣ ያንን ስራ እርግፍ አድርጎ ትቷታል፣ ዛሬ ስራ የለውም፡፡ አራዳ ጊዮርጊስን አጥሮ በያዘው ረጅሙ የድንጋይ ግንብ ላይ ቁጭ ብሎ፣ ፒያሳን ቁልቁል እያየ ሲተክዝ ይውላል፤ሲመሽ ጥጉን የእግረኛ መንገድ ይዞ፤ሁለት እጆቹን ወደኋላው አቆላልፎ ወደእንቁላል ፋብሪካ ያዘግማል፡፡

ይሄን አይነቱ እንደዋዛ እየተለማመደን የመጣው ሃገራዊ ትራጄዲ እንደ ትንሽ፣ ተራ ገጠመኝ አድርጎ የሚያስብ ካለ፤ ውስብስቡ የፖለቲካ ሴራ /የብሔር ፖለቲካ የመጨረሻ ግብ/ ገና ያልተገለጠለት ቅን ዜጋ ነው እላለሁ፡፡ ምክንያቱም ወደዛ ወደምፈራው የነገው ሃገራዊ /ብሔራዊ ውድቀት/ የሚያደርሱን እንደዚህ ዓይነት ትንንሽ ብሔር ተኮር ቁርቋሶሽ ተቀጣጥለው ነውና፡፡ እንጂ ሃገር ደርሳ በአንድ ፀሐይ እኮ ልትፈርስ አትችልም፡፡ እንደዚህ ዓይነት በየማሕበረሰቡ የዕለት-ተዕለት ሕይወት ውስጥ የሚፈጠሩ እንደ ባለታሪኬ አይነት ቁርስራሽ መጠቃቶች ግን፤ በህዝቡ መካከል የቂም እርሻውን እየጣለ ቆይቶ፣ "መጠቃቱና ማጥቃቱ" አይን እያወጣ ሄዶ የኢትዮጵያዊነት ግንዱን ከስሩ ፈንቅሎ /መንግሎ/ ይጥለዋል፤ ራሱ ህዝቡ… እርስ-በርሱ፡፡

ምክንያቱም የሠው ልጅ ማንነቱ እየተገፋ፤ በማንነቱ ክብር እያጣ በሄደ ቁጥር ያ ሃገራዊ /ኢትዮጵያዊነት/ ፍቅሩ እየደበዘዘ… እየደበዘዘ ሄዶ የራሱን ማንነት" /ብሔሩን/ ወደ መከላከል ዝቅ ይላል፡፡ እንግዲህ ከትልቁ ሃገራዊ ማዕቀፍ ወጥቶ ሰው ማንነቱን ወደመመከት ሲሸጋገር ያኔ ሃገር እየጠፋች ለመሆኑ ሀቅ ነው፡፡ ስለዚህ ሃገር አደጋ ላይ ናት ብለን እንመን ጎበዝ፡፡ ለግል የፖለቲካ ግባቸው ሲሉ የክልላዊነት ፖለቲካ በህዝባቸው ላይ በመጫን፣ አንዲትን ሃገር ወደ ብዙ ሃገርነት የቀየሩ ሀገራት መጥፎ ልምድ ገለጥ አድርገን ስናይ፤ እነዛ ሀገሮች ከመለያየታቸው በፊት ያሳዩትን የነበረው ምልክት በኢትዮጵያ ምድር ላይም እያየን ነው፡፡

ዛሬ በመከፋፈል ለሚያምኑ ጥቂት ኢትዮጵያዊያንን ይበልጥ አንድ ስንሆን፤ ይበልጥ ታላቅ ህዝብ እንሆናለን የሚለውን ፀረ-ዘረኛ አቋም በማቀንቀን የትውልድ ባላደራነታችን ልናሳይ እነሆ ሰዓቱ ቀርቧል፤ አስታዋሽ አጥታ ገደል አፋፍ ከጠርዙ ላይ የቆመችውን ሃገር፤ ወድቃ ሳትንኮታኮት ደርሰን ኢትዮጵያዊነትን እናድነው ዘንዳ ይሄው ከፈተናው ፊት - ለፊት ተጋፍጠን ቆመናል፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በብሔር ካፖርቱ ውስጥ ሽብለል ብሎ እንዲገባ እየተደረገ፤ በአንድነት የሚያምኑ ፖለቲከኞችን ፊት ለፊት በማይታይ ስውር ዘዴ እንዲገለሉ ሲደረግ እያስተዋልን፤ ጊዜ /ፀሐይ/ የወጣላቸው ብሄርተኞች ኮረኮንች እየተጠረገላቸው ሃገሪቱ ላይ ሰሪ - አፍራሽ እንዲሆኑ እየተሰራ፤ ከምንም በላይ ደግሞ ሃገር እየመራ ያለው አካል ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ የብሔር ፖለቲካ አፍቃሪ ስብሰብ መሆኑን በተግባር እያስተዋልን ፤ በዚህ ሰዓት "ኢትዮጵያዬ ብንረሳሽ ቀኝ ትርሳን" ብሎ አለመነሳት ሃገርን ለመከፋፈል ቆርጠው ከተነሱት ጎን ከመሰለፍ አይተናነስም፡፡


# የአክሊሉ ለማና የካሳሁን ግርማሞ ትውስታ



ፋንታሁን ኃይሌ



ዶ/ር አክሊሉ ለማ



ጋዜጠኛና የመድረክ አስተዋዋቂ ካሳሁን ገርማሞ

ብዙዎቻችን አጥፍተን ወይም በድለን ይቅርታ መጠየቅን፣ በጎ ስራ ተደርጎልን ወይም ውለታ ተሰርቶልን አመሰግናለሁ ማለትን፣ እንዲሁም ለየት ያለና ከሌሎች የተሻለ ስራ የሰራን ሰው ማድነቅን አናውቅበትም፡፡ ልምዱም የለንም፡፡ ግን ሁሉም ልንለምዳቸው የሚገቡ ነገሮች ናቸው፡፡

ዛሬ ምስጋና ስለሚገባቸው ሁለት ሰዎች ጥቂት ላውጋችሁ፡፡ ስለ እነኚህ ሰዎች የማስነብባችሁ በምርጫ ወይም በብልጫ ሳይሆን፤ ገጠመኞችም ስላሉኝ ነው፡፡

ጊዜው ስለረዘመ ትክክለኛውን ዓመትና ቀን ባላስታውሰውም በስራ ብዛት ላገኛቸው ባለመቻሌ ቅር ሲለኝ ኖሮ፣ ዶክተር አክሊሉ ለማን መንገድ አገጣጠመኝ፡፡

የተገናኘነው በኢትዮጺያ አየር መንገድ አውሮፕላን አብረን ለመጓዝ ሻንጣችንን ግራና ቀኝ ካለው የቦርሳ ማስቀመጫ፣ እቃችንን ቦታ ለማስያዝ በምንጥርበት ጊዜ ነበር፡፡ ታዋቂ ሰው የሚያውቁትን ላያውቅ ስለሚችል ከተገቢው ክብር ጋር ሰላምታ ሰጠኋቸው፤ ወንበር መርጠው አረፍ ሲሉ እጎናቸው ሄጄ ተቀመጥሁኝ፡፡ የጋዜጠኛነት ስራዬ ተገቢ ጥያቄ ለመጠየቅ ድፍረቱን ስለሰጠኝ ወዴት ነው የሚጓዙት? በማለት ጠየቅኋቸው፡፡ ሽልማት ለመሸለም ወደ ስዊድን እንደሚጓዙ ገለጡልኝና አንተስ? በማለት ጠየቁኝ፡፡

እኔ ጣልያን፣ስዊዘርላንድና ፈረንሳይ እንደምጓዝ ገልጬላቸው ታዋቂ ባልሆንም በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ እንደተሰማራሁ አስረዳኋቸው፡፡ "ይህንን ስም አውቀዋለሁ፤ ምን ገጽ ላይ ነው የምትጽፈው?"፤ አሉኝ፡፡ በስፖርት እና ሌሎች አምዶች ላይም እጽፋለሁ፤ ስላቸው "ስፖርት ስለምወድ የስፖርት ገጽን በምርጫ ነው የማነበው" የሚል ምላሽ ሰጡኝ፡፡ ጎን ለጎን ተቀምጠን ለ 5 ሰአት ያህል አብረን ተጓዝን፤ ፋታ ሳልሰጣቸው ነበር የደረስነው፡፡

ብዙ ነገር አጫውተውኝ አደራ ያሉኝ ነገር፣"እኔ ወደ ሀገሬ ሳልመለስ የነገርኩህን ጋዜጣ ላይ እንዳታወጣው" የሚል ነበር፤ ቃሌን ጠበኩኝ፡፡

ስለ ኢትዮጺያዊያነት፣ ስለ አንድነት ስለ ወገንና ሀገር ፍቅር፣ ስለ ሃይማኖት ስለ ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር፣ ስለ አባቶቻችንና ስለእናቶቻችን ጀግንነት፣ ስለ ኢትዮጵያ ልሂቃን (በሃይማኖትና በዘመናዊ ትምህርት) ስለ ስፖርት ጀግኖቻችን አንስተው በሰፊው አጫወቱኝ፡፡ በተለይ በተለይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሽልማት የሚያገኝ ሰው ሽልማቱ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለሃገሩ ጭምር ስለ መሆኑ፡፡

"ለምሳሌ በአንድ ኢንተርናሽናል መድረክ እኔ ለመሸለም ስጋበዝ፣ ወደ ሽልማቱ መድረክ የምጠራው Doctor Aklilu Lemma Scientist from Ethiopia (Africa) ( ዶክተር አክሊሉ ለማ ከኢትዮጺያ በመባል ነው)

ሀገርህን ውደድ! ወገንህን ውደድ! እናት ልታስቀይምና ልታስከፋ ትችላለች፣ ሀገርና ወገን ሊያስቀይሙና ሊያስከፉ፣ ባጠቃላይም ላይመቹ ይችላሉ፡፡በግልህ አስቀይመውኛልና አልተመቹኝምና፣ ለእኔ ስላልሆኑኝ ብለህ ሀገርህንና ወገንህን ፈጽሞ መክዳት የለብህም፡፡ በሰው ሕይወት ጣልቃ አትግባ፣ያለህን እያካፈልክ ኑር፡፡ ታዋቂ ለመሆን ብትችል እንኳን አንገትህን ደፍተህ፣ ተደብቀህ ኑር፡፡ እግዜር ለሰጠህ ችሎታ ለመታበይ አትሞክር፡፡" በማለት እየመከሩኝ እና ልምዳቸውን እያካፈሉኝ፣ሳናውቀው ሮም "ሊኦናርዶ ዳቬንቺ" አውሮፕላን ጣቢያ አርፈን፣ ቦርሳዎቻችንን ይዘን ወደ ላውንጁ በመሄድ ካፑችኖ ጠጥተን፤ መልካሙን ሁሉ ተመኝተን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተለያየን፡፡

ዛሬ ስለ ሳይንቲስት አክሊሉ ለማ ያነሳሁላችሁ፣ እኛ ኢትዮጺያዊያን በሁሉም ረገድ ሃገራችንንና ወገናችንን ማድነቅና ማመስገን እንደምናውቅበት ለማሳየት ነው፡፡

የቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) አባት ካሳሁን ገርማሞ፤ጥሩ ወዳጄና መካሪዬ እንደነበር ያለ ዛሬ አላነሳሁትም፡፡ በ1981 ዓ.ም አስኳል ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 መጻሕፍትን ጽፌ በነበረበት ወቅት፣ ለሰው ልጅ በጎ ይመኝ የነበረው ካሳሁን ገርማሞ፤ ስለ መጽሐፍቶቹ ተወዳጅነት እና በህዝብ ዘንድ ስላላቸው ተቀባይነት ከነገረኝ በኂላ እንዲህ አለኝ፡፡

"በህይወት ውስጥ ሀብት ወይም ገንዘብ ሲገኝ አብሮ የሚመጣ ነገር አለ፡፡ይህንን ማንም ላይነግረህ ይችላል፡፡ እኔ ግን እነግርሀለሁ፡፡ ለምሳሌ እከሌ፣እከሌ፣እከሌ ገንዘብ እና ዝና እንዳገኙ ነው ሳይበረክቱ ወዲያው ታይተው የጠፉት፡፡ አንዳንድ ጊዜ (ካላወቁበት) ገንዘብ አጥፊ ነውና ባይገኝ ይሻላል" አለኝ፡፡ የዚያ ዕለት ከቢሮ ወጥተን ቱሪስት ሆቴል ምሳችንን በላንና ማክሰኞ ምሽት የሚካሄደውን ጨዋታ ለማየት ወደ ስታዲየም ሄድን፡፡

በዚያው ሰሞን በአንዱ ቀን ሃይለኛ የራስ ህመም ገጠመኝ፡፡ ትክክል ልሁን አልሁን አላውቅም፤ የራስ ህመም የሌላ የሰውነት ክፍል ህመም ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ በሃይል ሲያመኝ እና ካስሽ ያስጠነቀቀኝ ትዝ ሲለኝ ሜክሲኮ ወደሚገኘው የፖሊስ ሰራዊት ዋና መምሪያ ሄድኩኝ፡፡

በነገራችን የኢትዮጵያ ፖሊስ ሰራዊት የሚል ጽሁፍ ያለበት ምርጥ የስዊዝ ሰዐት በጋዜጠኝነት ተግባሬ፣ ከሰራዊቱ ዋና አዛዥ ከጀነራል ወርቁ እጅ (ነብሳቸውን ይማር) ተሸልሜ ነበርና የሰራዊቱ ቤት፣ ቤቴ ነበር፡፡

እዚያ እንደደረስሁ ወደ ካሳሁን ቢሮ ከመግባቴ በፊት ታላቅ ወዳጄን ጀነራል ወርቁን ሰላም ለማለት (ለነገሩ ስታዲየም በየጊዜው እንገናኛለን) ወደ እርሳቸው ቢሮ ጎራ አልኩኝ፡፡ ዛሬ ታላቅ ኢንቬስተር የሆነው ለጋሱና ትሁቱ፣ ፈገግታ የማይለየው ባለውለታዬ ሀለፎም ፍጹም ጸሀፊያቸው ነበርና ከእርሱ ጋር ተጫውቼ፣ ተራዬን ጠብቄ በመግባት ሰላምታ አቅርቤ ወጣሁኝ፡፡ ወደ ካሳሁን ገርማሞ ቢሮ ሄድኩኝና አብረን በመውጣት ወደ ፍልውሀ ሆቴል ጎራ ብለን እየተጨዋወትን ባለንበት ወቅት "ራሴን አሞኛል፣ አተኩረህ አይተህኝ ነበር እንዴ?" ስለው፤ "አንተ ምንህ ላይ ይተኮራል? አንተን አይቼ… በመልክ እኔ እበልጣለሁ! እበልጣለሁ!" ስንባባል ቆይተን፤ባለፈው የነገረኝ አሳሰበኝና "ያልከው ሊሆን ነው እንዴ? ራሴን ያለማቋረጥ ያመኛል" አልኩት፡፡

"ቦካህ? እኔ እኮ ጀግና ትመስለኝ ነበር " ካለኝ ▶

በኋላ፤ ወደ ፖሊስ ሆስፒታል ሄደን ምርመራ አደረግሁኝ፡፡ ዶክተሩ በምርመራ ያገኙት ህምም እንደሌለና ደሜ በመጠኑ ከፍ እንዳለ ገለጡልኝ፡፡ ምን ምን እንደምበላና እንደምጠጣ ጠየቀው ጨውን እንድቀንስ፣ ከቻልኩ ጨርሼ እንድተው መከረውኝ፤ አመስግኜ ተለያየን፡፡ ካስሽ እና እኔ በወዳጅነት ስነበትን፤ እርሱ ቤት የፈረምኩባቸው መጻሕፍቶቼ በክብር እንደተቀመጡ ይነግረኝ ነበር፤ የዛሬውን አላውቅም፡፡ ነብስ ይማር፡፡

አባቶቻችን "ከእኔ አልፎ ለሀገርና ለወገን የሚበቃ ልጅ ስጠኝ" ብለው ይመርቃሉ፡፡ ይህ የእኔም የዘወትር ጸሎት ነው፡፡ ልጅ መውለድ ብቻውን ለሀገርና ለወገን የሚበጀው ነገር የለም፡፡ በስነ-ስርዓትና በትምህርት ኮትኩቶ በማስመረቅ፣ልጁን ያበረከተ ቤተሰብ እንደተመሰገነና እንደተመረቀ ይኖራል፡፡ ለሃገር ሽክም "ሆያ ሆዬ" ባይ፣ በመንጋ የሚነዳና በቤተሰቡ በወገኑና በሃገሩ ላይ በደል የሚፈጽም ልጅ ወልዶ አልጣለምና ምስጋና ሲያንሰው ነው፡፡

ተወዳጁ ጋዜጠኛ፣የመድረክ መሪና ገጣሚ ካሳሁን ገርማሞ እንደልፋቱና እንደጥረቱ ሳያገኝ ቢያልፍም፤ ቴዎድሮስ ካሳሁንን (ቴዲ አፍሮን) ከኢትዮጵያ አልፎ፣ በመላው ዓለም ለሚኖሩ ኢትጵያዊያን ወገኖቹ አበርክቶ አልፏልና ስሙን ሳነሳው ኩራት ይሰማኛል፡፡

## ወደ ተበረከተልን ታላቅ ልጅ እንመለስ

ሰዎች ታሪክን ይሰራሉ? ወይስ ታሪክ ሰዎችን ይፈጥራል? ሊያወያይ የሚችል ነው፡፡ ከላይ ነው ትዕዛዙ፣ "ከላይ ነው ሥጦታው" እንዲሉ ቴዲ ተሰጥቶናል፡፡ ከካሳሁን ገርማሞ ጣሪያና ግርግዳ ውስጥ የተፈጠረው ቴዲ ከዚያች ቤት፣ ከዚያች ሰፈርና አካባቢ፣ ከዚህች ከተማ፣ ከእናት ሃገራችን ኢትዮጵያ ይገኛል ብሎ የጠበቀ አልነበረም፡፡

ቴዎድሮስ ካሳሁን ፖለቲካ ነው፤ ኢኮኖሚ ነው፤ ማህበራዊ ኑሮም ነው፡፡ ድምጻዊ፣ገጣሚ፣ዜማ ደራሲ ከራሱ አልፎ ለሌሎች ዜማና ግጥም የሚሠጥ፣ ለችግር ደራሽ አይዟችሁ ባይ!

አርቆ አሳቢ፣ለሀገሩና ለወገኑ ሟች መሆኑን ዕድሜ ሰጥቶኝ ማየት በመታደሌ ካሳሁን ገርማሞን መውደዴን ወደድኩት፡፡

ቴዎድሮስ ካሳሁን ሰሞኑን እንደተባለለት፣ የኢትዮጵያ ሙዚቃ አልጋ ወራሽነቱን በሚያረጋግጥ መልኩ በአንድ ወር ውስጥ ሁለት ክብር ያላቸው ታላላቅ ሽልማቶችን ለመሸለም በቅቷል፡፡

በአትላንታ ከተማ የሚገኙ የሚዲያና የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ባዘጋጁት የሽልማት ስነ-ስርአት ላይ፣ በሙዚቃ ዘርፍ ለሃገሩ ለወገኑና ለሰው ልጆች ባበረከተው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሽልማት ተበርክቶለታል፡፡

ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የከተማዋ ከንቲባ ጽህፈት ቤትና የሞንቶጎሞሪ ራስ ገዝ አስተዳደር ጽህፈት ቤት በጋራ ባዘጋጁት የአፍሪካ ተጽእኖ ፈጣሪዎች የሽልማት ፕሮግራም ላይም ቴዎድሮስ ካሳሁን ተሸላሚ ሆኗል፡፡

ቴዎድሮስ ካሳሁን በሰራቸው ስራዎች በሃገር ውስጥና በውጭ ሀገር መሸለም የጀመረው ዛሬ ባይሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ በዚህ መልክ እውቅና አግኝቶ መሸለም መቻሉ ወጣት ስለሆነ ለወደፊቱ አያሌ ስራዎችን እንዲሰራ ከፍተኛ መነሳሳትን ይፈጥርለታል ብዬ አስባለሁ፡፡

እውነት ለመናገር መውለድ እንስሳትን ጨምሮ አእዋፋት ሳይቀሩ በአካልና በእንቁላል ልጆች እየወለዱ ዘራቸውን ያስቀጥላሉ፤ ያባዛሉ፡፡ ቁም ነገሩ እንደ ካሳሁን ገርማሞ ያለ እናት ልጁን በጥርሱ አንጠልጥሎ፣ ከአባትነት ፍቅሩ የተነሳ በስርዓት አሳድጎ ለሀገርና ለወገን ጠቃሚ የሆነ፣ሁሉም የሚሳሳለት፣ በችሎታ የተሞላ ቁም ነገረኛ ልጅ ለማበርከት መቻሉ ነው፡፡ ካሳሁን ገርማሞ በህይወት ባይኖርም የኢትጵያዊያን ልጅ የሆነው ቴዲ በስራው በኢንተርናሽናል ደረጃ ተመርጦ ለመደነቅና ለመሸለም ሲበቃ የካሳሁን ገርማሞ አጥንትም ይለመልማል፡፡

ቴዎድሮስ ካሳሁንን ስለምንና ስለማን እንዳዜመ፣ ምን አይነት መልእክት ለማስተላለፍ ግጥሞቹን እንደጻፈና ስላገኘው ተወዳጅነት ብዙ ብዙ የተባለና የተጻፈ ስለሆነ በዛሬው ጽሁፌ ወደ ውስጥ መግባቴን በዚሁ ማቀብ እወዳለሁ፡፡ አባቱን ካሳሁን ገርማሞን በብዙ እጥፍ ደረጃ ተክቶታልና አበጀህ፣ እግዚሀብሄር ይባርክህ ልለው ግን እወዳለሁ፡፡

ሌላ ቁም ነገር ላንሳ፡፡ ቴዎድሮስ ካሳሁን አባቱን በብዙ እጥፍ ተክቶ፣ ከራሱ አልፎ ለሃገሩና ለወገኑ ዝናና ክብርን በማግኘት አለማቀፋዊ ሽልማት ተሸልሟል፡፡ ሌሎች ወጣቶችስ? የሃገራችን ወጣቶች እንደ ቴዲ የአባቶቻችሁን አደራ እየጠበቃችሁ፣ አባቶቻችሁን እየተካችሁ በሀገር ግንባታው፣ በልማቱና በሌሎች መስኮች እየተሳተፋችሁ ነው?

ወይስ በሞባይላችሁ ላይ ተጥዳችሁ፣ የአክቲቪስቶች ካዳሚ ሆናችሁ፣ ስልጣኔ መስሏችሁ የህልም እንጀራ በመብላት ላይ ናችሁ? አክቲቪስቱ አጭበርብሮም ቢሆን (እድሉ ከመቶ አንድ አይሞላም) ስልጣን ለመያዝ፣ ካልያዘለት ደግሞ ላይክ በሚያደርጉለት ሰዎች ልክ ገንዘብ ለመሰብሰብ፤ስልፉ፣ረብሻው፣ማፈናቀሉ ከቀጠለ፣ ግርግር ለሌባ ይመቻል ነውና በአጋጣሚው ድርሻውን ለመቦጨቅ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ወጥቶ ወርዶ፣ ጥሮ ግሮ ያፈራውን በከና በመንጋ ጉልበተኞች ዝም ብሎ አያይም፤ልብ ሊባል ነው የሚገባው፡፡ ህገ-መንግስቱን የማስከበር ቀጥተኛና ዋነኛ ሃላፊነት ያለበት መንግስት በአሁኑ ጊዜ ትእግስትን ራሱን መታገሱን ያቆመ መሆኑን በተግባር እያሳየ ነው፡፡

...እውነት ለመናገር መውለድ እንስሳትን ጨምሮ አእዋፋት ሳይቀሩ በአካልና በእንቁላል ልጆች እየወለዱ ዘራቸውን ያስቀጥላሉ፤ ያባዛሉ፡፡ ቁም ነገሩ እንደ ካሳሁን ገርማሞ ያለ እናት ልጁን በጥርሱ አንጠልጥሎ፣ ከአባትነት ፍቅሩ የተነሳ በስርዓት አሳድጎ ለሀገርና ለወገን ጠቃሚ የሆነ፣ሁሉም የሚሳሳለት፣ በችሎታ የተሞላ ቁም ነገረኛ ልጅ ለማበርከት መቻሉ ነው...

አያቶቻችን፣ አባቶቻችንና እኛ ጭምር የገነባናትን ሃገርና ያለማነውን ልማት፤ ከተወሰነ አካባቢ በጫት፣ በሀሺሽና በአረቄ እየነበዙ "እናፈናቅላለን፣ እንዘርፋለን፣ በሰው ድካም እንበለጽጋለን" በሚል እሳቤ ከተንቀሳቀሱ፤ በቅድሚያ ህዝቡ ከዚያም በአካባቢው የሚገኝ ፖሊስና በየደረጃው የተቋቋመ የመንግስት የጸጥታ ሃይል እንዳመጣጣቸው ይመልሳቸዋል፡፡ የእጃቸውንም ይሰጣቸዋል፡፡

አንድን ልጅ "እሳት እንደሚፋጅ" ቤተሰብ የማሳየትና የማስተማር ሀላፊነት አለበት፡፡ ቤተሰብ ግዴታውን ተወጥቶ፣ ልጁ እጁን እሳት ውስጥ ከከተተ ይኮማተራታል እንጂ ምን ይደረጋል?

የመንጋ ጉልበተኞች ሁኔታ ባብዛኛው ይመሳሰላል፡፡ መንግስት በእርግጥ የሽግግር ጊዜ ህግን ተግባራዊ ለማድረግና ዓለም እንዲፈርድለት ሲል በእጅጉ ትግስት አሳይ ቷል፡፡ ወንጀል አያረጅምና በጉልበተኞች መፈናቀል፣ስደት፣የአካል መጉደልና የሞት ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖቻችን ፍትህ እን ዲያገኙ ዘንድ መንግስት እንደጀመረው በየአ ካባቢው ወንጀለኞችን ለፍርድ ሊያቀርብና የእጃቸውን ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ አክቲቪስት ነን ባዮችን ጨምሮ ወንጀለኞም ለፍትህ መቅረብ አለባቸው፡፡

1. ህገ-መንግስቱን የማስከበር ሃላፊነትን ለመወጣት

2. የህግን ሉአላዊነት ለማሳየትና ሰላምን ለማስፈን

3. ማንም ማንንም የማፈናቀል፣የማሳደድ፣ ለጉዳትና ለሞት የመዳረግ መብት የሌለው መሆኑን ማሳየት

4. ይህን መሰሉ ነገር እንዳይደገም ማድረግ

5. ጥያቄን በተገቢው መንገድ አቅርቦ መልስ ማግኘት የሚቻል መሆኑን ማሳየት፡፡

ለማጠቃለል፤ ምድር እህል፣ አትክልትና ፍራፍሬን እንደምታፈራ ሁሉ እሾህና አሜኬላ ታበቅላለች፡፡ እነ ዶክተር አክሊሉ ለማንና ቴዎድሮስ ካሳሁንን የመሳሰሉ በችሎታም በሰብአዊነትም ተከብረው የሚያስከብሩ፣ ለሰው ልጆች እኩልነት፣ነጻነት፣ጤንነትና ሰላም የሚደክሙ ሰዎችን የምታፈራውን ያህል የሃገር ውስጥና የውጭ ሃገር አውደልዳይ አክቲቪስቶች በመንጋ እየጨፈሩ፣ በጉልበት የሰውን ንብረት ለመዝረፍ የሚሰማሩ ስራ ጠል ዜጎችን ትዕግስትን ከመታገስ ባለፈ ፈጥነው ሊማሩ ወደሚችሉበት ቦታ ልናሰማራቸው ይገባል፡፡

ወጣቶቻችን ለማን ነው መሰዕዋት የምሆነው? ማንንስ ነው ለማፈናቀል የምሰማራው? በማለት ቆም ብለው ራሳቸውን ሊጠይቁም ይገባል፡፡



# ድንበሩ እና CVዉ

ዳንኤል ካሣ

"ወራጅ... ወራጅ አለ" አለ ሃይገር ባሱ ዉስጥ ከታጨቀዉ ህዝብ መሃል ቆሞ እየተንጠራራ፡፡ አዉቶብሱ ቆመ፡፡ ድንበሩ ከመኪናዉ ወርዶ እግሮቹን ጣል ጣል ያደርግ ጀመር፡፡

ይህች ዕለት ከአራት ዳገትማ የስራ አጥነት አመታቱ የሚገላገልባት ዕለት ልትሆን እንደሚገባ ሲዝት ነበር የቆየዉ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አካዉንቲንግ ዲፓርትመንት በሚያስደንቅ GPA ከተመረቀ 4 ክረምቶች አልፈዋል፣ 4 በጋዎች ነጉደዋል፡፡ ስራ ፈላጊ ደግሞም አጥ ከሆነም እንዲሁ፡፡

"ጠና ይስጥልኝ፡፡" አለ ቀድሞ ያሰናዳዉን ዶሴ ወደ ሠው ሃይል አስተደደሩ እያስጠጋ፡፡ "ስራ ለመወዳደር ነበር"

ሓላፊው እጁን ዘረጋና "ስልክህን ፅፈኃል?" ሲል ጠየቀ

"እ... አዎ ሲቪዉ ላይ አለ፡፡" ድንበሩ ከወገቡ እጥፍ አለ፡፡

"መልካም፤ ና እዚች ላይ ፈርም፡፡"

ድንበሩ ፈጠን ብሎ ፊርማዉን አኖረ፡፡

"እ..." አለ ሰውየው ወደ ድንበሩ አንጋጦ፡፡ "ያዉ በስልክ ነዉ የምንጠራችሁ፡፡"

"እሺ፤ እሺ አመሰግናለሁ፡፡"

## የምዝገባዉ ቀን አለቀ

የ ሓላፊው ጠባብ ቢሮ እግር መርገጫ የላትም፡፡ ረጋ ብሎ ዙሪያ ገባዉን አሰሰዉ፡፡ የሲቪ ስጦሽ መአት፡፡ በጥቂቱ እያዛጋ የአመልካቾችን መዝገበ ስም ሰለለ፡፡ 624 ሰዎች ተመዝግበዋል፡፡

"ሆ... ይጌን ሁሉማ ሳመሳቅል አልከርምም፡፡" ፈጠን ብሎ አንድ ባዶ ወረቀት አወጣ፡፡ ከ6ትም ሸነሸነዉ፡፡ በዉስጡ "ቀላሉ መንገድ ይጌ ነዉ" እያለ ነዉ፡፡ 6ቱ ብጫቂ ወረቀቶች ላይ ከA-F ፃፈ እና ከወንበሩ ተነስቶ ቆመ፡፡ ዓይኖቹ ወለሉ ላይ ከተከመረዉ የCV መንጋ ላይ ናቸዉ፡፡ መንጋዉ በ6 ተከፋፍሎ ነበር የተከመረዉ፡፡ ጎንበስ ብሎ Aን አንደኛዉ ክምር ላይ አስቀመጠ፡፡ Bን ሌላኛዉ ላይ፣ ቀሪዎቹንም ሌሎቹ ላይ፡፡

ሲጨርስ ወደ ወንበሩ ተመልሶ ሌሎች ከA-F የሆኑ ፊደላትን ፃፈ እና ለየብቻ ጠቀለላቸዉ፡፡ ሁሉንም መፅሐፍ ላይ አስቀምጦ መፅፉን እንደ ወፍጮ ማበጠሪያ ያርገፈግፈዉ ጀመር፡፡ ‹‹እጣጣጣጣጣጣጣ...›› እያለ፡፡ በሌላኛዉ እጁም አንዱን አንስቶ ተረተረዉ፡፡ የተመረጠዉ ወረቀት ላይ የተፃፈችዉ ፊደል C ሆነች፡፡ ለፈተና የሚጠሩት ተወዳዳሪዎች በዚህችዉ ክምር ዉስጥ ያሉት ብቻ ናቸዉ፡፡ የድንበሩ ሲቪ B ክምር ዉስጥ ነበር፡፡ ሌሎች እጅግ አመርቂ ዉጤቶችን የያዙ ሲቪዎችም በሌሎቹ፡፡ ድንበሩ ስልክ አልተደወለለትም፤ ለፈተናም አልተጠራም፡፡

## አራት ወራት ነጎዱ

ድንበሩ ስራ አላገኘም፡፡ ቢሆንም ሲቪዉን ሌላ መስሪያ ቤት አስገብቶ እየጠበቀ ነዉ፡፡

"እ... በቃ እሺ የኔ ቆንጆ" አለ፤ ሓላፊው በረሃማ አናቱን በመዳፉ እያሻሸ፡፡ "አዎ... እሱን እቤት ስመጣ ብናወራ አይሻልም? አዎ፤ አዎ ቻዉ በቃ፡፡ እሙዋ፡፡" ስልኩን ከዓይኖቹ በር ለግቶ ፈገግ አለ፡፡ እጮኛዉን ለራሱም እስኪደንቀዉ ያፈቅራታል፡፡ በቅርቡም ይጋባሉ፡፡ ጥር 18 ይጋባሉ፡፡

ስልኩን አስቀምጦ ቢሮዉ ዉስጥ የተዝረከረከዉን የሲቪ መአት አስተዋለዉ፡፡ የዚህን ሁሉ ጠግቦ ያልበላ ስራ ፈላጊ ፎቶ ማየት እንደማይፈልግ ያዉቀዋል፡፡ ድንገት ከመቀመጫዉ ተስፈንጥሮ እየተነሳ "የስ" አለ፡፡ አንድ ሐሳብ መጥቶለታል፡፡ "የሰርጌ ለታ" ተመልሶ ቁጭ አለና የእጩዎችን የስም ዝርዝር የያዘዉን ወረቀት አወጣ፡፡ትኩረቱንም የስልክ ቁጥራቸዉ ላይ አደረገ፡፡

ሰርጉ በአስራ ስምንት ነዉ የሚከወነዉ፡፡ የስልክ ቁጥሩ ዉስጥ አስራ ስምንት ቁጥር ያለበት ስራ ተወዳዳሪ ደግሞ ፈተና ወደሚባለዉ ፌዝ የሚያልፍ እድለኛ ሰዉ ይሆናል፡፡ ይህ ሓላፊ እያንጎራጎረ የተወሰኑ ስሞች ላይ ቲክ ያደርግ ጀመር፡፡ "የሰርጌ ለታ... የሰርጌ ለታ... የሰርጌ ለታ ከበሮዉ ተመታ... የሰርጌ የሰርጌ የሰርጌ የሰርጌ፣ ጫማየን አርጌ " ይህች ቀን የተባረከች ቀን ነች፡፡ ከፍቅሬ ጋ በአንድ ጎጆ መኖር የምጀምርባት፣ ወግ ማዕረጌን የማይባት ዕለት፡፡ ቁጥሩም እንዲሁ የተባረከ ነዉ፡፡

ልብ በሚሰብር ሁኔታ የድንበሩ ስልክ ቁጥር ዉስጥ ያች የእድል ቁጥር የለችም፡፡ 18፡፡ ድንበሩ ለፈተና አልተጠራም፡፡

## ሳምንታት ሄዱ

ድንበሩ ስራ አጥ ነዉ፡፡ ሲቪዉን ግን በየቦታዉ ከመበተን አልታጎለም፡፡ ኤች አር ማኔጀሩ ረዳቱ መርጦ ያመጣለትን የ30 ሰዎች ሲቪ እየመረመረ ነዉ፡፡ መዛግብቱን በማገላበጥ ላይ እያለ ድንገት ፊቱ ጠቆረ፣ ዐይኖቹንም ግድግዳ ላያ ተክሎ በሐሳብ ርቆ ነጎደ፡፡

አባቱ እጅግ የተከበሩ ገበሬ ነበሩ፡፡ እሱ ለዚህ ደረጃ የበቃዉም በአባቱ ያላሰለሰ ጥረት ነዉ፡፡ "ምን ዋጋ አለዉ" አለ ጥርሶቹን እያፋጨ፡፡ "ያ የተረገመ እርኩስ አባቴን ነጠቀኝ፡፡" የድንበሩን ሲቪ አፈፍ አድርጎ አስተዋለዉ፡፡ 3.8 ጂፒኤ አለዉ፡፡ ከተወዳዳሪዎቹ መካከልም ከፍተኛዉ ዉጤት የእርሱ ነዉ፡፡ ኤች አር ማኔጀሩ ግን በዚህ ደስተኛ አይደለም፡፡ "ማንም ይኼን ስም ይዞ እዚች መስሪያ ቤት አይሰራትም!!" አባቱ ድንበሩ በተባለ ሽፍታ ነበር የተገደሉት፡፡ ሲቪዉን ቀዳዶ ወረወረዉ፡፡

ድንበሩ አልተደወለለትም፡፡ ለፈተናም አልቀረበም፡፡

## መንፈቅ አለፈ

ድንበሩ ስራ አላገኘም፡፡ ፈተና ለመፈተን ክብር ግን በቅቷል፡፡ ፈተናዉ በእጅጉ ስለቀለለዉም ስራዉን ስለማግኘቱ ቅንጣት ጥርጣሬ የለዉም፡፡ የሚፈለገዉ አንድ ሰዉ እርሱ እንደሚሆን እርግጠኛ ነዉ፡፡

ኤች አሩ ፈተናዉን ከተፈተኑ ሃያ እጩዎች መካከል የአንድን ሰዉ ስም ፍለጋ እየባዘነ ነዉ፡፡ "ሒሩት ኃይሉ" የሚለዉን፡፡ ስልክ ቁጥሯን አዉጥቶ ደወለ፡፡ የጥሪ ድምፁን እየሰማም የፈተናዉን ዉጤት በዐይኖቹ ገረፍ አደረገ፡፡ 100 ከ 100 አምጥቶ ፈተናዉን በአንደኝነት ያሸነፈዉ ሰዉ ስም "ድንበሩ ይሁን" ይላል፡፡ "ዉጤቱ ከመለጠፉ በፊት ለሒ ሩት መደወል አለበት!" አለ በማልጎምጎም፡፡

እ... ሃሎ፡፡ ጠና ይስጥልኝ፡፡" አለ ዉበቷን በአዝነ ልቡናዉ እየሳለ፡፡ "ወ/ሪት ሒሩት... ለስራ ተመዝግበሽ ፈተናም ተፈትነሽ ነበር፡፡ እ... አዎ እዛዉ መስሪያ ቤት፡፡" ከወገቡ ለጠጥ ብሎ ተቀመጠ፡፡ "ግን በሚያሳዝን ሁኔታ 19ኛ ነዉ የወጣሽዉ፡፡ በእዉነት፡፡ እንግዲህ ዋናዉ ነገር እኔ አንደኛ ላደርግሽ እንደምችል ማወቅሽ ላይ ነዉ፡፡ አዎ ይኼን ቁጥር ይዘሽ ነገ ደዉይልኝ፡፡ ያዉ መቼም ስራዉ ያለዉን ቦነስና ጥቅማ ጥቅም አታጭዉም"

## መሸቶ ነጋ

ድንበሩ ሰሞኑን ሰንቆት የኖረዉ ኃያል ተስፋ የመከነዉ ጥዋት መስሪያ ቤቱ ደርሶ የተመለሰ ጊዜ ነዉ፡፡ የፈተና ዉጤቱ እንደ ሚያሳየዉ ድንበሩ 19ኛ ደረጃን ይዞ ነዉ ያጠናቀቀዉ፡፡ ተስፋ መቁረጥ በላዩ እንዳንዣበበ "የማይመስል ነገር" ይላል ደጋግሞ፡፡ ዐይኖቹ ድፍርስርስ ብለዋል፡፡ ደም ስሩ ተግተርትሯል፡፡ በደመ ነፍስ ብቻ እየተመራ ሲበር ወደ በኣቱ አመራ፡፡

ኤች አሩ የሒሩትን ገላ አንጋጦ እያየ ነዉ፡፡ ሒሩት እንደ ለጋ ፓፓዬ የሾሉ ጡቶቿን አስቀድማ ቀረበችዉ፡፡ ቸኩሏል፡፡ ከናፍሩን አረጣጥቦ እጇን ይዞ ጎተታት፡፡

ድንበሩ የክፍሉን በር አጥብቆ ዘግቶ የአልጋዉ ጠርዝ ላይ ቁጭ አለ፡፡ የዐይኖቹ ሽፋሽፍቶች የእንባ ነቁጦችን አንጠልጥለዋል፡፡ በእጁ የያዘዉን ነገር ትኩር ብሎ ተመለከተዉ እና ፊቱን አኮምጭጮ ወደ ጥቁሩ ጣራ አንጋጠጠ፡፡ "አልሆነማ" አለ ሳግ በሚያንቀዉ ሹክሹክታ፡፡ "ሰዉ የለማ፡፡... ሰዉ... የሚገባዉን ለሚገባዉ መስጠት  የሚያዉቅ ሰዉ የለማ"፤ በእጁ የያዘዉን ብልቃጥ ከከንፈሩ ለከከ፡፡

ኤች አሩ የሒሩትን ላብማ ገላ ጨፍቆ ቁና አየር ተነፈሰ፡፡ በስሜተ ወሲብ፣ በፍትወት እርካታ ላዩዋ ላይ ሆኖ አጓራ፡፡ በቆዳዉ ቀዳዶች የልፊ ላብ ደፈቀ፡፡ በድካምም ዝሎ ከሒሩት አጠገብ ወደቀ፡፡ ድንበሩ አልጋዉ ላይ ተጥመዘመዘ፡፡ ሆዱ ዉስጥ የገባዉ መርዝ እያንዳንዱን እቃ ሲበጣጥስ እየተሰማዉ አጓራ፡፡ ላብ አጥምቆት እየቃዠ፣ መልአከ ሞት እየታየዉ ከአልጋዉ ወደ መሬት ፈሰሰ፡፡



በአያሌው አስረስ

# እራስን በራስ ያሳዬ ውይይት

ሃሳብን ስለመግለጥ የሚናገሩ በየቀኑ የምንገለገልባቸው ምሳሌዎች አሉ፡፡ አንዳንዶች መናገርን ግድ ሲያደርጉት ሌሎች አላስፈላጊ ያደርጉታል፡፡"ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል" የሚለው ምሳሌ እያንዳንዳችን የልባችንን መሻት ሌላው ሰው ያውቅ ዘንድ፣ እኛም የእሱን ፍላጐት እንረዳ ዘንድ ምኖታችንን ፣ አላማችንን መግለጥ እንዳለብን ያስገነዝበናል፡፡

"ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም" የሚለው ደግሞ የምትናገረው ነገር ሊያስከትል የሚችለው ጉዳይ አስቀድሞ ስለማይታወቅ አንድም ነገር መናገር የለብህም ብሎ የሚገድብ ነው፡፡ ይህ የሀሳብ ነፃነትን ይገታል ብንል አልተሳሳትንም፡፡ ይሁን እንጂ " ከአነጋገር ይፈረዳል ከአያያዝ ይቀደዳል" በሚለው ምሳሌያዊ አነጋገራችን ሥርዓት ያለው ሃሳብ አገላለጥ ዋጋ እንዳለው ስለሚነግረን በእርሱ እንጽናናለን፡፡

የአንድ አሳቢ ከመሆን ይልቅ የመናገርን፣ ሃሳብ የመለዋወጥን ፣ የመወያየት አስፈላጊነትንና ጠቃሚነት የሚያምነው ኢንሽቲብ አፍሪካ " በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የውይይት ባህልን ማስረጽ" የሚል ፕሮጄክት ነድፎ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ፕሮጀክቱ የሚካሄደው አዲስ አባባ ባለው የስዊድን ኤምባሲ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን ፣ የውይይት ፕሮግራሙ ከሚካሄድባቸው ዩኒሸርስቲዎች ጋር በመሆን ዩዝ ኤንድ ካልቸር ዴቨሎፕሜንት ፋውንዴሽን የማስተባበር ሥራውን ይሠራል፡፡

በአምቦ ዩኒቨርስቲ አስተዳደር የመሰብሰቢያ አድራሻ፣ ዩሸርስቲው ለውይይት በመረጣቸው የሴቶች እኩልነት ጥያቄ እና ሥራዓተ ፆታ እንዲሁም የበጐ ፈቃድ አገልግሎት በሚሉ ሁለት ርዕሶች ላይ ሐምሌ 9 ቀን 2011 ዓ.ም. ውይይቱ ተካሄዷል፡፡ የውይይቱ ተካፋዮች የዩኒሸርስቲው ተማሪዎች፣ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች ነበሩ፡፡

"የሴቶች የእኩልነት ጥያቄና ሥርዓተ ፆታ" የሚለውን የመወያያ ርዕስ ያቀረቡት፣ በአምቦ ዩኒቨርስቲ የሕከምና ሳይንስ ኮሌጅ የድህረ ምርቃ ፕሮግራም አስተባባሪ፣ ተባባሪ ፕሮፌሰር ሲስተር ሸዋዬ ፈጡማ ሲሆኑ፣ በእኩልነት ጥያቄው ላይ ብዥታ የሚፈጥሩ በርካታ ነገሮች መኖራቸውን ጠቁመው ሊለወጥ የማይችለው የተፈጥሮ ፆታ የችግሩ መደበቂያ እየሆነ ማገልገሉን በአፅንኦት አስገንዝበዋል፡፡ የሴቶች ጥያቄ የፆታ ለውጥ ሳይሆን እኩል ድርሻ እኩል ተጠቃሚነት መሆኑን አስምረውበታል፡፡

በገጠር እናቶች በሴት ልጆቻቸው ላይ ሥራ ቢያበዙ ስለአላወቁ ነው ተብሎ ሊታለፍ ይችል ይሆናል፣ ሰልጥኖአል ተምሯል የምንለው የሕብረተሰብ ክፍል እራሱ ምን እየሠራ ነው? ብለው የሚጠይቁት ሲስተር ሸዋዬ፣ አባት ለልጆቹ መጫወቻ ሲገዛ ለወንድ ኳስ ለሴቷ የሕፃን አሸንጉሊት እንደሚገዛ ዘርዝርው ሴት ልጁን ምን ጊዜም ለማታጣው እናትነት እያዘጋጃት መሆኑን ልብ ልንል ይገባል ብለዋል፡፡

የሥርዓተ ፆታ ዋና ጉዳይም ይህን በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ለሴትና ለወንድ የሚገባና የማይገባ የሚለውን የተሳሳተ የሥራ ክፍፍል እንዲታረም ማድረግ፤ ሴትም ሆነች ወንድ ልጅ እኩል እንክብካቤ እንዲያገኙ የሚደረግበት ሥርዓት እንዲዘረጋ መሥራት መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ወደ ዩኒሺርስቲ ለመግባትም ሆነ በዩኒቨርስቲ ቆይታቸው ለሴቶች የሚደረገው ድጋፍ ብቃት የሌላቸውን ተማሪዎች ለማብቃት ሳይሆን፣ መጀመሪያውኑ ብቃቱ ኖሮአቸው እዚያ ደረጃ ላይ የደረሱ ሴት ልጆችን የበለጠ ለማብቃት መሆኑ ግንዛቤ ማግኘት እንዳለበት ሲስተር ሸዋዬ አሳስበዋል፡፡ አያይዘውም በሥርዓተ ፆታ ተግባር ላይ ወንዶች እየሠሩ በሚገኙበት ጊዜ፣ እሱን ደግሞ በሴት ጉዳይ ምን አገባው? የሚል ትችት እንደሚሰማ አውስተው፣ የሥርዓተ ፆታ ችግር ሕብረተሰቡ በረጅም ዘመኑ የገነባው ባህል በመሆኑ እሱን ለማስወገድ ደግሞ የወንዱም የሴቷም መተባበር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አሳውቀዋል፡፡

እኛ ስለ እኩልነት እንናገራለን፤ የክርስትና ሃይማኖት ደግሞ ወንድ የሴት ራስ ነው፣ ሚስት ለባሏ ትታዘዝ ወይም ትገዛ እያለ ያስተምራል፡፡ ከባህላችን መሰረቶች አንዱ ደግሞ ሃይማኖት ነው፡፡ ይህን ተቃርኖ እንዴት መፍታት ይቻላል? የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው ሲስተር ሸዋዬ ፣ ባለቤታቸው የእሳቸው ገዥ አለመሆናቸውን፣ የሃይማኖት አባቶችም ሴትና ወንድ እኩል መሆናቸውን እያስተማሩ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ የአተያይና ያረዳድ ችግር ሊኖር እንደሚችልም እንደሚገነዘቡ አስረድተዋል፡፡

አቶ ዐቢይ ወንድሜነህ ከሲቪክ የትምህርት ክፍል በአቀረቡት የመወያያ ሀሳብ በሃገራችን ብልጭ ድርግም ከሚል በቀር የቆየና ሥር የሠደደ የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ባህል የሌለን መሆኑን ጠቁመው፣ መለመድ ያለበት፣ ሊለመድ የሚችል መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ተማሪዎች በክረምት የእረፈት ጊዜያቸው ሕፃናትን እየሰበሰቡ መጽሐፍ ቢያነቡላቸው የንባብ ባህላችንን ለማሳደግ እንደሚያገለግል አሳውቀዋል፡፡

የበጐ ፈቃድ አገልግሎት በክፍያ የሚሰጥ አገልግሎት አይደለም፡፡ በምንሰጠው አገልግሎት ለሰው ልጅ ያለንን ክብር እናሳይበታለን፡፡ ይህን በማድረጋችን ደግሞ በገንዘብ የማይለካ የሕሊና እርካታ እናገኛለን" ያሉት አቶ ዐቢይ በበጐ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው አገልግሎት ይኸ ፣ይኸ ተብሎ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አለመሆኑን አመልክተዋል፡፡

የተማሪዎች የበጐ ፈቃድ አገልግሎት በንጉሡ ዘመን በፊደል ሠራዊት ዘመቻ ተጀምሮ እንደነበር ያታወሱት አንድ የውይይቱ ተሳታፊ በደርግ የተካሄደው የእድገት በሕብረት ዘመቻ ብዙዎችን የማንበብና የመጻፍ እውቀት እንዳስጨበጠ አስረድተው ዛሬም ወጣቶች ብዙ ሊሠሩበት እንደሚችሉ አስገንዝበዋል፡፡

ቀደም ሲልም የፕሮግራሙ አስተባባሪ የዩዝ ኤንድ ካልቸር ዴቨሎፕሜንት ፋውንዴሽን ዳይሬክተርና የፕሮግራሙ አስተባባሪ አቶ ዜናዬነህ ግርማ፣ በሃገራችን የተጀመረውን ለውጥ ለማምጣት ወጣቶች ከፍተኛ መስዋዕትነት መክፈላቸውን ዘርዝረው፣ አሁን አሁን በውይይት በመነጋገር ሊፈቱ የሚችሉ ጉዳዮች ሕይወት እስከ ማሳጣት እየደረሱ በመሆኑ የመወያየት ልምድ በከፍተኛ ተቋማት ሊጀመርና ሊዳብር እንደሚገባው አስገንዝበዋል፡፡

መንግሥት የሰላም ሚኒስቴር እንዲሁም የሰላምና የእርቅ ኮሚሽን የሚባሉ መሥሪያ ቤቶችን ማቋቋሙን ፣ አሥራ ሦስት ሕጐች ማሻሻሉን ጠቁመው፣ ብዙ ሊያወያዩና ሊያነጋግሩ የሚችሉ ሃገራዊ ጉዳዮች ዛሬም መኖራቸውን አስረድተዋል፡፡

"በሀገራችን 108 የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ፡፡ አላማቸው ምን እንደሆነ ሲናገሩ አይሰማም፡፡ በፊት የመሪ ችግር ነበር፤ አሁን ደግሞ የተመሪ ችግር እየታየ ነው" ያሉት አቶ ዜናዬነህ ተማሪዎች የውይይት ባህልን መገንባት እንዳለባቸው አሳውቀዋል፡፡

ተማሪ ፈንታዬነሽ ደመቀ በውይይቱ እራሷን ተመልሳ እንድታይ መገፋፋቷን ጠቁማ በበጐ ፈቃደኛነት የአካባቢዋን ሕብረተሰብ ለማገልገል ፍላጐት እንዳደረባት በሰጠችው አስተያየት አስረድታለች፡፡

አቅራቢና የውይይቱ ተሳታፊ ሲስተር ሸዋዬ የውይይቱን ፋይዳ፤ "ወፍጮ ቤት የገባ ሰው ዱቄት ሳይቦንበት አይወጣም ፡፡ ማንም ባዶውን ተመልሷል ብዬ አላምንም ፡፡ እኔ እራሴ ብዙ አዳዲስ ሀሳቦች ከውይይቱ አግኝቼበታለሁ" በማለት ገልጸውታል፡፡

ተማሪ ማሚቱ ይስሐቅ በበኩሏ ብዙ ልብ ያላለቻቸዉን ጉዳዮች ልብ እንድትላቸው ስብሰባው ማድረጉን በመገረም ስሜት አስረድታለች፡፡ የሷ ወደራስ ተመልሶ ራስን የማየት የብዙዎች ተሰበሳቢዎች ስሜት እንደነበር መረዳት አስቸጋሪ አልነበረም፡፡

ውይይቱን ሁሉም ራሱን እንዲያይ ያደረገ ብሎ ማግለጽ ይቻላል፡፡

# ዓለም ዓቀፍ ተሸላሚዋ መዓዛ መንግስቴ

ብሩክ መኮንን

“የተወለድኩት በ1970ዎቹ አጋማሽ ላይ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ነው፡፡ አያቴ የቀ.ኃ.ስ ቤተ መንግስት ሹመኛ ነበር፡፡ እኔ ስወለድ በሃገራችን አብዮት ፈንድቶ ፣ ንጉሱ ከስልጣን ተወግደው አለመረጋጋት ተከስቶም ነበር፡፡

የወቅቱ ሁኔታ ለቤተሰባችን ደህንነት አስጊ ስለነበረ መላው ቤተሰብ ሃገር ጥሎ ተሰደደ፡፡ በመጀመሪያ ናይጄሪያ ከቆየን በኋላ ሰባት ዓመት ሲሞላኝ ወደ አሜሪካ በማቅናት በኮሎራዶ ስቴት መኖር ጀመርን፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአሜሪካ በማቺን፣ በሎስአንጀለስ ስኖር ቆይቻለሁ፤ ለአመታት ወደ ኢጣልያ ሄጄ ነበር፣ ከዛ ተመልሼ በኒዮርክ እየኖርኩ ነው፡፡ አፌን የፈታሁት በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡

ወደ አሜሪካ ስገባ እንግሊዘኛ በደንብ እናገር ነበር፡፡ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ተከታትዬ ወደ ኮሌጅ ስገባ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወላጅ ልጁ እንዲሆንለት የሚመኘውን የሕክምና ዶክተር ለመሆን አስቤ ነበር፡፡ ግን ይህ ሐሳብ እንደማይሆንልኝ አመንኩኝ፡፡ እምነቴን ለወላጆቼ እንዴት ማስረዳት እንዳለብኝ እንኳን አላውቅም ነበር፡፡

ቤተሰብ ልጆቻቸውን ገና ወደ ትምህርት ቤት ሲልኩና ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ የሕክምና ዶክተር ወይንም ኢንጂነር ሆነው ለሃገርና ለወገን የሚተርፉ ይሆናሉ ብለው ነው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ወላጆች የሚያስቡት፡፡ እኔም በኮሌጅ ለመማር የወሰንኩትን ለማስረዳት ተቸገርኩ፡፡

ለወራት በዚህ መልክ ከቆየሁ በኋላ፣ እንደምንም ተደፋፍሬ ለአባቴ እያጠናሁ ያለሁት የእንግሊዘኛ ቋንቋ መሆኑን ነገርኩት፡፡ አባቴ “ለምድን ነው እንግሊዘኛ ቋንቋ የምትማሪው? መናገርም መፃፍም ትችያለሽ”ሲል ቅሬታውን ገልጾ ዝም አለኝ፡፡

ከዓመታት በኋላ የኮሌጅ ትምህርቴን አጠናቅቄ ወጣሁና በአንድ የንግድ ሥራ ክህሎት የማማከር አገልግሎት በሚሰጥ ኩባኒያ ውስጥ ተቀጥሬ ለሁለት ዓመት ሰራሁ፤ በወቅቱ በስራዬም ሆነ በሕይወቴ ደስታ ርቆኝ ነበር፡፡

ከዚህ የመንፈስ ድብታ ለመውጣት ወደሎስአንጀለስ በማቅናት በአንድ ግዙፍ የንግድ ማስታወቂያ በሚሰራ ኩባኒያ የፊልም ጽሁፎች በማዘጋጀትና በማዳበር ስራ ተሰማራሁ፡፡

አዲሱ ስራዬ የምመኘውና የሚያስደስተኝ ነው ብዬ አምኜ ለመቀበል ሞከርኩ፡፡ የምሰራው ለገበያ የሚቀርቡ ሸቀጦችን ገበያተኛው እንዲገዛቸው ከማማለል፣ በገበያው ተፈላጊ እንዲሆን ከማድረግ ውጭ ሌላ ፋይዳ እንደሌለው ስረዳ፤ ከወትሮው የበለጠ ደስታና እርካታ ራቀኝ፡፡ ለቅርብ አለቃዬ ስራውን ደስ



መዓዛ መንግስቴ

ብሎኝ ልሰራው ስላልቻልኩ ልተወው ነው ስል አማከርኩት፡፡

በዚህ ዓይነት መጥፎ ስሜት ውስጥ እያለሁ ነው ስለ ትውልድ ሃገሬ ስለ ኢትዮጵያና ሃገራችንን ጥለን እንድንሰደድ ያደረገንን አብዮትና በስልጣን ላይ የነበረው ወታደራዊ ጁንታን በተመለከተ ማሰብ የጀመርኩት፡፡ ይሄ በውስጤ የሚመላለሰው ሀሳብ እያደገ አብሮኝ ይኖር ጀመር፤ ቀደም ብዬ አጭር ልብወለድም ሆነ ይሄ ነው የሚባል ጽሁፍ ጽፌ አላውቅም፡፡ ይሄ ውስጤን ፋታ ያሳጣኝን ሀሳብ እንዴት ልገላገለው? በድንገት ሥራዬን ለቀቅሁና የድህረ ምረቃ ትምህርቴን ለመቀጠል ኒውዮርክ ዩንቨርስቲ ገብቼ መማር ጀመርኩ፡፡

ያኔ ነው ራሴ ወደላየሁትና ህይወት በሰጠኝች አማራጭ መንገድ ላይ ለመጓዝ ወሰንኩኝ፡፡ የምጽፈው በውስጤ ያለውን ሐሳብ ለመገላገል ነው፡፡ ያለማቋረጥ ቀን ማታ ሳልል እጽፍ ነበር፤ እረፍተ ቢስ ሆኜም ነበር፡፡ በእውነት ነው የምላችሁ፣ የምጽፈው መጽሐፍ ሆኖ ይታተማል ወይም እንዲህ ተነባቢ ይሆናል ብዬ አልነበረም፡፡”

የምትለው እውቋ ደራሲ መዓዛ መንግስቴ ከኢትዮ-አሜሪካውያን ደራሲዎች ነጋ መዝለቂያ፣ ዲናው መንግስቱ ጋር ስሟ የሚጠራው፣ በርካታ ዓለም ዓቀፍ ሽልማት የተሸለመችው ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ መአዛ መንግስቴ፤ ከዘጠኝ አመት በፊት በ2010 አመተ ምህረት ‘Beneath the lion’s gaze’ የተሰኘው መጽሐፏ በፈረንሳይኛ፣ በስፓኒሽ፣ በፖርቱጊዝ፣ በጀርመን፣ በኢጣልኛ፣ በደች፣ በ ስዊድን ቋንቋዎች ተተርጉሞ ለንባብ በቅቷል፡፡

“በርካታ የዓለም መገናኛ ብዙሃን ይህን መጽሐፍ በተመለከተ ዳሰሳ ሰርተው አቀረቡ፡፡ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በተለያዩ መድረኮች እየተገኘሁ ስለመጽሐፌ እንዲሁም ስለ ጽሁፍ ክህሎቴ ገለፃ እንድሰጥ እጋበዝ ጀመር፡፡

ሕይወቴ ከኢትዮጵያ ከጋራ የተያያዘ ነው፡፡ ገና በአስራ ሁለት ዓመት ዕድሜዬ አያቴ የሰጠችኝ የወርቅ አምባር አለ፡፡ ለአፍታም ቢሆን ከእጄ አወልቄው የማላውቀው፡፡ የተለያዩ ሃገራት ስገባኝ፣ ለሥራ ስሄድ በኤርፖርት ከደህንነት ፖሊሶች ጋራ ሁልጊዜ እወዛገብበታለሁ፡፡ ለአያቴ ቃል የገባሁላት እስከመጨረሻው ከእጄ አላወልቀውም ብዬ ስለሆነ፤ ቢያንስ ለ30 ዓመት ያህል ከእጄ አላወለቅሁትም፤ ወደፊትም አላወልቀውም፡፡” በማለት መዓዛ ኢትዮጵዊና ቤተሰባዊ ቃል ኪዳኗን ተናግራለች፡፡

በአሁኑ ወቅት በኒዮርክ ዩኒቨርስቲ በኪዊንስ ኮሌጅ በፈጠራ ስነ ጽሁፍ አጻጻፍ ዘዴ መምህር ስትሆን፤ በፕሪስተን ዩንቨርስቲ በሊዊስ ሴንተር ኦፍ አርትስ ኮሌጅም በሌክቸረርነት እየሰራች ነው፡፡

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳጅነት ያገኘውን መጽሐፍዋን ካሳተመች በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ለወራት በሰሜን ኢትዮጵያ፣ በባህርዳር ዙሪያ የጎጃም የተለያዩ ገጠራማ አካባቢዎች ቆይታለች፡፡ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ሕይወታቸውን በገጠር እንዴት እንደሚመሩ ለመረዳት፣ ባህል፣ ወግና ስርዓቷን በቅጡ ለማወቅ ያስቻላት ዕድል እንደሆነም ትናገራለች፡፡

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ girl rising የተሰኘ የጥናታዊ ፊልም ድርሰት በማዘጋጀት በልጅነቷ፣ ያለዕድሜዋ ተድራ ይህንን ኋላቀር አስተሳሰብ በማሸነፍ ወደ ቤተሰቦችዋ ተመልሳ ያቋረጠችውን ትምህርት በመቀጠል፣ ለስኬት የበቃች ወጣት ኢትዮጵያዊትን የሚያወሳ የፊልም ድርሰት በ2013 በመጻፍ፤ በዘርፉ አሸናፊ በመሆን በዓለም መድረክ ስሟን አስጠርታለች፡፡

“ከወላጆቼ የወረስኩት ፅናት፣አልበገር ባይነት መንፈስ ከእኔ ጋራ ነው፡፡ በመስከረም ወር 2019 ላይ ለገበያ የሚውል ሁለተኛ መጽሐፌ በሕትመት ላይ ይገኛል፡፡

ሰው እንደሚጠላው የሚነግረኝን ፒጃማ፣ ጋውን ወይም ረዥም ድሪያ እየጎተትኩ ልታገኘኝ ትችላለህ፤ የሚያስደስኝ መፃፍ፣ ማንበብ፣ ከሰዎች ጋር ማውጋት እና ተፈጥሮን ማድነቅ ብቻ ነው” ትላለች መዓዛ መንግስቴ፡፡

የፊል ብራይት ፌሎሺፕ የ2010 አሸናፊ የ2011 አሸናፊ፣ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከተመረጡ ልብወለድ ደራሲዎች ውስጥ ምርጧ በመሆን በ2010 ተጨማሪ ሽልማቶችን የወሰደችውና የክሬቲቭ ካፒታል አዋርድ የሥነ ጽሁፍ የልብወለድ ሥራዎች ደራሲ በመሆን በያዝነው ዓመት ተሸላሚ መአዛ መንግስቴ፤ በተለያዩ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ሥራዎችም ታካሂዳለች፡፡ “ዘ ወርድስ ዊዛውት ቦርደርስ” የተሰኘ መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚከሰቱ ግጭቶች የሚፈናቀሉ ሕፃናትና ወጣቶችን መብት የሚያስከብር ተቋም ሓላፊ ሆና በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡



ፍቅርተ ተሾመ

# ጥበብ በኛ ዘመን ማለት በዚህኛው

ጥበብ እና ጥበበኞች ከህዝብ የቀደሙ, ህዝብን በሐሳብ፣ በዕይታ እና በማስተዋል ቀድመው የሚገኙ መሆናቸው ከተራው ህዝብ ተለይተው ጥበበኛ ተብለው የጥበብን ካባ ለብሰዋል። ጥሩ የቢዝነስ አውድ ያገኘው ጥበብ በሓገራችን እንደሌሎች መስኮች ሁሉ የራሱ ተግዳሮቶች አሉት። እውን በዚህ ዘመን ተግዳሮት የሌለበት ምን ስራ አለና? አንድ ህዝብ በጥበብ ስራዎች እንደሚገራ ማሳያው ብዙ ነው። በሃገራችንም "የድሮ ናፋቂዎች" በሚል ማሸማቀቂያ ማንነታችንን ወደ ኋላ ተመልሰን እንዳናይ በማድረግ የኋላ ቀርነት መልክ ሊሰጠው ቢሞከርም፤ ከድንቅነታችን ባሻገር ሊፋቅ የማይቻል ነውና ልናይ ግድ ይሆናል።

እንዲህ ይላሉ ዶ/ር ሮዳስ ታደሰ፤ "ሰው ወደ ብድር ከመሄዱ በፊት ይህ ነገር እኔ ጋር አለ፣ የለም? ብሎ በቅድሚያ ይመረምራል፡፡ ከዚያም ከሌለኝ እንዲግዲያውንስ እኔ መስራት እችላለሁ ወይ? ብሎም ደግሞ ራሱን ይጠይቃል። ሰው ከዚህ በኋላ ነው ወደ ለማኝነት ፣ተመፅዋችነትና ወደ ብድር የሚሄደው" በማለት የተውሶ ባህላችንን ይገልፁታል። ያለንበትንም ቦታ ማጤን ያሻል፤ የትነን? ስንል ነጭ ቆዳ ያለው ጀግና ገፀባህርይ ውስጥ፤ አሁንም የት ነን? ስንል ቴሌቪዥንን ያቀረበው የእሩቅ እርቅ ስልጣኔ(ሰይጣኔ) ውስጥ፤ ይህ ምን አተረፈ? የጆሶ እንጀራ።

ታዲያ "ከጆሶ ዘመን ወደ ጮማ ዘመን መመለስ ተገኝቶ ነው" እንዳሉት። ጥበብ በሃገራችን የነበረው ቦታ እና ግዝፈት ህዝብን የሚመራ ነበር። በዋናነትም የህዝብን አስተሳሰብ እና ፍልስፍና ማሳያ እንደነበር ለማወቅ የተለያዩ ድርሳናትን እና መፃሕፍትን ማገላበጥ፣ የዘመኖችን የጥበብ ገላጭነት ፍንትው አድርጎ ያሳያል። ጠቢባን ዋጋቸው በዚያንም ጊዜ ግልምጫ እና ፍቅር ሁለቱም በፈረቃ እንደሚሰጣቸው ሁሉ አሁንም ይህ ሂደት ያለ ነው። ጠቢባን ይተቻሉ፣ ጠቢባን ሰላምንም ይሰብካሉ፣ ጠቢባን ያስታርቃሉ፣ ለጦርነትም ያነሳሳሉ። ይሄ ተሰጥኦቸው በሁኔታዎች ሊገታ አይቻለውም እንዲህ ናቸውና። እንዲያውም የሁኔታዎች መቀያየር ተሰጥኦቸውን እንዲያወጡና ጥበባቸው እንዲገለጥ ቢረዳቸው እንጂ።

## በዚህኛውስ ዘመን

በዚህኛውማ፤ ጠቢባን ጥበብን ከቢዝነስ ነክ ነገር ውጭ እንዴት ሆኖ ብለው፤ እንዲችም ብሎ ሃሳቡ ልፍለቅ፣ ልገንፍል ልገንፍል የሚላቸው አይመስልም። ጥበብም ዝም፣ ጠቢቡም ዝም። መቼም ለህዝብ እያገለገሉ "የህዝብ ነን" እያሉ፣ ብቻ ገቢ አይኑራቸው ለማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው። በዚህች በምጥ ውስጥ ሳለች ሃገር ብርን በማለት ብርር ሲሉ የቆሙባት ምድር በምጥ ትሙት ትኑር ሳያውቁ ደርሶ ብርርር ማለት የሚያስከፍለውን ዋጋ የተገነዘቡ አይመስልም። ያቺ በጥበብ የተደነቀች ሃገር እና ህዝብ አሁን በተቀደደለት የሚፈስ ዘመናዊ የጥበብ አካሄድ ውስጥ በተዘፈቁ "አርቲስቶች" "ጥበበኞች" እውነትም አማርኛው ይከብዳል መሰል እንኳንም ቀርቶባቸው አርቲስት ተባሉ ብቻ፣ ከጥበቧ ማማ ተጎትታ ወድቃ ረክሳለች ከክብሯ። ይሄ እለት እለት እየተጉ የጥበቡን ዙፋን ሊወስዱ ከጫፍ የደረሱትን አያካትትም። ሆኖም እኒህም የጥበብ ሰዎች ድሃውን የሃገሪቱን ማህበረሰብ የማዳረሳቸው ጉዳይ አሁንም አጠያያቂ ነው፡፡ መመራት የሚፈልገው ከታች ያለው የኑሮ መመወሳሰብ ግራ ያጋባው፣ ረሃብ፣ ጥማት፣ እርዛት ያሰጋው ሳቅ፣ደስታ፣ እና ሙላት እንደ ፀሐይ ጀምበር ስትወጣ የሚያያት ግን የማይሞቃት ተስፋ ሆና ለምትታየው ለዚያ

...ከጆሶ ዘመን ወደ ጮማ ዘመን መመለስ ተገኝቶ ነው" እንዳሉት፡፡ ጥበብ በሃገራችን የነበረው ቦታ እና ግዝፈት ህዝብን የሚመራ ነበር፡፡ በዋናነትም የህዝብን አስተሳሰብ እና ፍልስፍና ማሳያ እንደነበር ለማወቅ የተለያዩ ድርሳናትን እና መፃሕፍትን ማገላበጥ፣ የዘመኖችን የጥበብ ገላጭነት ፍንትው አድርጎ ያሳያል ...

ደሃ ህዝብ ግን ማን አለሁ ይበለው? ጥበብ ወዴት ይሆን?

## ጥበብ እና ሴቶች ከዚህኛው ዘመን

ከኢትዮጵያ ሴቶች ውስጥ ሃገራቸውን በጥበብ እና በልበ ሙሉነታቸው በምሳሌነት ከሚነሱት ውስጥ አንዷ ንግስት ሣባ ናት። በጥበቧ እጅግ ያስደነቀችው ንጉሥ ሰለሞንን እንዲህ ጠየቀችው፤ ሁለት ተመሳሳይ ሊለዩ የማይችሉ የተፈጥሮ እና ተፈጥሮአዊ ያልሆነ (አርቲፊሻል) አበባዎችን ይዛ "አበባ አየህ ወይ አለችው?" እርሱም ቢያያቸው በፍፁም ሊለያቸው አልቻለም እና መስኮቱን አስከፈታት፤ ኋላም ንቦች ለመቅሰም በተፈጥሮአዊው አበባ ዙሪያ ሲዞሩ አይቶ "ይህ አበባ የተፈጥሮ ነው" አላት የሚሉ የታሪክ ትውፊቶችን ያገኘነው ከኛው ከኢትዮጵያውያን ልበ ሙሉ ሴቶች ነው ሲሉ ዶ/ር ሮዳስ በአንድ ዲስኩራቸው ላይ ተደምጠዋል። ጥበብ በሃገራችን እየተሰበሰበች እና እየተሰራች ነው በሚሏት ሳይሆን ተሰርታ እና ተገንብታ ባለቀችው ኢትዮጵያ ነግሳ ትኖር ነበር። ጠቢባኑ ያኔ በአይናቸው ብቻ አንጋጠው በማየት፣ የከዋክብትን ህብር ለይተው በማጥናት በልበ ሙሉነት ባላቸው ድንቅ እውቀት ስማቸውን በሰማይ በከዋክብቱ ዓለም ከዓለም ሁሉ ቀድመው ሰቅለውት ይታያል። "ኰዊን ኦፍ ኢትዮጵያ"፣ "ኪንግ ኦፍ ኢትዮጵያ" ብለው ያስጠራሉ ከዋክብት ሲጠሩ ።

## እና አሁን ምን ይሁን

ጠቢባን ጥበብን በጥበብ ተጠቀሙ! ህዝብ እንደሚለው ሳይሆን ህዝብ የሚለው ሁኑ! ዶክተሩም፣ አስተማሪውም፣ አርቲስቱም፣ ገበሬውም፣ አክቲቪስቱም፣ ጋዜጠኛውም፣ ሲቪክ ሰራተኛውም ሁሉም ጥያቄ አለው፡፡ ሁሉም የሚሊየነርነት እና የቢሊየነርነት ትልም አለው። ይህ የሚሳካው ሲሰራ እንደሆነ ያልነቃው ሰልፍ ይወጣል፣ የነቃው ለፍቶ ያድራል፣ ዋጋ ይከፍላል። አርቲስቶች ሆይ ጠቢባን ሁኑ! ተንገዋለሉ፤ አረማችሁን አበጥራችሁ በጥራት ቅረቡ፤ አቅርቡ። ጥበብ ግጥም ብቻ እስኪመስል ድረስ ሰዎች "ግጥም" ብለው የሚመለከቱት ነገር ግጥም ብቻ ሆኗል፤ ግጥምን በሞላ አዳራሽ በማያረፍድ እድምተኛ ዘመነኛው ጥበብ። ኧረ ያ ከሻማ ወደ መብራት ዓለም የተሸጋገርንበት የጥበብ ድግስ ምሽት አሁን ወዴት አለ? ከተሰራ ሃገር ፈርሶ ወደሚሰራ ሃገር ሃገር ሽግግር ላይ ጥበብ ምነው ልጓም ተያዘላት? ሽግግር ነው፤ አሁንም ያው ሽግግር ነው።

# ዝክረ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጴጥሮስ!

## የ83ኛ ሙት ዓመት ማስታወሻ

ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሰማዕት ብፁዕ ወቅዱ አቡነ ጴጥሮስ ለፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል “አልንበረከክም” ብለው ለሀገራቸውና ለሐይማኖታቸው ክብር ሲሉ በግፍ ከተገደሉ እነሆ 83 ዓመት ሞላቸው፡፡ ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም አሁን መታሰቢያ ሐውልታቸው በክብር ቆሞ በሚገኝበት ቦታ ግፈኛን የፋሽስት ወራሪ “ረግመውና ገዝተው” በጥይት ተደብድበው ሠማዕት የሆኑት አርበኛውና የሀይማኖት መሪው ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ለሐይማኖታቸው ዘላለማዊ ክብር ሲሉ የፈፀሙት አኩሪ ገድል ምንጊዜም በታሪክ ሲዘከር የሚኖርባ ስማቸውን ከመቃብር በላይ አውሎ ምንግዜም እንዲታወሱ የሚያደርጋቸው ሲሆን የአዲስ አበባ ም/ከንቲባ ኢንጂነር ታከለ ዑማ በተገኙበት ሥነ ሥርዓትም የሙት ዓመት መታሰቢያቸው በአገር አቀፍ ደረጃ ታስቦ ውሏል፡፡

በዕለቱ የአቡኑ ሐውልት በሚገኝበት ስፍራ በተከናወነው የመታሰቢያ ፕሮግራም ም/ከንቲባው ከሐውልቱ ሥር ባለው የመናፈሻ ስፍራ ችግኝ የተከሉ ሲሆን ባደረጉት ንግግርም « የአቡነ ጴጥሮስ መስዋዕትነት ዛሬ ላለነው ትውልድ ብዙ መልዕክት አለው » ብለዋል፡፡ በሐውልቱ ሥርም የመታሰቢያ ጉንጉን አበባ አኑረዋል፡፡

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጴጥሮስ 83ኛ ሙት አመት መታሰቢያ የተዘከረበት ሐምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም በአገር አቀፍ ደረጃ ችግኝ ከመትከል የአረንጓዴ ዘመቻ ዕለት ጋር መገጣጠሙ በብዙሃን ዘንድ እንደ ትልቅ ታሪካዊ ግጥምጥሞሽ ተደርጎ የሚታሰብ ሊሆን ችሏል፡፡ የዛሬ 83 ዓመት በፋሽስቱ ወራሪ ሀይል በግፍ ተይዛ የለቅሶና የዋይታ ሀገር ሆና የነበረችው አገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ድህነትን ድል ለመንሳትና ተፈጥሮ ለማደስ በዘመቻ መልክ አረንጓዴ አብዮት ላይ የመገኘቷ እውነታም ብዙ የሚያስተላልፈው ብርቱ ቁም ነገር እንዳለው እየተነገረለት ይገኛል፡፡

የግዮን መጽሔት ዝግጅት ክፍልም የእኚህን ታላቅ ኢትዮጵያዊ መስዋዕት አኩሪ ታሪክ በማስታወስ ለ83ኛ ሙት ዓመት መታሰቢያቸው ይሆን ዘንድ ይህን የዝክር ማስተወሻ ጥንቅር ለአንባቢያን እነሆ ብሏል፡፡

በ1875 ዓ.ም.በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሰላሌ አውራጃ ፍቼ ከተማ ተወለዱ፡፡ ወላጆቻቸው ዕድሜያቸው ገና በወግ ለትምህርት ሳይደርስ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመውሰድ ባሕታዊ ተድላ ለተባሉ መምህር አደራ ሰጧቸው፡፡ በዚያው ገዳም የንባብ ቤቱን ና የዜማውን የትምህርት ደረጃዎች በሚያስገርም ሁኔታ በአጭር ጊዜ አቀላጥፈው በመጨረስ ገና በልጅነት የዕድሜ ደረጃቸው ሦስተኛውን የቅኔ ትምህርት ጀምረው በአጭር ጊዜ ሙሉ ቤት ተቀኙ፡፡ ይህንኑ የቅኔ ትምህርት ለማስፋፋት በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ወደ ሚገኘው የቅኔ ትምህርት ማዕከል ዋሸራ ተሻግረው ለመምህርነት የሚያበቃውን ትምህርት ፈጽመው አስመሰከሩ፡፡

ከዚያም ከቅኔው ዓውድማ ጎጃም ወደ ዜማው አዝመራ ጎንደር ተሻገሩ፡፡ በዚያም እንደ ቅኔው ሁሉ እስከ ማስመስከር ባይደርሱም የዜማውን ትምህርት በአጥጋቢ ሁኔታ ቀጠሉ፡፡ ከጎንደርም በወቅቱ ወሎ ቦሩ ሜዳ ከተባለው ቦታ ላይ ወንበር ዘርግተው የመጻሕፍትን ምሥጢር በየዓይነቱ ሲመግቡ ወደ ነበሩት ስመ ጥሩው መምህር አካለ ወልድ ዘንድ በመሔድ ዋና ዋናዎቹን የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርቶች ማለትም ብሉያትን፣ ሐዲሳትንና ሊቃውንትን በብቃት ተከታተሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ልክ በ1900 ዓ.ም. እዚያው ወሎ አማራ ሳይንት በተባለው ቦታ ወደሚገኘው ምስካ በ ቅዱሳን ገዳም በመሔድ ወንበር ዘረጉ፡፡ በዚያው ቦታ ለዘጠኝ ዓመታት ያህል ቅኔንና መጻሕፍትን አስተማሩ፡፡ በዚህ ዓይነት በመማርና በማስተማር ራሳቸውን በእግዚአብሔር ቃል በሚገባ ከጐሰሙ በኋላ በ1909 ዓ.ም. ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመሔድ ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ ማዕረገ ቅስናን ተቀብለው ከወንበሩ አገልግሎት ጋር የቤተ መቅደሱን ተልእኮም ደርበው ያዙ፡፡ በ1910 ዓ.ም. መምህር ኃይለ ማርያም ተብለው በወላይታ ሶዶ በሚገኘው ደብረ መንክራት ምሁር ኢየሱስ ገዳም ተሾሙ፡፡ በ1916 ዓ.ም. እንደገና በዝዋይ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም በመምህርነት ተሾሙ፡፡ በ1919 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ማርቆስ መምህርና በቤተ መንግሥት የግርማዊ



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አበ ንስሐ ሆኑ፡፡

የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ከአንድ ሺ ስድስት መቶ ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያን በዕውቀት መንፈሳዊ ከእርሷ ተወልደው በእቅፏ ውስጥ ባደጉ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንድትመራ ፈቃዷን ስትገልጽ ከተመረጡት አባቶች አንዱ በመሆን ግንቦት 18 ቀን1921 ዓ.ም. በእስክንድርያው መንበረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ማዕረገ ጵጵስናን ተቀበሉ፡፡ ከዓመት በኋላም “አቡነ ጴጥሮስ ጳጳስ ዘምሥራቅ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ኢየሱስ ሞዓ” ተብለው በያኔው መንዝና ወሎ አገረ ስብከት ተሾሙ፡፡

የኢጣሊያ ፋሺስት በ1928 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ላይ የግፍ ጦርነትን ባነሣ ጊዜ ብፁዕ አቡነጴጥሮስ ከጦር ስፍራ ለመለየት ስላልሆነላቸው፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ተከትለው ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ዘምተዋል፡፡ ፋሺስቱ በማይጨው የመርዝ ጦርነት ከማድረጉ የተነሣ፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሲበታተንም ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የተመለሱት አቡነ ጴጥሮስ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄደው ለአገርና ለነፃነት መሞት ቅዱስ ተግባር መሆኑን ለሥላሴ አርበኞች በመስበክም ይታወቃሉ፡፡ አርበኞች አዲስ አበባን በሁለት አቅጣጫዎች ከሰሜናዊ ምዕራብ እና በደቡባዊ ምሥራቅ አቅጣጫ ለመቆጣጠር ውጊያ በከፈቱበት ጊዜ የተማረኩት አቡነ ጴጥሮስ፣ ለፋሺሽት እንዲገዙ የኢጣሊያ መንግሥት ገዢነትንም አምነው አሜን ብለው እንዲቀበሉ ግፊት ቢያደርጉባቸውም፤ እምቢኝ ለሀገሬና ለሃይማኖቴ ብለው ለሰማዕትነት ያበቃቸውን የሞት ጽዋ ተቀብለዋል፡፡

አቡነ ጴጥሮስ ከሚገደሉበት ስፍራ ሲደርሱ አራቱን ማዕዘን በመስቀላቸው ባረኩ፡፡ በህዝቡም ፊት ቆመው እንዲህ አሉ፡፡ “ፋሽስቶች የአገራችንን አርበኞች ሽፍታ ቢላቸውም እውነት አይምሰላችሁ፡፡ ሽፍታ ማለት አለሀገሩ ሀገሩ መጥቶ የሰውን ሀገር የሚወር፣ ይህ በመካከላችሁ የቆመ አረመኔው ፋሽስት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ለእሱ እንዳይገዛ ውጉዝ ነው፡፡ የኢትዮጵያም መሬት እንዳትቀበለው የተገዘተች ትሁን፡፡” ብለው ተናገሩ፡፡

« እኔ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ፡፡ ሓላፊነትም ያለብኝ የቤተክርስቲያን አባት ነኝ፡፡ ስለዚህ ስለሀገሬና ስለ ቤተ ክርስቲያኔ እቆረቆራለሁ፡፡ . እኔን ለመግደል እንደወሰናችሁ አውቃለሁ፡፡ ስለዚህ በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ፡፡ ግን ተከታዮቼን አትንኩ» ሰማዕተ ጽድቅ በሆነ ደማቸው አተሙ፡፡ አኩሪ በሆነ አባታዊ ሓላፊነታቸው ለአገር፣ ለቤተክርስቲያን፣ ለወገን ሁሉ አለኝታነታቸው አረጋግጠው ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም. በሰማዕትነት አለፉ፡፡

ሐምሌ 22 ቀን 1928 ስምንት ወታደሮች በስተጀርባቸው ሃያ እርምጃ ርቀው ተንበርክከው በተንጠቀቀ ቆሙ፡፡ ወዲያው አዛገፉ «ተኩስ» በማለት ትእዛዝ ሲሰጥ ስምንቱም ተኩሰው መቷቸው፡፡ ግን በስምንት ጥይት ሳይሞቱ ቀሩ፡፡ መሞታቸውንና አለመሞታቸውን ለማረጋገጥ ዶክተር ተጠራ፡፡ ዶክተሩም እንዳልሞቱ አረጋገጠ፡፡ ከዚያም ሌላ ወታደር በሦስት የሽጉጥ ጥይት ራስ ቅላቸውን መትቶ ገደላቸው፡፡ የብፁዕነታቸውን አኩሪ ታሪክ ትውልድ ሲያዘክርላቸው እንዲኖርም መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ ሐምሌ 16 ቀን 1938 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ እምብርት ሐውልት ቆሞላቸዋል፡፡

ለፒያሳ (አራዳ) ግርማ ሞገስ በመሆን ሕያው ተጋድሎን ሲዘክር የኖረው የአቡነ ጴጥሮስ ሀውልት በአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ምክንያት ከቦታው ተነሥቶ 5ኪሎ በሚገኘው ብሔራዊ ሙዚየም ጊቢ ውስጥ ከ2 ዓመታት በላይ ያሳለፈ ሲሆን ጥር 29 ቀን 2008 ዓ/ም ዕለት እሑድ ወደ ቀድሞ ቦታው ተመልሷል፡፡ የአቡነ ጴጥሮስ አደባባይ ከቀደሙት ጊዜያት በተለየ ሁኔታ ሀውልቱ ላይ ሊከሰት የሚችለውን የተሽከርካሪ አደጋ ሊከላከል በሚችል መልኩ ጥናት ተደርጎበት በአዲስ መልክ ተገንብቷል፡፡ አደባባዩ ፋውንቴን ፣ አረንጓዴ ስፍራ እና ማረፊያ ቦታዎችንም አካቷል፡፡

# ከችግኝ ተከላው...

*ከገጽ 28 የዞረ*

በረሃብ የረገፉት ተፈጥሮ ፊቷን በማዞሯ ነው፡፡ ጀግኖቹ በወረርሽኝ ተረትተው በሜዳ የቀሩት ተፈጥሮ ከከርሷ ባስተነፈሰችው ገዳይ መርዝ ነው፡፡ ለዚህ ሁሉ ዕልቂትና ዘርፈ ብዙ ችግር የዳረገን የምዕራባውያኑ ቸልተኝነትና የተፈጥሮን ነባራዊ ዑደት እንዲዛባ ባደረጉበት የርስ በርስ ፉክክር መሆኑ ግልፅ ቢሆንም የነበረንን የተፈጥሮ ድቅድቅ የደን ሀብት በረባ ባልረባው መጨፍጨፍን የሀገራችንን ተራሮች ራቁት እንዲቀሩ ማድጋችንም ለደረሰብንና እየደረሰብን ላለው ሁሉ የራሱ እገዛ የለውም ማለት አንችልም፡፡ አሁን ግን እጅግ ዘግይተንም ቢሆን የነገሩ መነሻ ገብቶን መፍትሔው ላይ መረባረብ ጀምረናል፡፡ በጠ/ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አዝማችነት ሀገራችንን አረንጓዴ ለማልበስ ክተት አውጀናል፡፡

## የዐቢይ 4 ቢሊየን ችግኞች፤

በጠ/ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ ሀሳብ አመንጪነትና የዘመቻ አስጀማሪነት ባለፈው ሰኞ ሀምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም በመላ ሀገሪቱ በተከናወነው የችግኝ ተከላ አረንጓዴ ዘመቻ በአንድ ቀን 2 መቶ ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ዕቅድ ተይዞ የተገኘው ውጤት ከተጠበቀው በላይ ሆኗል፡፡ የብሔራዊ ደን ልማት አስተባባሪው ዶ/ር ተፈራ መንግሥቱ እንደገለፁት በሰኞ ዕለቱ አረንጓዴ ዘመቻ ከ23 ሚሊየን በላይ ኢትዮጵያውያን ተሳትፈው 350 ሚሊየን ችግኞችን በመትከል የዓለም ክብረ ወሰንን የሠበረ አኩሪ ተግባር ፈፅመዋል፡፡

"አረንጓዴ አሻራ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት በጠ/ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ ጠንሳሽነት የተጀመረው ችግኝ የመትከል ዘመቻ በአንድ ቀን 2 መቶ ሚሊዮን ችግኞችን፣ በአጠቃላይም 4 ቢሊዮን ችግኞችን በኢትዮጵያ ምድር የመትከል አላማ አንግቦ የተጀመረ ሲሆን፣ እስካሁን በዚህ ተግባር የዓለምን ክብረ ወሰን ይዞ የቆየችው ህንድ ካከናወነችው በ6 ዕጥፍ በላቀ መልኩ ውጤታማ ለመሆን ተችሎበታል፡፡ በአንድ ቀን ከ350 በላይ ችግኞችን የተከለችው ሀገራችን ኢትዮጵያ በቀጣይ ቀናት በዓለም የድንቃ ድንቅ ተግባር መዝገብ (ጊኒስ ቡክ ኦፍ ሪከርድስ) ስሟ በክብር የሚሰፍርበት ስራ እየተከናወነ እንደሚገኝም ተረጋግጧል፡፡

የዶ/ር ዐቢይ የ4 ቢሊዮን ችግኞች አረንጓዴ ዘመቻ አሁንም በተለያዩ የአገራችን ከተሞችና የገጠር ቀበሌዎች መከናወኑ እንደቀጠለ ሲሆን በቅርቡ ሙሉ በሙሉ መተግበሩ በይፋ እንደሚታወጅ ይጠበቃል፡፡

## ችግኞቹ እንዴት ተቆጠሩ?

የሚተክሉ ችግኞችን በቁጥር ለይቶ የማወቅ ተልዕኮ አንግቦ ስራውን የሰራው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሲሆን፣ ይህንኑ ተግባር የሚከውን ቡድን አቋቁሞ ነው ስራውን የጀመረው፡፡ ይህ ቡድን የሚተከሉ ችግኞችን የመቁጠርና የመመዝገብ ሀላፊነት ወስዶ ወደ ስራ ሲገባ ለዚህ ተግባር አጋዥ የሚሆን አዲስ ሶፍትዌርም ሠርቶ በስራ ላይ አውሏል፡፡ የቡድኑ አስተባባሪና በሶፍትዌር ፈጠራው ላይ አስተዋፅዖ ያበረከቱት አቶ ኢምራን አቡበከር እንደገለፁት ሶፍትዌሩ በችግኝ ተከላ ጣቢያዎች በተመደቡ ባለሙያዎች ስልክ ላይ ብቻ የተገጠመ ሲሆን፣ ባለሙያዎቹ በቦታው ተገኝተው የተተከሉ ችግኞችን ብዛት በቁጥር የሚያስተላልፉበት አሰራር ያለው ነው፡፡

ለችግኝ ተከላው ዘመቻ ማከናወኛ እንዲሆኑ በተመረጡ ስፍራዎች የተሰማሩት ባለሙያዎች በዓይናቸው እያዩ የቆጠሯቸውን የተተከሉ ችግኞች ቁጥር ወደዚህ ሶፍትዌር ሲያስገቡ ሶፍትዌሩ አጠቃላዩን ድምር አስልቶ እንዲያሳውቅ ተደርጎ መሰራቱን የገለፁት አቶ ኢምራን ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ባደረጉት ቁጥሩን የመለየት ጥረት በመላ ሐገሪቱ የተተከሉት ችግኞች ብዛት ከ350 ሚሊየን የሚልቅ መሆኑን ለማረጋገጥ እንደተቻለ አመልክተዋል፡፡ ይህ የችግኞቹን ብዛት በቁጥር ለመለየት ያስቻለው አዲስ ሶፍትዌር ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች የተሰራ መሆኑ ሲታወቅ፣ ሀገራችን በቴክኖሎጂ ፈጠራ ረገድ ብዙ ብቁ ባለሙያዎችን እያፈራች ለመሆኗ አይነተኛ ማሳያ ተደርጎ የሚቆጠር መሆኑም በሰፊው እየተነገረለት ይገኛል፡፡

## ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሚዲያዎች፤

የኢትዮጵያ "አረንጓዴ አሻራ" ችግኝ ተከላ ዘመቻ የበርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማትንና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሚባሉ ታዋቂ ሚዲያዎችን ትኩረት ለመሳብ ችሏል፡፡ ከመንግስታቱ ድርጅት (ተመድ) ጀምሮ በተዋረድ እስከ አህጉር አቀፍ ድርጅቶች ድረስ ያሉ በርካታ ተቋማት ዘመቻውን መጀመር በአዎንታዊ ጎን አጉልተው ሀገሪቱ የጀመረችውን የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር አድንቀዋል፡፡

በኢትዮጵያ 35 በመቶ የነበረው የደን ሽፋን ወደ አራት በመቶ ማሽቆልቆሉን ያመለከተው ተመድ ሀገሪቱ የጀመረችው የችግኝ ተከላ ዘመቻ ከራሷ አልፎ ለአለም የሚኖረውን ብርቱ ጥቅም በመጥቀስ ተግባሩን አወድሷል፡፡ ሌሎቹም ዓለም አቀፍና አሕጉር አቀፍ ድርጅቶችም ይህንኑ የተመድ መወድስ ተጋርተውታል፡፡

እንደዚሁ ሁሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ የበዛ ተሰሚነት ያላቸው ታዋቂ የሚዲያ ተቋማትም "ለአረንጓዴ አሻራ" ዘመቻ የዘገባ ሽፋን የሰጡት ሲሆን፣ ቢቢሲ፣ ኦሶሼትድ ፕሬስ፣ ዘኔሽን፣ ዋሽንግተን ፖስት፣ ዘጋርዲያን፣ ሬውተርስ፣ አልጀዚራ፣ ሲኤንኤን፣ ዘ ኢንዲፔንደንት እና ሌሎች ሚዲያዎች ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ዜናውን በዓለም ሁሉ አሰራጭተውታል፡፡

ፋርም አፍሪካ የተባለው ታዋቂ ግብረ ሰናይ ተቋም የችግኝ ተከላ ዘመቻውን በሚመለከት ባወጣው መግለጫ ሁሉም ዜጋ፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የንግዱ ማህበረሰብ በችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩ ከፍተኛ ርብርብ በማድረጉ በህንድ በአንድ ቀን ተተክሎ የነበረውን 66 ሚሊዮን ችግኝ ሪከርድ መስበር ተችሏል ብሏል፡፡

በኢትዮጵያ በአንድ ቀን የተተከሉትን 350 ሚሊዮን ችግኞች በአለም ክብረወሰንነት የመመዝገብ ሀላፊነት ያለበት ጊነስ ቡክ ኦፍ ሪከርድስ የዛፍ ተከላ ክብረ ወሰኑን እንዲመዘግብ ተጋብዞ የነበረና የተቋሙ ተወካዮች ለፕሮግራሙ አለመድረሳቸውን የገለፁት የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ሁሴን "አሜሪካ ባለው ኤምባሲ በኩል ጥሪ ደርሷቸው ነበር፡፡ አምባሳደር ፍፁም አረጋ ጉዳዩን ይዞት ነበር፤ ነገር ግን ለፕሮግራሙ አልደረሱም፡፡ ተከላውና የቆጠራው ሂደቱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የውጭ ዜጎችም እንዲያዩት ክፍት ሆነ ነበር፡፡ ነገር ግን የእኛ ሀሳብ ከዛ የዘለለ ነው፡፡ አሁን ይህን ያክል ስራ ከሰራን መድገምም እንደምንችል እናውቃለን" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

## የትግራይ "ዘመቻ መለስ ለአረንጓዴ ልማት" ለምን?

በጠ/ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ የሀሳብ ጠንሳሽነትና የዘመቻ አነሳሽነት በመላ ሀገሪቱ ተግባራዊ የተደረገው "የአረንጓዴ አሻራ" የዛፍ ተከላ ዘመቻ በትግራይ ክልልም የተከናወነ ሲሆን፣ የትግራይ ክልል መንግሥት ለዘመቻው "ዘመቻ መለስ ለአረንጓዴ ልማት" የሚል ስያሜ መስጠቱ ግን ብዙዎችን ግራ አጋብቷል፡፡

የሀሳቡ አፍላቂና የዘመቻው አስጀማሪ የሆኑት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ሆነው ሳለ የትግራይ መስተዳደር ለዘመቻው ተለዋጭ ስያሜ መስጠቱን እንደ ትንኮሳ የቆጠሩ አንድ የፖለቲካ ምሁር ምናልባትም ለጠ/ሚ/ር ዐቢይ ተግባር ዕውቅና ለመንፈግ የታለመ ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን ሰንዝረዋል፡፡

የዘመቻውን መከናወን አስመልክተው ደስታቸውንና ምስጋናቸውን ያቀረቡት ጠ/ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው የሰው ልጅ ከአፈር ተፈጥሮ ወደ አፈር የሚመለስ መሆኑን በመጥቀስ አፈርን በእጅ መንካትና ከአፈር ጋር መለማመድ መልካም እንደሆነ የገለፁበት የመልዕክታቸው ክፍል ውስጠ ወይራ እንዳለው የጠረጠሩ አንድ አንጋፋ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ በበኩላቸው ይህን የጠ/ሚ/ር ዐቢይን ንግግር የትግራይ ክልል ፕሬዚዳንቱ ዶ/ር ደብረፂዮን በችግኝ ተከላ ዘመቻው በተሳተፉ ጊዜ አፈር በአካፋ ዝቀው የችግኙን ጉድጓድ ሲሞሉ ከመታየታቸው ጋር አያይዘውታል፡፡ ዘመቻው በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲከናወን በአዋጅ መልክ ይፋ ሲደረግ ለዘመቻው አንድ ወጥ የሆነ ስያሜ የተሰጠውና "የአረንጓዴ አሻራ ቀን" ተብሎ በግልፅ የተቀመጠ መሪ ቃል ቢኖርም የትግራይ መንግስት ከዚህ ብሔራዊ የዘመቻው ስያሜ ይልቅ የራሱን ስያሜ ለማበጀት መፈለጉና በተለይም ዘመቻውን ከሟቹ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር ማያያዙ ለብዙዎች የሚዋጥላቸው ካለመሆኑም ባሻገር አሁንም የትግራይ መንግሥት ለፌደራል መንግስቱ ጋር በትብብር ላለመስራት በማንገራገር ላይ እንደሆነና ከተንኳሽ አካሄዱ መቆጠብ እንደማይፈልግ በግልፅ ያሳየበት እንደሆነ አድርገው የሚቆጥሩት መሆኑን በርካታ አስተያየት ሰጪዎች ሲናገሩ ተደምጧል፡፡ የትግራይ ክልል መንግሥት የዘመቻውን ጥሪ ተቀብሎ የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩን ማከናወኑ በበጎ መልኩ የሚታይ ቢሆንም የዘመቻውን ብሔራዊ ስያሜ መለወጡ ግን ተገቢ እንዳልሆነ ሰፊ አስተያየት እየተሰጠበት ይገኛል፡፡

## ማጠቃለያ

በዶ/ር ዐቢይ አህመድ የሀሳብ ጠንሳሽነት ሰኞ ሀምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወነው የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ከታሰበለት ዓላማ በላይ ግቡን መትቷል፡፡ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል አሳታፊ ለማድረግ የመንግሥት ተቋማት ለግማሽ ቀን ዝግ እንዲሆኑ በተደረገበት በዚህ ዘመቻ ከ23 ሚሊዮን የሚልቁ የሀገሪቱ ዜጎች ተሳታፊ ሆነውበት በአንድ ቀን 353,633,660 (ሶስት መቶ ሃምሳ ሶስት ሚሊየን ስድስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ) ችግኞች ተተክለዋል፡፡ ይህም በረሃብ፣ በሽታና ጦርነት ትታወቅ የነበረችውን ሀገራችንን አዲስ ፀዳል የተላበሰች የተስፋ ምድር እንድትሆን የራሱን በጎ ሚና የሚጫወት አኩሪ ተግባር ሆኖ በቅርቡ በዓለም መዝገብ ላይ ስሟን በክብር እንደሚያስመዘግበው ተስፋ ተጥሎበታል፡፡

ኢትዮጵያውያን ከተባበርንና ከተደማመጥን ከዚህ የላቀ ብሔራዊ ስኬትና ድል ማስመዘገብ የምንችል ስለመሆናችንም ብርቱ ተጨባጭ ማሳያ ሆኖ በምሣሌነት ይጠቀሳል፡፡ ከመነጣጠልና ከመለያየት ይልቅ አንድ ብንሆን፣ ከጥላቻና ከበቀል ይልቅ በፍቅር ብንጋመድ፣ ከመናናቅና ከመተቻቸት ለጋራ ጥቅም ብንተባበር የማንወጣው ዳገት እንደሌለ ታሪካዊ ማረጋገጫችን በመሆን የሚጠቀስልን አኩሪ ገድላችን ሆኖም ተመዝግቧል፡፡

# “ካለንበት የመጠፋፋት...

*ከገጽ 6 የዞረ*

ይሄንን ፕሮጀክት፤ ክፍል ሁለት ብለን አፍሪካ ላይ የተጀመረ ዶክመንተሪ እየሰራን ነው ያለነው፡፡ ትንሹን ትልቅ በማድረግ፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ የተለያዩ አፍሪካ ሀገሮች ሄደን በመስራት ስራውን የማሳደግ ዕቅድ ነው ያለን፡፡ ሐሳቡ አንድ አገር ወይም አካባቢ ላይ ብቻ ተወስነህ የምትሰራው አይደለም፡፡ በዛው ልክም ጀምረህ የምትተወው ተራ ፕሮጀክት አይደለም፡፡ ዛፎችን አለመትከል ነገ በልጆቻችን ላይ ምን ያህል ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ገብቶት፣ ችግኞች በደንብ መትከልና መጠበቅ አለብት የሚል እምነት ስላለኝ እስከምችል ድረስ እሰራለሁ፡፡

የተማርኩበት ት/ቤትና ሌሎች ዩንቨርስቲዎችም ሆነ በአንዳንድ ቦታዎች ሲጋብዙኝ ሄጄ ችግኞችን እተክላለሁ፡፡ ሄጄ ውሃ ካላጠጣሁትና በደንብ ተንከባክቤ ካላሳደግሁት፣ ይሄን ብቻ ማድረጉ በቂ ነው ብዬ አላምንምና፤ በዋናነት ካላደረግነው ያለውን ጉዳት፣ ስናደርገው ደግሞ ጥቅሙ ምን ያህል እንደሆነ፤ በሰው ጭንቅላት ውስጥ መግባት አለበትና እዛ ላይ ማተኮሩን እወደዋለሁ፡፡

**ግዮን፡- ሐምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር አከናውኗል፤ ይሄንንስ እንዴት አየሽው?**

አምለሰት፡- ሰው አካባቢውን መጠበቅ ያለበት በየቀኑ ነው፡፡ በአንድ ቀን ሕዝብ ሆ! ብሎ ወጥቶ ችግኝ እንዲተክል፣ የዛፍ ጥቅምን እንዲያውቀው ማድረግ በራሱ ትልቅ ነገር ነው፤ ያልተለመደም ነገር ነው፡፡ የእኛ ሰው አትክልት፣ ግሪን ኤሪያ ምናምን ብዙም ስሜት አይሰጠውም፡፡ ሰሞኑን በተካሄደው መርሃ ግብር የጉዳዩ ጠቀሜታነት ለሰው ስሜት እንዲሰጠው በመደረጉ ደስ ብሎኛል፡፡

አካባቢን መጠበቅ ማለት ያው ዞሮ ዞሮ ራሳችንን መጠበቅ ማለት ነውና በእንዲህ ዓይነቱ መንገድ በሕዝብ ላይ መነቃቃት መፈጠሩ ይበረታታል፡፡ ምናልባት ከዚህ ሁሉ ሕዝብ የተወሰነው ሰው ዓላማውን ሊቀጥልበት ይችላል፡፡ በደንብ ገብቶትም ይሆናል የሚያደርገው፤ ካለማድረግ ማድረግን የመሰለ ነገር የለምና ሐምሌ 22 የተካሄደውን የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻን ሳላደንቅ አላልፍም፡፡ እኔም ከልጆቼ ጋር በዕለቱ ወጥቼ ችግኞችን ተክያለሁ፡፡

**ግዮን፡- የቴዲ አፍሮ “ማር እስከ ጧፍ” ዜማ ክሊፕ በጣም ተወዳጅ ሆኗል፡፡ ዳይሬክተሯም አንቺ ነሽ፣ ይህ ዘፈን ከአልበሙ ውስጥ እንዴት ሊመረጥ ቻለ?**

አምለሰት፡- ማር እስከ ጧፍ፤ ከፍቅር እስከ መቃብር መጽሐፍ ውስጥ የተወሰዱ ሀሳቦች ናቸው በብዛት ያሉበት፡፡ ይህን መጽሐፍ ደግሞ ብዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንብቦታል፣ ወይም ሲተረክ አድምጧል፡፡ እኔም ደጋግሜ መጽሐፉን አንብቤዋለሁ፤ ከቴዲ ጋር ደግሞ ብዙ ጊዜ የወጋየሁን ትረካ እናደምጠው ነበር፡፡


በጣም የምነሸጥበት ስራ ነበር ፍቅር እስከ መቃብር፡፡ እንደውም ፊልም አድርጎ የመስራት ዕቅድ ከበፊት ጀምሮ ነበረኝ፤ ቴዲ ሙዚቃውን ከሰራው በኋላ ደግሞ የበለጠ ተነሳሳሁ፡፡ ካልወደደው ሊከፋ ይችላል በሚል እንደ ክሊፕ ሳይሆን እንደ ፊልም ሠራነውና ቴዲ እንዲያየው አደረግን፡፡ ቀረፃው አስራ ሁለት ቀን ፈጅቶብናል፡፡

ክሊፑ ላይ የተሳተፉትን ሰብስበን በሚኒባስ ወደ ደብረ ማርቆስ ሄድን፡፡ አንድ ገጠር ውስጥ ገብተን ግቢ ሰጡን፣ እዛ ውስጥ ነው በብዛት ቀረፃውን ያደረግነው፡፡ በጣም ደስ የሚል ነገር ነው ያየነው፡፡ ባህሉ፣ ደግነቱ፣ የሰው አቀባበል መልካም ስለነበረ በደንብ አሰርቶናል፡፡ እዛ ጋር በትክክል ብሉ፣ ጠጡ፣ የሚለው ሃገራዊ ስሜት ነበር፡፡ እልልታ፣ ጭፈራ፣ እስክስታው በትክክልም አለ፡፡ ያ ሁሉ ስሜት ነው ሰው ጋር ሄዶ ያረፈው፡፡ እኔ ራሴ መጀመሪያ ላይ በዚህ መጠን ይወደዳል የሚል ዕምነት አልነበረኝም፡፡

የቴዲን ዘፈን በክሊፕ ለመስራት መነሳት ቀላል አይደለም፡፡ እኛ ተጨማሪ ድምፅ ሁሉ አስገብተንበት ነበር የሰራነው፤ ካልወደደው አጭር የፍቅር እስከ መቃብር ታሪክ አድርጌ አወጣዋለሁ በሚል ዕሳቤ ነው የተሰራው፡፡ ጨርሰን ስናሳየው ግን ወደደው ፣ ኤዲቲንጉ ላይ እንደውም እሱም በደንብ ተሳታፊ ሆኖ ሲያግዘን ሳየው ደግሞ ደስ አለኝ፡፡

**ግዮን፡- ቀረፃውን ስትጀምሩም ሆነ ደብረማርቆስ ስትቀመጡ ቴዲ አያውቅም ነበር? አልተነጋገራችሁም?**

አምለሰት፡- አልተነጋገርንም፡፡ ራሴ ነኝ ፕሮዲዩስ ያደረግሁት፡፡ እንደውም እሱን ብር አልከፈለኝም፤ አስታወስከኝ፣ እቀበለዋለሁ፡፡ ለእሱ መንገር ያልፈለግነው ቴዲ ክሊፕ ውስጥ መግባት ስለማይወድ ነው፡፡ ክሊፕ ውስጥ ያለው ይሄ መወዛወዝ፣ መደነስ የሚባሉት የእሱ ነገሮች አይደሉም፡፡ በዛ መንገድ የእሱን ተሳትፎ ልንጠይቀው ስለማንችል፣ ክሊፑን ባያችሁት መልኩ ፃፍኩትና የሆነ ሰዓት ላይ፤ “ፊልሙን ከወደድከው ይህቺን ብቻ ትገባለህ” ብዬው፣ ክሊፑ ሲጀምር ቴዲ የሚታይበትን ፓርት ከጨረስን በኋላ ተመልክቶት፣ ቤት ውስጥ ነው የቀረፅነው፡፡



ስንጨርስ ስክሪፕቱን አይቶ ወደደው፣ የተቀረፁትንም ነገሮች አያቸው፤ ከዛ በደንብ ቁጭ ብሎ ኤዲት አስደረገው፡፡ የእሱ ተሳትፎ ደግሞ የበለጠ አሳመረው፡፡ ፍቅር እስከ መቃብርን በጣም ስለሚወደው የቀረፅነውን ካየ በኋላ ደስ ብሎት ነበር ኤዲቲንጉን ያገዘን፡፡ የወጋየሁን ትረካ ሁልጊዜ ይሰማዋል፤ የሆነ ወቅት ላይ እንደውም ማታ ማታ እሱን እያዳመጥን ነበር የምንተኛው፡፡

**ግዮን፡- በቅርቡ ቴዲ በአሜሪካ ሁለት ሽልማቶችን አግኝቷል፡፡ ይህ ክብር በሁለታችሁ ላይ ምን ዓይነት ስሜት ፈጠረ?**

አምለሰት፡- ይሄን ጥያቄ እሱ ቢመልሰው ይሻላል፡፡ በርግጥ ያገኘው ሽልማት ደስ ይላል፡፡ እንደ ፋሚሊ እኔም ልጆቼም በጣም ነው ደስ ያለን፡፡ ሕዝብ እንደሚደሰተው ተደስተናል፤ ከዛ ከፍ ሲል የቴዲ ቤተሰቦች በመሆናችን ደግሞ የበለጠ ተደስተናል፡፡

እንኳን የራስህ ሰው፣ የአገርህ ዜጋ የሆነ ኢትዮጵያዊ እንዲህ ዓይነት ክብር ሲያገኝ ያስደስታል፡፡ መመስገንን የመሰለ ነገር የለም፡፡ በጎ ለሚሰራውም በጎ እንዲሰራ መልካም የሚያስበውም ጥሩ እንዲያስብ መመስገን ትልቅ ብርታት ነውና፡፡

**ግዮን፡- ከሃገራችን አጠቃላይ ወቅታዊ ጉዳዮች በመነሳት ስለ ፍቅር፣ ስለ ሰላም፣ ምንድን ነው የምታስተላልፊው መልዕክት?**

አምለሰት፡- በሰላም ወጥቶ በሰላም መግባት፣ ስራን በአግባቡ መስራት፣ ልጆችን በፍቅር ማሳደግና በሰላም መኖር የማይፈልግ ሰው የለም፡፡ ምንም ዓይነት የሐሳብ ልዩነቶች ቢኖሩም የመግባባት፣ የመደማመጥ የመሸናነፍ፣ “አንተ ትብስ” “አንቺ ትብሽ” ብሎ የአብሮነት ስሜትን ማዳበር አቅቶን ነው እንጂ እንዲህ የምንቸገረው ሁሉም ሰው ሰላምና ፍቅርን ይፈልጋል፡፡

መግባባትና መቻቻሉ ላይ ብናተኩር ይበጀናል፡፡ ሰው ጥላቻን አርቆ ቢዋደድ፣ ቢፋቀር የበለጠ ሰላምን ማስፈን ይቻላል፡፡ የእኛ ያልሆነ መቼ እንደምንሞት የማናውቅበት፣ ወጥተን መመለሳችንን ርግጠኛ የማንሆንበት ሕይወት ይዘን፤ ሰውን መግፋትና ፍቅርን ማጥፋት ተገቢ አይደለም ብዬ አምናለሁ፡፡

ሁላችንም ራሳችንን የምናዳምጥበት፣ እኔ ተሸንፌ ምን መፍጠር፤ ምን ማድረግ እችላለሁ? የሚል እልህ ውስጥ ሳንገባ፣ በጥሞና ነገሮችን የምናልበፍበት ጊዜ እንዲሆን እግዚአብሔርም እንዲረዳን ነው የምመኘው፡፡ አሁን አንዳንድ የምንሰማቸውና የምናያቸው ነገሮች ሁሉ የሰይጣን ናቸው፡፡ የሰይጣን ስራን የምናሸንፈው በጸሎት፣ በፍቅርና በሰላም ነውና ያንን እግዚአብሔር ያብዛልን፡፡ የገጠመን ነገር ፈተና ነው፤ ፈተና ደግሞ ያልፋል፤ የማያልፍ ነገር የለም፡፡ አሁን ወደ ጥፋት እየወሰዱን ካሉት ሰይጣናዊ ስራዎች፣ ከመጠፋፋትና ከመገፋፋት ፈተና ግን እንወጣለን፤ ካለንበት የመጠፋፋት ችግር እንደምንወጣ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ተስፋ ሳንቆርጥ እግዚአብሔር እንዲረዳን መጸለይ፣ መዋደድና መቻቻል ብቻ ነው ያለብን፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

# ከችግኝ ተከላው ወዲህና ወዲያ!

አለማየሁ ባዘዘው

ዓለማችን እጅግ አደገኛ ወደ ሆነ የተፈጥሮ ውድመት ልትሻገር ጥቂት አመታት ብቻ ቀርተዋታል። የዓለማችን የተፈጥሮ አየር መዛባት በይፋ ከተነገረበት ጊዜ ወዲህ ባሉት አመታትም እጅግ በከፍተኛ ፍጥነት ሙቀቷ ጨምሮ በየክፍለ ዓለሙም ዘግናኝ ውድመት ያስከተሉ የተፈጥሮ አደጋዎች ተከስተዋል። በዘርፉ ጥልቅ ምርምር ያደረጉ ልሂቃን እንደሚያምኑት ከሆነ ደግሞ መጪው ጊዜ ያዘለው አደጋ እስካሁን ከታዩት ሁሉ በብዙ ዕጥፎች የላቀ ነው። ምድርን ለማንም የማትሆን ምድረ በዳ የማድረግ አቅሙም እጅግ ከፍተኛ ነው።

ተመራማሪዎቹ እንደሚሉት የምድራችን ፍጡራን ሁሉ ሊቋቋሙት የማይችሉትን ሙቀት ማመንጨት ልትጀምር ጥቂት ብቻ ነው የቀራት። የምድር ሙቀት የያዘውን ፍጥነት ቀጥሎ በየዓመቱ 0.17 ሴሊሺየስ መጨመሩን የሚገታ ሀይል ካልተገኘ አይቀሬው ጥፋት እውን የሚሆንበት ጊዜ በጣም ቅርብ ነው።

የምድራችን ሀያል ስጋት የሆነው በተለይም የሠው ልጆችን ከምድር የማጥፋት አቅሙ ከፍተኛ የሆነው የሙቀት መጨመር ጉዳይ አሳስቧቸው በ2015 (እ.አ.አ) ጉባኤ የተቀመጡ የዓለም መንግሥታት ዓመታዊ የሙቀት ፈጣን ጭማሪውን በ2 ዲግሪ ሲልሺየስ ለመቀነስ በየሀገራቸው ብርቱ ስራ ሊሰሩ ተስማምተው የነበረ ቢሆንም፣ እየታየ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ግን የስምምነቱን መተግበር አያረጋግጥም። እንደተባባሪ ፕሮፌሰር ጆሃን ሮክስቶርም ዕምነት ከሆነ ደግሞ የምድር ሙቀት በየዓመቱ 0.17 ዲግሪ ሴልሺየስ መጨመሩ ካልተገታ የሠው ልጆች ሁሉ በምድር የመቆየት ዕድላቸው እጅግ አናሳ ነው የሚሆነው።

አሁን ከተፈጥሮ ሙቀት መጨመር ጋር ተያይዞ ሊደርስ የሚችለውን ከባድ ቀውስ በተወሰነ መልኩ እየተከላከሉ ያሉት የምድር በረከቶች ሆነው የሚገኙት በየአህጉሩ ያሉ ጥቅጥቅ ጫካዎች፣ የአርክቲክ ግግር በረዶ እና የውቅያኖሶች ቅዝቃዜ ብቻ ናቸው። እነዚህ የተፈጥሮ በረከቶች ግን በነበራቸው አቅም ልክ የሰውን ልጅ ከዕልቂት እየታደጉ ለመቀጠል የማይችሉበት አደጋ ተጋርጦባቸዋል። ሙቀት የሚያስነሳው ሠደድ እሳት፣ የግግር በረዶዎች በፍጥነት መቅለጥና የውቅያኖሶች ግለት መጨመር ነገሮች በአጭር ጊዜ መልካቸውን እየቀየሩ ስለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ ሆኗል። እናም አለማችን ራሷን ከዚህ የጥፋት አደጋ መከላከል የምትችልበትን አንዳች ተዓምራዊ መፍትሔ እስዳላበጀች ድረስ ምድር ባዶ የምትሆንበት ዘመን ሩቅ አይሆንም።

እንደ ተመራማሪዎች የጥናት ውጤት ከሆነ የሠው ልጆች ከመጪው ከባድ አደጋ ራሳቸውን ለማዳንና የምድር ቆይታቸውን ለማስቀጠል ያሏቸው የመፍትሔ አማራጮች በግልፅ ተለይተው ታውቀዋል። እነዚህም የተለያዩ ውጤቶችን ለማስገኘት ተብለው የሚቃጠሉ ግብዓቶችን በማስቀረት ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቁ የበካይ ጋዝ ልቀቶችን መቀነስ፣ ብዙ ደኖችን መትከል፣ ጥቅጥቅ የደን ሀብቶችን መንከባከብና ካርቦን ዳይኦክሳይድን ከካባቢ አየር ማስወገድ የሚችሉ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን ተግባር ላይ ማዋል ናቸው።

ሰፊው አለም በኢኮኖሚና ሀያል ሆኖ በመውጣት እሽቅድምድም ውስጥ ተዘፍቆ የነገን ክፉ እጣ ፈንታ የዘነጋ በሚመስልበት በዚህ ወቅት አገራችን ኢትዮጵያ ግን የድርሻዋን ለመወጣት የምትችለውን ሁሉ ለማድረግ ቆርጣ መነሳቷን በአረንጓዴ ዘመቻ አዋጅ በተግባር አሳይታለች፡ ፡ አራት ቢሊየን ችግኞችን በመትከል ምድርን ከጥፋት ለማዳን ቀዳሚዋ ዘማች መሆኗን በተጨባጭ አረጋግጣለች።

## የተፈጥሮ አደጋዎች በኢትዮጵያ፤

ሀገራችን ኢትዮጵያ በጀግንነትና በአትንኩኝ ባይ የነፃነት መንፈሷ ከምትታወቅበት መለያዋ በበለጠ መላው ዓለም የሚያውቃት በረሃብና በበሽታ ነው። እነዚህ የመልኳ መለያ ሆነው ዘወትር ስሟ በተነሳ ቁጥር አብረው የሚጠቀሱ ገጿን ያኮሰሱ አደጋዎች ደግሞ ከተፈጥሮ አየር መዛባት ጋር ተያይዘው የተከሰቱ ክፉ እጣዎቿ ናቸው። በሚሊየን የሚቆጠሩ ንፁሀን ዜጎቿ

ቀሪውን በገጽ 26 ይመልከቱ

